አሥራ ዘጠነኛ ትምህርት

የደኅንነት በረከቶች – ክፍል 3

ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አምነው በሚቀበሉበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር አስደናቂና የተትረፈረፉ የደኅንነት በረከቶችን በላያቸው ላይ ያፈስሳል። በዚህም አዲስ ሕይወትን ይሰጣቸዋል፥ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው በማድረግ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር ይላቸዋል፤ ከዚያም ከእርሱ ጋር መታረቃቸውን በማሳወቅ፥ የቤተሰቡ አካል ያደርጋቸውና በፊቱ ቅዱሳን ሆነው እንዲገኙ በሕይወታቸው ውስጥ ይሠራል። ሆኖም፤ እያንዳንዱን አማኝ ወደፊት የሚጠብቀው በረከት አለ፤ ይህም የክብር በረከት ነው። ስለሆነም ከዚህ ሕይወት ፍጻሜ በኋላ፥ አማኞች ሁሉ ዘላለማዊ የሆነ የክብር ሕይወት እንደሚያገኙ የተረጋገጠላቸው እውነታ ነው። ከዚህ በመነሣት በዚህ ሳምንት ስለሚመጣው የክብር በረከትና አማኞች ይህን የክብር በረከት የሚያገኙ ስለመሆናቸው ስላለው ዋስትና አብረን እናጠናለን።

መጀመሪያ ቀን – ክብር

በዚህ ዓለም ውስጥ ያሉትን በሽታዎችና የተለያዩ ሥቃዮችን በመመልከት፥ «ይህ ዓለም የከፋ ስፍራ ነው» ብላችሁ ያሰባችሁበት ጊዜ ይኖር ይሆን? «እርግጥ በዚህ ዓለም ውስጥ ብዙ የተዛነፉ ሁኔታዎች ሲከሰቱ እንመለከታለን። ልንገራችሁና የራሴም ሕይወት ቢሆን ችግር አለበት። ስለዚህ አካሉ በሕመም ምክንያት ኃይለኛ ስሜት የሚያመጣብኝ ጊዜ አለ። ላደርገው የማልፈልገውን ነገር ሳደርግ እገኛለሁ። የከፉ የኃጢአት ድርጊቶችንም እፈጽማለሁ። በዚህ ዓለም ላይ የእኔም ሕይወት ሆነ የዓለም ሁኔታ በትክክለኛው መንገድ እንደ ተመራ ቢኖር በጣም ደስ ባለኝ ነበር!» ሕይወታችንንም ሆነ፥ ይህን ዓለም በሚመለከት ብዙ የተበላሹ ነገሮች አሉ። የእግዚአብሔር የማዳን በረከቶች ግን እኛን ከእርሱ ጋር ለማስታረቅ በሂደት ላይ ናቸው። እግዚአብሔር በበረከቱ ሕይወትን ይሰጠናል፥ ከዚያም ከእርሱ ጋር መታረቃችንን በይፋ ይገልጥልናል። ቀጥሎም የቤተሰቡ አካል ያደርገናል፥ እንዲሁም በቅድስና ጎዳና ላይ ይመራናል። ይህም ሆኖ፥ ሥቃይና ከፋት በሰፈነበት ዓለም ውስጥ እንኖራለን። ሰውነታችንም በኃጢአት የተሞላ ርኩሰት ያሸነፈው በመሆኑ፥ ብዙ ጊዜ ከሥቃይ የራቀ አይደለም። ይህን እንጂ ክርስቲያኖች ሁሉ፥ ከዚህ ሕይወት በኋላ በሚመጣው ሕይወት፥ የክብር በረከቶችን እንደሚቀበሉ የተረጋገጠላቸው እውነታ ነው። መክበር የሚባለው፥ በመጨረሻው ጊዜ በሕይወታችንና በአካላችን ላይ ያለውን የኃጢአት መርገም የሚያስወግድልን የደኅንነት በረከት ነው። እንዲሁም መክበር፥ ሕይወታችንና አካላችንን እግዚአብሔር ወዳዘጋጀው የፍጹምነት ደረጃ የሚያደርስ የደኅንነት በረከት ነው።

1. እንከብራለን ሲባል ምን ማለት ነው?

1.1 መከብር (ክብር) ማለት ፍጹማንና ንጹሐን እንሆናለን ማለት ነው።

1ኛ ጥያቄ፡– 1ኛ ቆሮ. 1፡8 አንብብ። እግዚአብሔር ለአማኞች ምን ተስፋን ይሰጣል?

2ኛ ጥያቄ፡– ኤፌ. 5፡25–27 አንብብ። ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ሆና ትቀርባለች?

3ኛ ጥያቄ፡– ቆላ. 1፡22 አንብብ። እግዚአብሔር እኛን ከራሱ ጋር የማስታረቁ ውጤት ምንድን ነው?

4ኛ ጥያቄ፡– ይሁዳ 24 አንብብ። እግዚአብሔር ምን ያደርግልናል?

5ኛ ጥያቄ፡– 1ኛ ተሰ. 5፡23–24 አንብብ። እግዚአብሔር ታማኝ የሆነው ምን ሊያደርግልን ነው?

በምንከብርበት ጊዜ በመጀመሪያ የምንቀበለው በረከት፥ ያለነውር፥ ፍጹምና ንጹሕ መሆንን ነው። 1ኛ ቆሮ. 1፡8 ላይ እግዚአብሔር እስከ መጨረሻው ቀን ጠብቆ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከሚመለስበት ቀን ያለነቀፋ ሆነን እንድንገኝ ያደርገናል ይላል። ይህ የጌታችን የኢየሱስ ቀን የተባለው እርሱ ተመልሶ የሚመጣበት ቀን ነው። በዚህ ምድር ላይም ክርስቶስን አምነው እንደ አዳኛቸው ተቀብለው ያሉትን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በሰጣቸው ተስፋ መሠረት ኢየሱስ እስኪመለስ ድረስ በእምነታቸው የጸኑና የጠነከሩ፥ ከነውርም ሁሉ የጸዱ አድርጎ ይጠብቃቸዋል። ከኃጢአት ሁሉም የነጹ ይሆናሉ። በኤፌ. 5፡25–27 ውስጥ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ክርስቶስ ፊት የመቅረብዋን ሁኔታ፥ በሠርጋቸው ቀን ሙሽሪት ወደ ሙሽራው በምትቀርብበት አኳኋን መስሎ ጽፎታል። እንደሚታወቀው ሁሉ ሙሽሮች በሠርጋቸው ቀን ቆንጆ ልብስ ይለብሳሉ፥ ባማረ ሁኔታም ያጌጣሉ። በዚህን ዕለት ሙሽሪት በሁለመናዋ ያማረችና የደመቀች ሆና በሙሽራው ዓይን ትታያለች። ታዲያ ቤተ ክርስቲያን፥ በጌታ ኢየሱስ ፊት በምትቀርብበት ጊዜ፥ ፍጹም ለመሆን በመጣር ብቻ አትቀርብም፥ ነገር ግን እጅግ በጣም ፍጹምና እንከን የለሽ ሆና ትቀርባለች። ግለትም ያላንዳች ኃጢአት፥ እንከንና ነውር ሆና ፊቱ ትቀርባለች። እናም ፍጹም የሆነ ቅድስናን ትጎናጸፋለች። በቆላ. 1፡22 ላይም፥ እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ስለ አስታረቀን፥ ቅዱሳንና ንጹሐን፥ ነቀፋም የሌለብን አድርጎ በፊቱ አቆመን ይላል። በምንከብርበት ወይም ክብርን በምንጎናጸፍበት ጊዜ፥ ከኃጢአት ፈጽመን ለምን ጊዜውም እንነጻለን። ከዚህ በኋላ ማንም ሰው ቢሆን በኃጢአት ወይም በስሕተት አሳብቦ ሊከሰን አይችልም። በይሁዳ 24 ላይ እግዚአብሔር በደኅንነቱ ውስጥ እንደሚጠብቀንና በፊቱም ያላንዳች ነውር እንደምንቆም ተስፋ ይሰጠናል። በ1ኛ ተሰ. 5፡23–24 እግዚአብሔር ያላንዳች ነውር ጠብቆ ክርስቶስ ተመልሶ እስከሚመጣ ድረስ እንደሚያቆየን ያረጋግጥልናል።

6ኛ ጥያቄ፡– በቅርቡ ኃጢአት የሠራችሁበትን ጊዜ አስቡ። ስለዚህ ኃጢአት ለእግዚአብሔር ከተናዘዛችሁ በኋላ እንኳን ምን ተሰማችሁ?

አንዳንድ ጊዜ ሰይጣን ወደ እኛ ዘንድ ይመጣና ስለ ሠራናቸው ብዙ ኃጢአቶች ያስታውሰናል። ይህን በመሰለ ሁኔታ ወደ እኛ ይጠጋና በደላችንን እያነሳ፥ ፈጽሞ በእግዚአብሔር ፊት መቆም የማይገባን ኃጢአተኞች መሆናችንን እየነገረ ያስፈራራናል። ኃጢአታችንን በእግዚአብሔር ፊት የተናዘዝን ሆነን ሳለን እንኳን ቢሆን፥ ወደ እኛ ቀርቦ የኃጢአታችን ሸክም የከበደ መሆኑን እየወተወተ ማስፈራራቱን ይቀጥልበታል። ሰይጣን ይህን ያድርግብን እንጂ እግዚአብሔር እንደሚሰጠን ተስፋ ከሆነ፥ ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በከፈለው መሥዋዕትነት ኃጢአታችንን ይቅር በማለቱ፥ ከዚህ ሕይወት በኋላ የሥነ ተፈጥሮ ኃጢአት ጨርሶ ሊኖርብን እንደማይችልና፥ ከዚህም በስተቀር ኃጢአት የሚኖርበት ሥራ እንደማይሠራ ያረጋግጥልናል። በሁለመናችንም ፍጹማን ስለምንሆን፥ ሰይጣን ከዚያ ወዲያ እኛን የሚከስስበት ምክንያት ጨርሶ አይኖረውም። ክብርን በምንጎናጸፍበት ጊዜ፥ ከኃጢአት፥ ከበደልና ከክስ ነፃ እንሆናለን።

1.2 መከበር (ክብርን መጎናጸፍ) ማለት የአካላችን ወደ ፍጹምነት መታደስ ማለት ነው።

7ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮ. 15፡20፥ 42-44፥ 49-57 አንብብ። ሀ) ሐዋርያው ጳውሎስ አካላችን አሁን ምን ይመስላል አለ? ለ) ሐዋርያው ወደፊትስ አካላችን ምን ይመስላል አለ?

8ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ቆሮ. 5፡1 አንብብ። ሀ) ሐዋርያው ጳውሎስ ያሁኑን አካላችንን ከምን ጋር ያመሳስለዋል? ለ) ደግሞስ በሞታችን ጊዜ የምንለብሰውን አካል ከምን ጋር ያመሳስለዋል?

9ኛ ጥያቄ፡- ፊልጵ. 3፡21 አንብብ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ፥ ይህን የተዋረደውን ሰውነታችንን ወደ ምን ይለወጣል?

ይህ የለበስነው አካላችን ወደፊት በሚመጣው የክብር አካል እንደሚተካው ከሚያስተምሩት እጅግ ግልጽ ከሆኑት ክፍሎች አንዱ 1ኛ ቆሮ. ምዕራፍ 15 ነው። በ10ኛው ትምህርት ላይ እንደተከታተልነው፤ የክርስቶስ ትንሣኤ እርሱን እንደ አዳኛቸው አምነው ለተቀበሉት ሁሉ *የመጀመሪያው ፍሬ ወይም በኵር* ነው። የእርሱ ትንሣኤ የእኛን መጪውን ትንሣኤ ያረጋግጥልናል። እንዲሁም የክርስቶስ የተነሣው አካል፥ ለመጪው ለሚነሣው አካላችን ምሳሌ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚናገረው፥ በምንሞትበት ጊዜ የሚቀበረው አካላችን ጠፊ፥ ደካማ፥ ተፈጥሮአዊና ክብር የለሽ ነው። ነገር ግን ከሙታን በምንነሣበት ጊዜ፥ የማይጠፋና ሕያው፥ ክብርን የተጎናጸፈ፥ ኃይልና መንፈሳዊነትን የተሞላ አካል ይኖረናል። ጌታ ኢየሱስ ከሙታን በተነሣ ጊዜ እንደ ነበረው ያለ የተሟላ የሰው አካል ይኖረናል። ያሁኑ አካላችን ከአፈር የተሠራውን የአዳምን አካል የሚመስል ነው። ነገር ግን አካላችን ክብርን ሲለብስ ወይም ሲከብር፥ ከሰማይ የመጣውን የኢየሱስን አካል ይመስላል። ሐዋርያው ጳውሎስ «የማይጠፋ፥ ሕያው» ብሎ ሲል፥ በፍጹም የማይሞት አካል ይኖረናል ማለቱ ነው። የሰዎች የመጨረሻው ጠላት የሆነው ሞት ፈጽሞ ድል ይሆናል። የደኅንነት

የክብር በረከት፥ የማይታመም፥ የማይደክምና የማይሞት አካልን ይሰጠናል። ጳውሎስ በፊልጵ. 3፡21 ውስጥ፥ «እርሱ ይህን የተዋረደውን ሰውነታችንን በመለወጥ የእርሱን ክብሩ ሰውነት እንዲመስል ያደርገዋል» ይላል።

በ2ኛ ቆሮ. 5፡1 ውስጥ ጳውሎስ ይህን ሥጋችንን በድንኳን፥ ክብርን የሚጎናጸፈውን አካላችንን ደግሞ በእግዚአብሔር በታነጸ ዘላለማዊ መኖሪያ ይመስለዋል። ይህ ያለንበት አካላችን ጊዜያዊ ቤታችን ነው። ከዚህም የተነሣ ነው የሚያረጀው፥ የሚደክመውና ለሥቃይም በቀላሉ የሚጋለጠው። ነገር ግን ይህ ሕይወት ካለፈ በኋላ፥ ከምንኖርበት፥ የተደረተ ጊዜያዊ ድንኳን ወደ አማረና ለዘላለም ወደማያረጀው ቤታችን እንዛወራለን። እዚህ ላይ ጳውሎስ፥ ይህ አካላችን ከፈረሰ በኋላ፥ ነዋሪ ወደ ሆነው ዘላለማዊ ቤታችን እንገባለን ብሎ የተናገረውን በጥሞና አስቡ። አማኞች የሆኑ ሁሉ ከዚህ ዓለም በሞት በሚያልፉበት ጊዜ፥ ወዲያውኑ የክብር በረከት የተሞላበትን አካል ይለብሳሉ። የተለምዶ ስለሆነ፥ ቤተሰቦቻችን ወይም ወዳጆቻችን በሞት በሚለዩን ጊዜ እናዝናለን። ነገር ግን በሞት ምክንያት ከምንወዳቸው ሰዎች የመለየት ሁኔታ እንዲሁ የተለምዶ ነው ማለት አንችልም። ሞት የጎዘን ወቅት ቢሆንም፥ በተለይ በጌታ ኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ የጎዘናቸው ጊዜ ሆኖ ሊወሰድ አይገባም። ምክንያቱም በክርስቶስ ለሚያምኑት በሚሞቱበት ጊዜ ወቅቱ አሮጌና ጊዜያዊ ከሆነው የመኖሪያ ድንኳናቸው ወደ አማረውና ዘላለማዊ ወደ ሆነው ቤታቸው የሚዛወሩበት ጊዜ ስለሆነ ነው። ስለዚህ እንዲህ ላሉት አማኒያን በማንባት ፈንታ፥ በደስታ ልንሸኛቸው ይገባናል!

10ኛ ጥያቄ፡– 2ኛ ቆሮ. 4፡16–18 አንብብ። በክርስቶስ አማኝ የሆኑ ሰዎች ዛሬ ባሉበት ሁኔታ በአካላቸው ላይ ሥቃይ በሚደርስባቸው ጊዜ ስሜታቸው እንዴት ሊሆን ይገባል?

11ኛ ጥያቄ፡– ሀ) አሁን በቅርቡ ታምማችሁ ወይም ተሠቃይታችሁ ስለነበረበት ሁኔታ አስቡ። የሚመጣው የክብር ተስፋ እንዴት መጽናኛ ሊሆናችሁ ይችላል? ለ) አሁን በቅርቡ ስለ ሞተ ስለምታውቁት ሰው ለማሰብ ምክሩ። ለአማኞች ሁሉ የተሰጠው የክብር ተስፋ እንዴት መጽናኛ ይሆናችኋል?

አካላችን በክብር የመነሣቱ ተስፋ ከደኅንነት በረከቶች መካከል እጅግ በጣም አስደናቂው ነው። ዛሬ አመም ሲያደርገን፥ ወይም ሥቃይ ሲደርስብን፥ ከዕለታት አንድ ቀን በቅርቡ ጨርሶ ሥቃይ የሌለበት አካል እንደሚኖረን እናምናለን። ምንም እንኳን እርሱ በዚህ ሕይወት ሁልጊዜ ከሚደርስብን ሕመም ሳይፈውሰን፥ ወይም ከሚሰማን ሥቃይ ሳያወጣን ቢዘገይም፥ ይህ ሕይወት ካለፈ በኋላ ነዋሪውን አካል በምንለብስበት ጊዜ፥ በሽታና ሥቃይ ጨርሶ የማይኖርበትን ሕይወት በመኖር እንደምንደሰት ያረጋግጥልናል። እንደዚሁም፥ ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒታቸው ተቀብለው የነበሩ ወዳጆቻችን ወይም የቤተሰብ አባላት ሲሞቱ፥ በሕይወታቸው ሳሉ የደኅንነትን የክብር በረከት ያገኙ በመሆናቸው ደስ ልንሰኝ ይገባናል። እንዲያውም የእነርሱ ሁኔታ ከእኛ ይልቅ የተሻለ ነው። ምክንያቱም ወደ ዘላለማዊው ቤታቸው ገብተዋልና ነው! ስለዚህ፣ በማንኛውም ጊዜ ሥቃይ ሚደርስብን ጊዜ፥ ስለ ደረሰብን ሥቃይ ከማሰብና ከመጨነቅ ይልቅ፥

ዓይናችንን በሚመጣው ክብር ላይ ተክለን መላ አሳባችን ሁሉ በእርሱ ላይ ሊያርፍ ይገባል። ዛሬ የሚደርስብን ሥቃይ፥ ሊመጣ ያለው የእግዚአብሔር አስደናቂ የክብር በረከት መምጫ መንገድ ነው።

1.3 ክብር (መከበር) ማለት ፍጹም የሆነ እውቀት ይኖረናል ማለት ነው።

12ኛ ጥያቄ፡– 1ኛ ቆሮ. 13፡12 አንብብ። በዚያን ጊዜ ወደፊት እንዴት እናውቃለን?

በ1ኛ ቆሮ. 13፡12 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ጽኑዕ የሆነ ተስፋ ይሰጣል። ስለዚህም ሲገልጥ ሐዋርያው፥ በዚህ ሕይወት ሳለን ስለ መንፈሳዊ እውነታ የምናውቀው በጣም ጥቂት መሆኑን ይነግረናል። ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ መንፈሳዊ ሰጦታዎች ማወቅ ስለ እግዚአብሔር አንዳንድ ነገሮችን ያስተምረናል። ነገር ግን፤ በዚህ ሕይወት እያለን ስለ እግዚአብሔር የምናውቀው ድንግዝግዝ ባለ በመስተዋት እንደምናየው ዓይነት ነው። እንዲሁም ዛሬ ባለንበት ሕይወት ስለ እግዚአብሔር የምናውቀው፥ የሕግንን እውቀት ያህል ነው። ጳውሎስ እንደሚለው፤ ከርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ፥ ያን ጊዜ ፍጹም የሆነ እውቀት ይኖረናል።\እዚህ ላይ ጳውሎስ የሚናገረው እኛ ስለ እግዚአብሔርና ስለ እውነተኛው መንፈስ ያለንን እውቀት ነው። እነሆ፥ እኛ በማናውቀውና በማንገነዘበው ምሥጢራዊ መንገድ ስለ እግዚአብሔር የሚኖረን እውቀትና፥ የደኅንነታችን ምሥጢር በምንከብርበት ጊዜ ፍጻሜ ያገኛሉ። ኢየሱስን የማወቃችንና እርሱም ያደረገልንን ሁሉ የመገንዘባችን ሁኔታ፥ እኛ የተፈጠርንለትን ዓላማ በፍጹምነት የሚያሟላ ሂደት ነው። በምንከብርበት ጊዜ ያኔ እግዚአብሔር እኛ እንድናውቀው ባቀደልን መንገድ ልናውቀው እንችላለን።

13ኛ ጥያቄ፡– 1ኛ ዮሐ. 3፡2 አንብብ። ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ግንን እንመስላለን?

ምናልባት የክብር በረከት በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ስላለው ሁኔታ ማጠቃለል ብንፈልግ፡– . . .

❖ መከበር ማለት እኛ ኢየሱስን እንመስላለን ማለት ነው!

እዚህ ላይ ኢየሱስን እንመስላለን ሲባል፥ እኛ ራሳችን የኢየሱስን መለኮታዊ ባሕርያትን ሁሉ እንላበሳለን ማለት አለመሆኑን መገንዘብ ያሻል። እግዚአብሔር ብቻ አምላክ ስለሆነ ወደ ሰማይ በምንሄድበት ጊዜ እኛ እግዚአብሔርን መሆን አንችልም። ነገር ግን ኢየሱስን በሰብአዊ ፍጹምነቱ ልንመስል እንችላለን። ኢየሱስ ያላንዳች ነውር ፍጹም እንደ ነበረ ሁሉ፥ ንጹሕ እንደሆነ፥ እንዲሁም ቅዱስ እንደ መሆኑ ሁሉ፥ እኛም ነውር የሌለብን፥ ንጹሓንና ቅዱሳን እንሆናለን። በዚሁ ሁኔታ፥ ጌታ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ በሙሉ አካል እንደተገለጠው ሁሉ እኛም በትንሣኤ ሙሉ አካል ይኖረናል። እንደዚሁም ጌታ ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ፍጹም የሆነ እውቀት ያለበት ግንኙነት እንደ ነበረው ሁሉ፥ እኛም እንደ እርሱ ፍጹም

እውቀት ያለበት ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ይኖረናል። ስለሆነም መከበር ሲባል እኛ ኢየሱስን እንመስላለን ማለት ነው!

2. የእኛ መከበር በተቀሩት ፍጥረታት ላይ ምን ውጤት ይኖረዋል?

14ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 8፡18-23ን አንብብ። የእኛ መከበር (ክብርን መጎናጸፍ) በተቀሩት ፍጥረታት ላይ ምን ውጤት ይኖረዋል?

ጌታ ኢየሱስ ዳግም ተመልሶ በሚመጣበትና በእርሱም የሚያምኑ ሁሉ በሚከብሩበት ጊዜ፥ የመክበራችን ውጤት በተቀረው ፍጥረት ላይ ይፈስሳል። በሮሜ 8፡18-23 ጳውሎስ ሲናገር፣ የሰው ልጆች ካመጡበት የኃጢአት መርገም የተነሣ ፍጥረት ሁሉ እንዲሠቃይ ሆኖአል ይላል። ስለዚህ ከኃጢአት ውጤት የተነሣ በምንሠቃይበት ጊዜ ፍጥረት ሁሉ አብሮን ይሠቃያል። በአንጻሩ፥ የምንጎናጸፈው ክብር አሁን ያለብንን ሥቃይ ጠርጎ ስለሚያስወግደው፥ እንደዚሁ ሁሉ፥ የእኛ ክብርን መላበስ የፍጥረታት ሥቃይ ሁሉ እንዲያበቃ ያደርጋል። ስለዚህ ፍጥረት በመላው፥ እኛ ክብርን አግኝተን የኃጢአት ውጤት ሁሉ የሚወገድበትን ጊዜ በናፍቆት ይጠባበቃል። የምናገኘው ክብር አካላችንን የሚያድሰው ብቻ ሳይሆን፥ በዙሪያችን ያለውን ሥነ ተፈጥሮአዊ ዓለምንም አዲስ ያደርገዋል።

3. እንደምንከብር (ክብርን እንደምንጎናጸፍ) እንዴት እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን?

15ኛ ጥያቄ፦ ቲቶ 1፡2 አንብብ። የማይዋሸው አምላክ፥ በእርሱ ለተመረጡት የሰጠው ተስፋ ምን ነበር?

16ኛ ጥያቄ፦ ዕብ. 11፡16፥ 39-40 አንብብ። የእምነት አርበኞች ከእኛ ጋር ምንን ያገኛሉ?

17ኛ ጥያቄ፦ ያዕቆብ 2፡5 አንብብ። እግዚአብሔር በእምነት ለበለጸጉትና ለሚወዱት ምንን ሊሰጣቸው ተስፋ አደረገ?

18ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 8፡30 አንብብ። አስቀድሞ የወሰናቸው፥ ደግሞም የጠራቸውና ያጸደቃቸው ምን ይሆናሉ?

በመላው የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ጊዜያት በሰጠው ተስፋ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ወደ እርሱ ዘንድ የሚመጡት ሁሉ ክብርን እንደሚጎናጸፉ እርግጠኞች ሊሆኑ እንደሚገባ ገልጿል። በቲቶ 1፡2 ሐዋርያው ጳውሎስም እንደተናገረው፣ «የማይዋሸው አምላክ ይህን ሕይወት ሊሰጠን ከዘመናት በፊት ቃል ገባልን» ይላል። በዕብ. 11፡39-40ም ያለው ቃል የብሉይ ኪዳን የእምነት አርበኞች ከአዲስ ኪዳን አማኞች ጋር በአንድነት ሰማያዊት ከተማ የሆነችውን ፍጹማዊት ውርስን ይወርሳሉ ይላል። በዚህ ዓለም ውስጥ ምንም እንኳን ድሆች ብንሆንም፥ ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ምዕራፍ 2፡5 ላይ እግዚአብሔር የሚወዱትን የመንግሥቱ ወራሾች እንዲሆኑ የመረጣቸው መሆኑን ይናገራል። በሮሜ

8፡30 እግዚአብሔር አስቀድሞ የመረጣቸው እንዲሁም የጠራቸውና ያጸደቃቸው እንደሚከብሩ ይገልጻል። ጌታ ኢየሱስን እንደ መድኃኒታቸው አድርገው ያወቁት ሁሉ ከዚህ ሕይወት በኋላ የደኅንነትን የክብር በረከት ይቀበላሉ።

19ኛ ጥያቄ፦ እስቲ ለመጨረሻ ጊዜ ከሞት በኋላ ምን እንደሚደርስባችሁ የፈራችሁበትን ወቅት አስቡ። ከሆነ፥ የዛሬው ትምህርት በምን አኳኋን ሊያጽናናችሁ ይችላል?

ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ያመኑበትና ከእርሱም ጋር መታረቃቸው የተነገረላቸው ሁሉ፥ የዘላለምን ደኅንነት ክብር ያላንዳች ጥርጥር ያገኛሉ። እግዚአብሔር ከዚህ የተሻለ ምን ተስፋን ሊሰጥ ይችላል? ከሞት በኋላ ምን ይደርስብን ይሆን ብላችሁ ፍርሃት በሚሰማችሁ ጊዜ፥ ዛሬ ወደ ተማርነው ክፍል መለስ በማለት እግዚአብሔር የሰጣችሁን አስደናቂውን የደኅንነት ክብር በረከት ተስፋ አስቡ።

ክርስቶስን እንደ አዳኝ አምነው የተቀበሉትን እግዚአብሔር የማከበሩ ነገር፥ አማኞች ይህ ያገኙት ደኅንነት አስተማማኝ መሆኑ ብዙ ጥያቄዎችን አስከትሏል። ስለዚህ በዚህ ሳምንት ውስጥ በቀሪው ክፍለ ጊዜ የእነዚህ እውነተኛ አማኞች ዘላለማዊው ደኅንነት የተረጋገጠላቸው ስለ መሆኑና ስላለመሆኑ፥ እንዲሁም እነዚህ እውነተኞች አማኞች ለእግዚአብሔር ታማኞች በመሆን በዚሁ የሚቀጥሉ ስለ መሆናቸው እናጠናለን።

ሁለተኛ ቀን— የዘላለማዊ ዋስትና ማረጋገጫ እና የእግዚአብሔር ቅዱሳን ጽናት፥ ክፍል 1

በክርስቲያኖች መካከል የሚነሣ አንደኛው አስቸጋሪና አከራካሪ የሆነ ርእሰ ጉዳይ፥ እውነተኛና ዳግም የተወለዱ አማኞች ደኅንነታቸውን ይዘውት ይቆያሉ ወይስ ያገኙትን የሚያጡበት ሁኔታ ይኖራል? የሚለው ነው። ማንኛውም ክርስቲያን በአንድ ወቅት ክርስቶስን አምነው የተቀበሉና ኋላ ግን ይህን እምነታቸውን የተዉ ሰዎችን የሚያውቅ ይመስለኛል። አብዛኛዎቹ አማኞች አንድ ጊዜ መልካም የክርስትና አካሄድ የነበራቸውና ኋላ ላይ በኃጢአት ውስጥ ከመውደቃቸው የተነሣ ያንን የመልካም ሕይወት አኗኗርን የማይኖሩ ሰዎች ያውቃሉ። ከዚህ የሕይወት ገጠመኝ የተነሣ፤ ብዙ ሰዎች በአንድ ወቅት ድነው ይዘውት የነበረውን ሕይወት በሌላ ጊዜ ከኃጢአታቸው የተነሣ ወይም በክርስቶስ ማመናቸውን ስለሚያቆሙ፥ የተቀበሉትን ደኅንነት ያጣሉ የሚለውን አሳብ መቀበሉ ቀላል ነው። ነገር ግን በትናንትናው ትምህርታችን ላይ እንደተከታተልነው ሁሉ፥ ሌላውን የደኅንነቱን በረከቶች የሚቀበሉትን ሁሉ ክብርን እንደሚቀበሉ እግዚአብሔር ተስፋ ይሰጣል። ምንም እንኳን ደኅንነታቸውን ያጡ የሚመስሉ ሰዎችን የምናውቅ ብንሆንም፥ እኛ መደምደሚያ ልናደርገው የሚገባን መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን ትምህርት እንጂ የግል ተሞክሮአችንን ወይም ግንዛቤአችን ሊሆን አይገባም። አማኞች ስላላቸው ዋስትና ወይም መተማመኛ፥ እንደዚሁም የክርስትና ሕይወታቸውን በማራመድ ረገድ ስላላቸው ጽናትና

የመንፈስ ብርታት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያስተምረናል? ስለሆነም በሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ስለ እነዚህ ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጣቸውን መልሶች እንመረምራለን።

20ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 4፡22-25፤ 5፡1-2፥ 5፡8-10 አንብቡ። ሀ) ጽድቅ ለማን ተሰጠ? (ሮሜ 4፡22-25) ለ) በእምነት ከጸደቅን ምንን እናገኛለን? (ሮሜ 5፡1) ሐ) በእምነት ከጸደቅን ትርፋችን ምን ይሆናል (ሮሜ 5፡2)? መ) ለዘላለም ሕይወት ያለን ተስፋ በምን ምክንያት አያሳፍረንም? (ሮሜ 5፡5) ሠ) ከቁጥር 8-10 በተጻፈው መሠረት፥ ከእግዚአብሔር ቁጣ እንዴት እንደምንድንና የዘላለምን ሕይወት እንዴት እንደምናገኝ አብራራ?

---

1. አማኞች ለዘላለም ዋስትና አላቸው፥ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁ መሆናቸው ስለ ታወቀና ከእርሱም ጋር ሰላም ስላላቸው ነው።

ባለፈው ትምህርት 18 ላይ አስደናቂ ስለሆነው የጽድቅ ደኅንነት በረከት አጥንተን ነበር። በዚሁ ወቅት ሰዎች ክርስቶስን እንደ መድኃኒታቸው አምነው ሲቀበሉ፥ እግዚአብሔር ከበደላቸው ነፃ መሆናቸውን እንደሚያሳውቅ ተገንዝበናል። እግዚአብሔር እነዚህ ሰዎች ከእርሱ ጋር የታረቁ መሆናቸውን በይፋ ያሳውቃቸዋል። በኢየሱስ ባላቸው እምነት፥ እግዚአብሔር የኢየሱስን ጽድቅ ጽድቃቸው አድርጎ ይሰጣቸዋል። እግዚአብሔር ይህ በኢየሱስ ጽድቅ ላይ የተመሠረተ ጽድቅን የሚሰጣቸው ላለፈው ኃጢአታቸው ብቻ ሳይሆን፥ ለሠሩት ኃጢአት ሁሉ ነው። ሮሜ 5፡1-2 እግዚአብሔር አማኞች ከእርሱ ጋር ታርቀው ኅብረት መመሥረታቸውን ስለ ገለጠ፥ ከአሁን ወዲያ ከእርሱ ጋር ሰላም አላቸው ይላል። በእምነት ከእርሱ ጋር ለታረቁት፥ እግዚአብሔር በክርስቶስ መስቀል ላይ የተጠቀመበትን የማስታረቅ ተግባር እዚህም በሥራ ላይ ያውላል። ስለሆነም አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ሰላም፥ ለወደፊቱ ለሚያገኙት ዘላለማዊ ሕይወት ተስፋን ይሰጣቸዋል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ተስፋ» የሚለው ቃል አሳብ መተማመን ወይም ዋስትናን ያመለክታል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን እርቅ ቀደም ሲል የታወቀ በመሆኑ፥ ለዘላለም ዓለም እግዚአብሔር ባለበት እኛም እንደምንሆን ዋስትናው የተረጋገጠልን ነው።

ጳውሎስ በሮሜ 5፡8-10 ውስጥ፥ ጽድቅ ለዘላለማዊ ደኅንነታችን ማረጋገጫ እንደሚሰጠን ሰፋ አድርጎ በዝርዝር ይጽፋል። እኛ በእግዚአብሔር ላይ ያመጽን ኃጢአተኞች ሆነን ሳለን፥ እግዚአብሔር ጻድቃን አድርጎ እኛን በመቀበል ከእርሱ ጋር ሰላም እንዲኖረን ሲያደርግ፥ ይህን ተግባሩን ከፍጻሜ በማድረስ የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጠን እርግጠኞች ነን። በእነዚህ ሦስት ጥቅሶች ውስጥ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለት ሐረጎች ተጠቅሞ ክርስቶስ ስለሞተላቸው ሰዎች ገልጾአል። በቁጥር 8 ውስጥ ኃጢአተኞች ነበርን ይላል። እንዲህ ሲል እኛ ሕጉን ስላፈረስን ከመንገዱ ወጥተን የትም ስንቅበዘበዝ ነበርን ማለት ነው። ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛችን ምክንያት፥ ከእርሱ የምንጠብቀው ምንም መልካም ተግባር አልነበረም። በቁጥር 10፤

ሐዋርያው የእግዚአብሔር ጠላቶች እንደ ነበርን ይናገራል። እንዲህ ማለት በእግዚአብሔር ላይ በግልጽ በማመፃችን፥ በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል ጦርነት ነበር ማለት ነው። ያም ሆኖ፣ እኛ ደካሞች፥ ሕግ አፍራሾችና ጠላቶቹ ሳለን፥ ክርስቶስ ለእኛ ምን አደረገልን? ለእኛ ሲል ሞተ! ስለዚህ ድርጊት ጳውሎስ ሲጽፍ በመገረም ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ለሌላው ሕይወቱን አሳልፎ በመስጠት የመሞት ድርጊት ያልተለመደና ብርቅ ስለሆነ ነው። ለጠላቱ ሲልስ የሚሞት ማን ነው? ለበደለውስ ራሱን አሳልፎ ለሞት የሚሰጥ ኧረ ማን ነው! ነገር ግን እግዚአብሔር በእርሱ ለሚያምኑት ያደረገው ይህን ነው።

በቁጥር 9 እና 10 ውስጥ ጳውሎስ ነገሩን ሲያጠቃልል፥ «እግዚአብሔር ጠላቶቹ ለነበሩ ለኃጢአተኞች ያደረገውን ተመልከቱ» ይላል። ኢየሱስ ሞቶአል፥ የእርሱም ደም የኃጢአትን ቅጣት ከፍሎአል። እግዚአብሔርም በፊቱ ጻድቃን አድርጎ ተቀብሎአቸዋል። እንደዚሁም ከእነርሱ ጋር ሰላምን መሥርቷል። በዚህም ወዳጆቹ አድርጓቸዋል። ኢየሱስ አሁን ይህን ግንኙነት ጠብቆ ለዘላለም ይኖራል። እንግዲህ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ካደረገ፥ እነዚህ ኃጥአን የነበሩ ሁሉ፥ በፍርድ ቀን የእግዚአብሔር ቁጣ አይወርድባቸውም። ክርስቶስ በመጨረሻው ጊዜ ፍጹም የሆነ ደኅንነትንና የዘላለም ሕይወትን እንደሚሰጣቸው እርግጠኞች ነን። አንድ ክርስቲያን ደራሲ እነዚህን ጥቅሶች በሚከተለው ሁኔታ አጠቃሎአቸዋል፦ «እግዚአብሔር አስቸጋሪ የነበረውን ነገር አስቀድሞ ያደረገ ከሆነ፥ ማለትም የመጨረሻ ኃጢአተኞችን የሚያጸድቅ ከሆነ፥ አስቀድሞ በፊቱ ጻድቃን አድርጎ የተቀበላቸውን ከቁጣው እንደሚያድናቸውና እንደሚያጸድቃቸው ያላንዳች ጥርጥር ልናረጋግጥ እንችላለን።»

አንድ የተከሰሰ ሰው ፍርድ ቤት ውስጥ እንደ ቆመ ገምቱ። ከዚያም ዳኛው ይህን ችሎቱ ፊት ቆሞ ያለውን ሰው ከተከሰሰበት ወንጀል ነፃ መሆኑን በይፋ ያሳውቃል። እዚያው ችሎቱ ውስጥ የነበሩ ዘመድ ወዳጆቹ ይህን ሲሰሙ ብድግ ብለው ያቅፉትና ደስታቸውን ይገልጹለታል። ከዚያም ዳኛው ሰውዬውን አሁን ነፃ ስለሆንክ ልትሄድ ትችላለህ ይለዋል። ሰውዬውና ዘመድ ወዳጆቹ አብረውት ከፍርድ ቤቱ ወጥተው ይሄዳሉ። ነገር ግን በፍርድ ቤቱ በር ላይ ዘብ ቆሞአል። ታዲያ ይህ ነፃ የወጣው ሰው ዘቡን አልፎ መውጣት ይፈራልን? ዘቡ አቁሞ ይዞ ወደ እሥር ቤት እንደሚመልሰው ሰግቶ ይፈራ ይሆን? በፍጹም አይፈራም! ቀደም ሲል ዳኛው በደል እንደሌለበት የገለጸ ስለሆነ ምንም ጥርጥር አያድርበትም። ደግሞም ነፃ ስለሆነ በልበ ሙሉነት በበሩ ወጥቶ ወደፈለገው ሊሄድ ይችላል።

ለእኛ በክርስቶስ ላመንነው ዳኛው ከማንኛውም በደል ነፃ መሆናችንን አስታውቋል። ይህ መግለጫ በመጨረሻ ከተሰጠ በኋላ ከፍርድ ቤቱ ወጥተን ለመሄድ የሚያሠጋን ምንም ምክንያት አይኖርም። ሞትንም ሆነ ወይም የመጨረሻውን በእግዚአብሔር የሚሰጥ ፍርድ መፍራት አያስፈልገንም። ጽድቅ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖረን ያደርጋል። እግዚአብሔር

በመጨረሻው ጊዜ ለሚሰጠን የዘላለም ሕይወት የማረጋገጫ ዋስትና ይሆናል። ስለዚህ ደኅንነታችን የታመንና የተረጋገጠ ነው።

2. እግዚአብሔር ሁልጊዜ የጀመረውን ሥራ ስለሚፈጽም የአማኞች ሁኔታ ለዘላለም የተረጋገጠ ነው።

21ኛ ጥያቄ፡– ሮሜ 8፡30 አንብብ። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለመረጣቸው፥ ለጠራቸውና ላጸደቃቸው ምን ተዘጋጅቶላቸዋል?

22ኛ ጥያቄ፡– ፊልጵ. 1፡6 አንብብ። ጳውሎስ እርግጠኛ የሆነው ስለ ምንድን ነው?

በሮሜ 8 ውስጥ ጳውሎስ በሮሜ 5 ውስጥ የጀመረውን አሳብ ይቀጥላል። እግዚአብሔር ቀደም አድርጎ ከበደል ወይም ከወንጀል ነፃ መሆናችንን አሳውቆልናል። እግዚአብሔር የሚጀምረውን ሥራ ሁልጊዜ ከፍጻሜ ያደርሳል። በትምህርት 15 ላይ እንደ ተመለከትነው፥ የእግዚአብሔር የማዳን ተግባር የተጀመረው በራሱ ምርጫና ጥሪ ነው። ትናንትናም በሮሜ 8፡30 ውስጥ እንደ ተከታተልነው፥ ጳውሎስ ሲናገር፥ አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፥ የጠራቸውንም አጸደቃቸው ብሏል። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅን ያገኙ ሁሉ ክብርን አግኝተዋል። በእግዚአብሔር ዓይን፥ ዘላለማዊው የደኅንነታቸው ክብርም አሁኑኑ ተረጋግጧል! በእርግጥ ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ወደፊት እንድን ይሆንን ብለው ሊሠጉ አይገባም። እግዚአብሔር እንደሚለው፥ በጽድቅ አማካይነት በደላቸውን ሁሉ ይቅር ካላቸው፥ አስቀድሞ በሰማይ ክብርን አዘጋጅቶላቸዋል። እንደ እግዚአብሔር አደራረግ፥ ሥራውን ለጀመረላቸው ሁሉ የደኅንነት ተግባርን አስቀድሞ ጨርሶላቸዋል። ከእርሱ ጋር የታረቁ መሆናቸውን ካላወቀ፥ ዘላለማዊው ደኅንነታቸው ልክ አስቀድመው ዘላለማዊ ክብርን እንዳገኙ ያክል የተረጋገጠላቸው እውነታ ነው።

በእውነት ዳግም በተወለዱ ሰዎች ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ እንደሚፈጽም የሚያስተምረን ሌላው ጥቅስ ፊልጵ. 1፡6 ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ክርስቲያኖች ሲያበረታታቸው በሕይወታቸው ውስጥ የደኅንነት ሥራ የጀመረው አምላክ «እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን» የሚቀጥል መሆኑን ያረጋግጥላቸዋል። የኢየሱስ ክርስቶስ ቀን የሚባለው ክርስቶስ ወደ ምድር የሚመለስበት ቀን ነው። እንደዚሁም ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር እግዚአብሔር አንድ ጊዜ የደኅንነት ተግባሩን በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ መሥራት ሲጀምር፥ እስከ ዘላለም ዓለም መጀመሪያ ድረስ ዘልቆ ይፈጽማል ይላል። ስለዚህ ክርስቶስን እንደ አዳኝ ተቀብለው ወደ እርሱ ዘንድ የሚመጡ ዘላለማዊ ደኅንነታቸው ተረጋግጠላቸዋል።

3. አማኞች ለዘላለም ደኅንነታቸው ተረጋግጠላቸዋል፥ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ የተቀበሉ ስለሆኑና በእርሱም የታተሙ በመሆናቸው ነው።

23ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 8፡16 -17 አንብብ። ሀ) መንፈስ ቅዱስ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ምንን ይመሰክራል? (ቁጥር 16) ለ) ከማን ጋር ወራሾች እንሆናለን? (ቁጥር 17) ሐ) ወራሾች መሆናችን ምንን ያረጋግጥልናል? (ቁጥር 17)

24ኛ ጥያቄ፡- ኤፌ. 1፡13-14 አንብብ። ሀ) በአመንን ጊዜ በምን ታተምን? ለ) እንደ ቁጥር 14 መንፈስ ቅዱስ ምን ያደርግልናል?

25ኛ ጥያቄ፡- ኤፌ. 4፡30 አንብብ። መንፈስ ቅዱስ ለምን ሲል አተመን?

በሮሜ 5፡5 ላይ እንደ ተገነዘብነው፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ስለ ሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ሕይወትን የመውረሱ ተስፋ አያሳፍረንም። እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወትን እንደሚሰጠን በእውነት ተስፋን ሰጥቶናል። ለዚህም አስቀድሞ መንፈስ ቅዱስን አፍስሶብናልና ነው። እያንዳንዱ እውነተኛ አማኝ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎአል። የዚህ መንፈስ በልባችን ማደር እግዚአብሔር ሥራውን የሚፈጽም ስለመሆኑ ማረጋገጫ ነው።

በሮሜ 8 ውስጥ ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ መኖር እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወትን እንደሚሰጠን ማረጋገጫ ነው ይላል። ስለዚህ አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ሰጦታ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ (ሮሜ 8፡9)፤ በእኛ ውስጥ ያለው መንፈስ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር እውነተኞች የእግዚአብሔር ልጅነታችንን ይመሰክራል። ክርስቶስን አምናችሁ እንደ አዳኛችሁ ከተቀበላችሁ፤ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በውስጣችሁ ያድራል፤ የእርሱ በእናንተ ውስጥ አድሮ በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችሁን ያሳስባችኋል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን፥ የሰማዩን የክብር ውርስ ተካፋዮች ነን። በትምህርት 17 ውስጥ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ስላለን፥ የውርሱ ተከፋዮች መሆናችንን አስተውለናል። እንደዚሁም በውስጣችን የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ፥ በደኅንነታችን ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ስላለን፥ የክርስቶስ ዘላለማዊ ክብር ውርስ ተካፋዮች እንደምንሆን ያረጋግጥልናል።

መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን በመኖሩ ዘላለማዊውን ደኅንነታችንን ያረጋግጥልናል፥ ደግሞም የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንንም ይመሰክርልናል። ይህ በውስጣችን የሚኖር መንፈስ፥ ማኅተማችንና የመጪው ደኅንነታችን ዋስትናም ነው። ኤፌ. 1፡13 -14 እና 4፡30 ይህንን የመንፈስ ቅዱስ በረከትን ሁኔታ ይገልጻል። እንዲሁም በኤፌ. 1፡13 ውስጥ ጳውሎስ ሲናገር፥ ማንም ሰው በክርስቶስ እንዳመነ ወዲያውኑ በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ይታተማል ይላል። በአዲስ ኪዳን ዘመን፥ እኛ ዛሬ እንደምናደርገው ደብዳቤ በፖስታ ውስጥ ታሽጎ አይላክም ነበር። ደብዳቤ ለመላክ የሚፈልገው ሰው ከጻፈ በኋላ ያንን ይጠቀልልና በትኩስ ሰም ያሽገዋል። በዚህ ትኩስ ሰም ላይ ማኅተሙን በመጫን የላኪው ሰው ማኅተም ይታተምበታል። ማኅተሙ ሁለት ዓላማዎች ነበሩት። አንደኛው፥ ደብዳቤው ለተላከለት ሰው እስኪደርሰው ድረስ እንዳይከፈት ይጠብቀዋል። ሁለተኛው፥ ማኅተሙ ደብዳቤው ከማን እንደ ተላከ ያመለክት ነበር። ጳውሎስም መንፈስ ቅዱስ ይህንን መሰል ተግባር በአማኞች ላይ እንዳለው

ነው የገለጸው። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር በሚሰጠን ደኅንነት ውስጥ እንድንኖር ያደርጋል፥ ቀጥሎም እኛ የእግዚአብሔር መሆናችንን ያመለክታል። ኤፌ. 4፡30ም ይህንኑ የማኅተም ሁኔታ በመድገም፥ የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም «ለቤዛ ቀን» እንደሚሆነን ይነግረናል። የቤዛ ወይም የደኅንነት ቀን እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር ፊት የምንቆምበትና ወደ መጨረሻው የዘላለም ሕይወት የምንገባበት ቀን ነው። መንፈስ ቅዱስ እውነተኛና ዳግም የተወለደ አማኝን ጠብቆ ለዚያ ቀን ያበቃዋል። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ ጠብቆና ማንነታችንን ለይቶ ለዚያ ጊዜ የሚያደርሰን ብቻ ሳይሆን፥ ዋስትናችንም ነው። ኤፌ. 1፡14 መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ዘንድ መኖሩ፥ ለውርሳችን የመያዣ ዋስትናችን ነው ይላል። አንድ ሰው ለአንድ ነጋዴ ቀብዱን ከፍሎ ኋላ በመመለስ ቀሪውን ዋጋ እንደሚከፍል እንደሚያረጋግጥለት ሁሉ፥ እግዚአብሔር ደኅንነታችንን እንደሚያሟላ ዋስትናችን መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ የዘላለማዊ ደኅንነታችን ቀዳሚ ክፍል ነው። አሁን የተቀበልነው በመሆናችን፥ ቀሪውን የዘላለም ደኅንነታችንን እንደምናገኝ በዚህ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

4. አማኞች የዘላለም ዋስትና አላቸው፥ ምክንያቱም ኢየሱስ ራሱ ስለሚጠብቃቸውና ስለሚንከባከባቸው ነው።

26ኛ ጥያቄ፡– ዮሐ. 6፡37–40 አንብብ። ሀ) ኢየሱስ፥ አብ ለሰጠውና ወደ እርሱም ዘንድ ለሚመጡት ምን ያደርጋል? (ቁጥር 37) ለ) እግዚአብሔር ከኢየሱስ የሚፈልገው ወይም የሚጠባበቀው ነገር ምንድን ነው? (ቁጥር 39) ሐ) ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ምንን ይሰጣል?

27ኛ ጥያቄ፡– ዮሐ. 10፡28–29 አንብብ። የኢየሱስን በጎች ከእጁ ችሎ የሚነጥቀው ማን ነው?

በዮሐንስ ወንጌል በሁለት ክፍሎች ውስጥ፥ ኢየሱስ አማኞችን ስለሚጠብቃቸው ለዘላለም ምንም ሊነካቸው እንደማይችል ተስፋ ይሰጣቸዋል። በዮሐ. 6፡37 ውስጥ ኢየሱስ አብ የሰጠው ሁሉ ወደ እርሱ እንደሚመጡና እርሱም እንደማያባርራቸው ይናገራል። ስለዚህ ወደ ጌታ ኢየሱስ ዘንድ የሚመጣና በእርሱ የሚያምን ማንም ሰው አይጠፋም። ምክንያቱም በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ከሞት አስነሥቶ የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶላቸዋልና ነው። እንደዚሁም በዮሐንስ ምዕራፍ 10 ውስጥ ኢየሱስ በጎቹን የሚጠብቅና የሚከላከል ቸር እረኛ እርሱ መሆኑን በግልጽ ያስረዳል። ስለዚህ ይህ የእርሱ የጥበቃ ዋስትና ማንም ከእርሱ እጅ ሊነጥቃቸው እንደማይችል የማረጋገጫው ቃል ነው። በእርግጥም የእርሱ እውነተኛ በጎች የሆኑት ሊጠፉ ከቶ አይችሉም።

5. አማኞች ለዘላለም የተጠበቁ ናቸው። ምክንያቱም ከክርስቶስ ጋር ሞተው ሕያዋን ሆነው የተነሡ ስለሆኑ ነው።

28ኛ ጥያቄ፡– ኤፌ. 2፡4–6 አንብብ። እግዚአብሔር ምን ሦስት ነገሮችን አደረገልን?

29ኛ ጥያቄ፡– ሮሜ 6፡3–6 አንብብ። ከኢየሱስ ጋር አንድ ለመሆን የተጠመቁ ሁሉ ምን ይሆናሉ?

30ኛ ጥያቄ፡– 2ኛ ቆሮ. 5፡17 አንብብ። ከክርስቶስ ጋር የተባበሩ ምን ይሆናሉ?

በ17ኛው ትምህርታችን ውስጥ ዳግም በመወለዳችንና ከክርስቶስ ጋር ስላለን ኅብረት ስለምናገኘው የደኅንነት በረከቶች ተምረናል። በትምህርታችንም ወቅት አንድ ሰው በእምነት ክርስቶስን እንደ አዳኙ በሚቀበልበት ጊዜ፥ በሞቱና በትንሣኤው ከክርስቶስ ጋር እንደሚተባበር አስተውለናል። ቀድሞ የነበረበት አሮጌው ሰውነት ይሞታል። አዲሱ ሰው ሕያው ይሆንና ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ይኖራል (ኤፌ. 2፡4–6)። ይህ እግዚአብሔር ለአማኞች የሚሰጣቸው አዲስ ሕይወት መንፈሳዊ ሕይወት ነው። እነዚህ አማኞች የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ለመሆን ከላይ ተወልደዋል። ክርስቶስን አምነን እንደ አዳኛችን በምንቀበልበት ጊዜ፥ የነበርንበት አሮጌው ሰውነት ይሞትና አዲሱ ሰውነት ሕይወት ይወርሳል። በሮሜ መልእክት ምዕራፍ 6 እንደሚለው፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ለመሆን የተጠመቅን ሁላችን ከኢየሱስ ጋር ሞተን ተቀብረናል ይላል። በ20ኛ ክፍለ ትምህርታችን ውስጥ እንደምንመለከተው፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሰዎች ክርስቶስን አምነው መቀበላቸውን በሕዝቡ ፊት ወዲያው እንዳሳወቁ ይጠመቁ ነበር። ይህ የጥምቀታቸው ወቅት፥ የመለወጣቸው ጊዜ ሆኖ ተቀባይነትን አግኝቶ ነበር። ስለዚህ አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ፥ ከክርስቶስ ጋር ይሞታል፥ ከክርስቶስም ጋር ይቀበራል፥ ከክርስቶስም ጋር ለአዲስ ሕይወት ይነሣል። በእውነተኛው ሁኔታ ዳግም የተወለዱ ሰዎች የአዲስ ሕይወትን ስጦታ ብቻ አያገኙም፥ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸው አዲስ ሰዎችም ይሆናሉ እንጂ! 2ኛ ቆሮ. 5፡17 ውስጥ የነበሩበት አሮጌው ሰውነት አልፎአል፥ ስለዚህ አሁን አዲስ ሰዎች ሆነው ዳግም ተወልደዋል ይላል። እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር አስነሥቶን እንደ አዲስ ፍጥረት ካደረገን፥ እንዴት አሳቡ ይለወጣል? እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ ከላይ ዳግም አዲስ ሕይወትን የሰጠን ሥራውን ይለውጣል? አንድ ሰው «ላለመወለድ» ይችላል? ደግሞስ አንድ ፍጥረት «ላይፈጠር» ይችላል? እግዚአብሔር ለእኛ አዲስ ሕይወትን በመስጠት አዲስ ሰዎች የማድረጉ ሁኔታ የሚያረጋግጥልን፥ እግዚአብሔር በሕይወት ዘመናችን ውስጥ የማዳን ተግባሩን የሚፈጽም መሆኑን ነው።

በዛሬው ትምህርታችን ውስጥ እግዚአብሔር ያዳናቸው ሰዎች የደኅንነታቸው ሁኔታ እግዚአብሔር ወዳለበት እስከሚገቡበት ጊዜ ድረስ ተጠብቆ የሚቆይ የመሆኑን አምስት ምክንያቶች አጥንተናል። በነገው ትምህርታችን ደግሞ አማኞች በምን ምክንያት ለዘላለም የተጠበቁ እንደሚሆኑ፥ እንዲሁም በሮሜ ምዕራፍ 8 ውስጥ አማኞች ስለሚኖራቸው ጥበቃና ዋስትና ጠቅለል ባለ ይዘት መልካም ትምህርት እንቀስማለን።

ሦስተኛ ቀን– የዘላለማዊ ዋስትና ማረጋገጫና የእግዚአብሔር ቅዱሳን ጽናት፥ ክፍል 2

በትናቱ ዕለት ትምህርታችን ስለ አማኞች ዘላለማዊ ዋስትና መረጋገጥ ወይም ጥበቃ ማጥናት ጀምረናል። በዚህ ትምህርት ላይም፥ አማኞች በደኅንነታቸው ረገድ ሁኔታው ዋስትና እንዳለውና የተጠበቀላቸው መሆኑን ተመልክተናል። ይህ ሊሆን የቻለበትም ምክንያት፥ ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቃቸውና ሰላምንም በመመሥረታቸው ምክንያትና እንደዚሁም እግዚአብሔር ሁልጊዜ የጀመረውን ሥራ ስለሚፈጽም ነው። ከዚህም ጋር መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ በመሆናቸውና ኢየሱስ ራሱ ስለሚጠብቃቸው፥ ከዚህም የተነሣ አዲስ ሰዎች ስለሆኑ ነው። ዛሬ ደግሞ አማኞች በተጨማሪም ለዘላለም የተጠበቁ የሆኑበት ምክንያት እያንዳንዳቸው የክርስቶስ አካል ክፍሎች ስለሆኑና ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ ኢየሱስ ስለሚማልድላቸውም እንደሆነ እናጠናለን። እንዲሁም በሮሜ ምዕራፍ 8 ውስጥ ስለ አማኞች ዘላለማዊ ዋስትና መጠበቅ ጠቃሚ የሆነ አጠቃላይ ትምህርትን በመከታተል፥ አማኞች ስለ ዘላለማዊ ዋስትናቸው መጠበቅ ስለሚኖራቸው ስሜት እናስተውላለን።

6. አማኞች ዘላለማዊ ዋስትናቸው የተጠበቀ ነው፥ ምክንያቱም እያንዳንዳቸው የክርስቶስ አካል ክፍሎች ስለሆኑ ነው።

31ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮ. 12፡27 አንብብ። እያንዳንዱ አማኝ ምን ይሆናል?

በ17ኛው ትምህርት ውስጥ እንደ ተመለከትነው፥ በክርስቶስ በማመን መድኃኒቱ አድርጎ የተቀበለው ሁሉ፥ የክርስቶስ የአካሉ ክፍል እንደሚሆን አስተውለናል። 1ኛ ቆሮ. 12፡27 እንደሚያስገነዝበው፥ እያንዳንዱ አማኝ የአካሉ ክፍል እንደሆነና እያንዳንዶቹ አማኞችም በመሰባሰብ የክርስቶስ አካል እንደሚሆኑ ይናገራል። ስለዚህ በዚህ ምድር ላይ ስላለን ሁላችን በአንድነት የክርስቶስ አካል በመሆን፥ እርሱን ለዓለም በጉልህ ማሳየት ይገባናል። አማኞች በእውነተኛው አኳኋን ደኅንነታቸው የተረጋገጠላቸው ካልሆነ በስተቀር፥ የክርስቶስ አካል አንድ መሆኑ ቀርቶ ይከፋፈላሉ። ግን አንድ ሰው በክርስቶስ ካመነና ለዘላለሙም የአካሉ ክፍል ከሆነ፥ ደኅንነቱም ለዘላለም ዋስትና ያለውና የተጠበቀ ይሆናል።

7. አማኞች ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ፥ ኢየሱስ ስለሚማልድላቸው፥ ለዘላለም ዋስትናቸው የተጠበቀ ነው።

32ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 8፡34 አንብብ። ኢየሱስ አሁኑኑ ስለ እኛ ምን እያደረገ ነው?

33ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ዮሐ. 2፡1-2 አንብብ። ሀ) አማኞች ኃጢአት በሚያደርጉበት ጊዜ ስለ እነርሱ ሆኖ የሚናገር ማን ነው? ለ) ምልጃቸው በምን ምክንያት ውጤታማ ሊሆን ቻለ?

34ኛ ጥያቄ፡- ዕብ. 7፡24-25 አንብብ። ኢየሱስ ስለ እኛ የሚያደርገው ጸሎት ውጤት ምንድን ነው?

ብዙ ክርስቲያኖች ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ደኅንነት የሚቀማቸው እየመሰላቸው ይሸበራሉ። ነገር ግን በትናንትናው

ትምህርታችን ውስጥ በሮሜ 8፡34 እንደ ተመለከትነው፥ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ሆኖ ስለ እኛ እንደሚማልድ ተገንዝበናል። በ1ኛ ዮሐ. 2፡1 እኛ ኃጢአት በምናደርግበት ጊዜ ኢየሱስ ስለ እኛ እንደሚማልድ በግልጽ ይነግረናል። ኢየሱስ ስለ እኛ የሚያቀርበው ምልጃ ውጤታማ እንደሚሆን እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን፥ ምክንያቱም እርሱ ራሱ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚመልስ መሥዋዕት ስለሆነ ነው። የኃጢአታችንን ቅጣት የከፈለልንና በእግዚአብሔር ቁጣ ምክንያት ስለ ኃጢአታችን የተሠቃየው እርሱ አሁንም ኃጢአት በምንሠራበት ጊዜ ይማልድልናል። ዕብራውያን 7፡24–25 ያለው ክፍል ክርስቶስ ባለማቋረጥ ስለ እኛ የሚያደርገው ምልጃ ፍጹም የሆነ ደኅንነት እንደምናገኝ ያረጋግጥልናል። በትምህርት 12 ውስጥ እንደተመለከትነው፥ እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል። በነገው ትምህርትም እንደምናጠናው የክርስቲያኖች ኃጢአት ሁልጊዜ የከፋ ውጤት ይኖረዋል። ነገር ግን ኃጢአት በምንሠራበት ጊዜ፥ ኢየሱስ ይማልድልናል። አማኞች ደኅንነታቸውን የሚያጡበት ጊዜ ቢኖር፥ የኢየሱስ ጸሎት በማይመለስበት ጊዜ ነው። በእርግጥ ደግሞ የኢየሱስ ጸሎት ሁልጊዜ ይመለሳል። ኢየሱስ ሁልጊዜ የሚማልድላቸው በመሆኑ፥ አማኞች ደኅንነትን በማግኘታቸው ረገድ እርግጠኞች መሆናቸውን ሊገነዘቡ ይገባል።

8. ጠቃሚ የሆነ ማጠቃለያ፡– ሮሜ 8፡31–39

35ኛ ጥያቄ፡– ሮሜ 8፡31–39 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ልጁን ለእኛ የሰጠ ስለሆነ፥ ከልጁ ጋር ምንን እንደሚሰጠን እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን? (ቁጥር 32) ለ) ሐዋርያው ጳውሎስ በቁጥር 33፡34ና 35 ውስጥ ለጠየቃቸው ጥያቄዎች ውስጠ ታዋቂ ሆኖ የቀረበው መልስ ምንድን ነው? ሐ) እንደ ቁጥር 38ና 39፥ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን የሚችል ምንድን ነው?

በሮሜ 8፡31 –39 የቀረበው ቃል፥ ጳውሎስ ከሮሜ ምዕራፍ 5–8 ያቀረበው ትምህርት ማጠቃለያ ወይም የተሰባሰበ አሳብ ሲሆን፥ አሳቡም ስለ አማኞች የደኅንነት ዋስትና መረጋገጥ የሚናገር ነው። በሮሜ 8፡31–32 ውስጥ የማጠቃለያ አሳቡን በሚጀምርበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር እስከ ዛሬ ያደረገልን ተግባር፥ ያጸድቀናል፥ መንፈስ ቅዱስን ይሰጠናል፥ ያስታርቀናል፥ የጀመረውን ሥራ ይፈጽምልናል፥ ደግሞም የዘላለም ሕይወትን ይሰጠናል በግለት ያረጋግጥልናል። ከዚያም በቁጥር 33–35 ውስጥ ጳውሎስ አማኞች ለዘላለም የጸኑ መሆናቸውን ለመግለጽ፥ ሦስት ጥያቄዎችን ይጠይቃል። በመጀመሪያም፥ የሚያቀርበው ጥያቄ፥ «በእግዚአብሔር ፊት በድፍረት ቆሞ አማኞችን በደለኞች ናቸው ብሎ በመክሰስ፥ በኃጢአታቸው ምክንያት መሠቃየት ይገባቸዋል የሚል ይኖር ይሆን?» የሚል ሲሆን፥ መልሱም፥ «በእግዚአብሔር ፊት በድፍረት ቆሞ አማኞችን የሚከስስ ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ «በደለኞች አይደሉም»፣ በኢየሱስ ደም ምክንያት «ጻድቃን» ናቸው ሲል አስታውቋልና ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር አስቀድሞ «በደለኞች አይደሉም» ስላለ፥ በክርስቶስ አማኞች የሆኑትን ሁሉ ተላክቶለት ሊከስስ የሚችል ክቶ አይኖርም።

በሁለተኛ ደረጃ ጳውሎስ በሚያቀርበው ጥያቄ፥ አማኞች በኃጢአታቸው ምክንያት እንዲቀጡ ማን ሊኮንናቸው ይችላል? የሚል ነው። ለጥያቄውም መልስ ለመስጠት ሲል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ለአማኞች ኃጢአት ቅጣት አጸፋውን የከፈለ በመሆኑ፥ ፈራጅ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ እንደሚማልድላቸው ያስታውሰናል። ሰይጣን አማኞችን በእግዚአብሔር ፊት በሚከስስበት ጊዜ፥ በአማኞች ፈንታ ለመናገር ጌታ ኢየሱስ በእዚያ ነው። እርሱም ሲናገር፥ «አዎን! ይህ ሰው ሊኮነን የሚገባው ኃጢአተኛ ነው። ነገር ግን እኔ ስለ እርሱ ኩነኔ ሥቃይን ተቀብያለሁ። ስለ ኃጢአቱም ይከፍለው የነበረውን ቅጣትም ከፍየለታለሁ። ስለዚህ የሚኮነንበት ምንም ምክንያት አይኖርም» በማለት ይመልሳል። በትምህርት 17 ውስጥ በሮሜ 8፥1 እንደተመለከትነው፥ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ያላቸው ሁሉ አይኮነኑም። ጳውሎስ ደግሞም ሲናገር፥ ከክርስቶስ ጋር የተባበርን እንደ መሆናችንና ኢየሱስም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ስለ እኛ ስለሚማልድ፥ ኩነኔ ጨርሶ ሊኖርብን አይችልም ይላል።

ሦስተኛው ጳውሎስ የሚያቀርበው ጥያቄ አማኞችን ማንኛውም ነገር ቢሆን፥ ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለያቸውና የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ውርስ የሚያሳጣቸው እንደሌለ ነው። በተለይም እርሱን የሚያሳስበው በአማኞች ሕይወት ውስጥ ስለሚከሰተው የሥቃይ ሁኔታ ነው። በአማኞች ሕይወት ውስጥ ሥቃይ አለ ማለት፥ የአማኞች ሕይወት ከእግዚአብሔር ፍቅር ይለያል ማለት ነውን? እንደዚሁም አማኞች በስደት፥ በረሃብ፥ በድኅነትና በጦርነት ምክንያት ሥቃይን ቢቀበሉ፥ ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍቅር ለይቶ ዘላለማዊ ውርሳቸውን ያሳጣቸዋል ማለት ነውን? አይደለም! ጳውሎስ መዝሙር 44፥22ን በመጥቀስ፥ የእግዚአብሔር ተከታዮች ለሆኑት ሁሉ ሥቃይን መቀበል የተለመደ ክስተት በመሆኑ እንደ ቁጣ ሊታይ አይገባም ይላል። በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ሁልጊዜ እንደሚታረዱ በጎች ይቆጠራሉ። ምንም እንኳን አማኞች ሥቃይን የሚቀበሉ ቢሆኑም፥ በመጨረሻው ቀን ድልን እንደሚቀዳጁና ዘላለማዊ ውርስን እንደሚያገኙ የተረጋገጠላቸው ሐቅ ነው (ቁጥር 37)።

በመጨረሻውም ላይ፥ በቁጥር 38 እና 39 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ታይቶ ያልታወቀና አሁን የታየ እንግዳ ነገርም ቢሆን፥ አማኞችን ከእግዚአብሔር ፍቅር ፈጽሞ ሊለያቸው እንደማይችል በማረጋገጥ ነገሩን ይቋጫል። በዚህ ማጠቃለያ አሳቡም ላይ አማኞችን ከእግዚአብሔር ፍቅር ለመለየት የሚሞክሩ ጠላቶችን በዝርዝር ይገልጻል። እነዚህም፥ ዲያቢሎስ፥ ሞት፥ ወደፊት የሚሆነው ነገር ጥርጣሬና የመሳሰሉትን አደናቃፊዎች ከዘረዘረ በኋላ፥ ምንም ልንፈራው የሚገባን ነገር ከቶ ሊኖር እንደማይችል በማበረታታት ነገሩን ይደመድማል። የትኞቹም ዓይነት ጠላቶቻችን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለዩን አይችሉም።

36ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ከእግዚአብሔር ሊለየን ይሆናል ብላችሁ አንዳንዴ የምትፈሩት ነገር ምንድን ነው? ለ) ይህ የተመለከታችሁት ክፍል እንዴት ሊያጽናናችሁና አለኝታ ሊሆናችሁ ይችላል?

ሁሉም አማኞች ቢሆኑ በሕይወታቸው ውስጥ ጥርጣሬ የሚያጋጥማቸው ወቅት አለ። ይህም ሊከሰት የሚችለው ስለ መዳናቸው ተጠራጥረው ፍርሃት በሚሰማቸው ጊዜ ነው። ይህ የጥርጣሬ ስሜትም ወደ አእምሮአችን የሚገባው በሰይጣን አማካይነት ነው። ሰይጣን ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ስለ እርሱ እንክብካቤ እንድንጠራጠር ይፈልጋል። ስለ ዘላለማዊ ደኅንነታችንም ጥርጣሬ እንዲገባን ያደርጋል። ከዚያም ያለፈው ኃጢአታችን ፊታችን ተደቅኖ እንዲታወሰንና ጨርሶ ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ብቃት የሌለን አድርጎ ያሳየናል። እኛም ምንኛ ኃጢአተኞች መሆናችንን በምናስታውስበት ጊዜ፥ ስለ ደኅንነታችን መጠራጠር እንጀምራለን። እንደዚሁም ሰይጣን የአጋንንቱን ኃይል አጉልቶ ሊያስታውሰን ይሻል። ከዚህም የተነሣ ስለ ሞትና ወደፊት ስለሚሆነው ሁሉ እንድንጠራጠር ያደርጋል። «ምን ሊሆን እንደሚችል የምታውቀው ምን ነገር አለ?» በማለት ይጠይቃል። ይቀጥልና፥ «ወደፊት ስለሚሆነው ነገር፥ ስለ ሞትና መቃብር መፍራት አለብህ፥ እንዲሁም የማንኛውንም አጋንንቶቼን ኃይልና አቅም መፍራት አለብህ» ይላል። ነገር ግን እግዚአብሔር በተስፋው ቃል እንዳረጋገጠው፥ በክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ ኃጢአታቸውንና በደላቸውን ይቅር ብሎአቸዋል። እርግጥ ነው፥ እኛ የእግዚአብሔር ደኅንነት የማይገባን ኃጢአተኞች ነን። በዚህ በኃጢአታችን ሁኔታና በክፋታችን ውስጥ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት መቆም አንችልም። ነገር ግን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ ለብሰን በእግዚአብሔር ፊት ልንቆም እንችላለን። ሮሜ ምዕራፍ 8 እንደሚያሳስበን ከሆነ፥ ጌታ ኢየሱስ አስቀድሞ ከፈጸመልን ተግባር የተነሣ የዘላለም ደኅንነታችን ሁኔታ ዋስትና ያለውና የተረጋገጠ መሆኑ ነው።

አማኞች ለዘላለም ስለተረጋገጠላቸው ደኅንነት ያላቸው አመለካከት እንዴት ነው?

አንዳንድ ሰዎች፥ አማኞች ያላቸው ደኅንነት ለዘላለም የተረጋገጠ ነው የሚለውን ትምህርት በሚሰሙበት ጊዜ ይጠራጠሩና አሳቡ ሰዎችን የበለጠ ኃጢአት እንዲሠሩ ይገፋፋቸዋል በማለት ይፈራሉ። እንዲያውም ሰዎች «በምንም ሁኔታ ደኅንነቴን አላጣውም፥ ስለዚህ ሄጀ እንዳሻኝ ኃጢአት ልሥራ፥ ወደ ሰማይ የምገባ መሆኔ አሁንም ተረጋግጦልኛል» ብለው ያሰባሉ ሲሉ ያምናሉ። ነገር ግን አዲስ ኪዳን በግልጽ እንደሚናገረው፥ *ያገኘውን ደኅንነቱን የሚያጣ መሆኑ ሳይሰማው በድፍረት ወደ ኃጢአት ተመልሶ የሚገባ ሰው፥ ዳግም የተወለደ እውነተኛ አማኝ አይደለም።* አዲስ ኪዳን እንደሚያስተምረን እውነተኛ የሆኑ አማኞች እግዚአብሔርን ለማስደሰትና ለእርሱም ለመታዘዝ ይፈጥናሉ እንጂ፥ በሰሜት ተነሣሥተው ኃጢአትን ለመሥራት አይጣደፉም።

37ኛ ጥያቄ፡– ቲቶ 2፡11–13 አንብብ። የእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ምን ያስተምረናል? የተጋላ መልስ ስጡ። መልሳችሁም ልናደርገው ስለሚገባንና ስለማይገባን ነገር የያዘ መሆን አለበት።

38ኛ ጥያቄ፡– ሮሜ 6፡1–2 እና 15–18 አንብብ። አማኞች በእግዚአብሔር ጸጋ ሥር በመሆናቸው ኃጢአት ሊሠሩ የማይገባው በምን ምክንያት ነው?

በ16ኛው ትምህርታችን ውስጥ፥ ሰዎች የዳኑት በንስሐ፥ በእምነትና በመለወጥ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ እንጂ፥ በመልካም ሥራቸው እንዳልነበረ ተመልክተናል። ሆኖም፣ አሁንም ቢሆን መልካም ሥራ በአማኞች ሕይወት ውስጥ በጣም ጠቃሚ ሆኖ ይገኛል። መልካም ሥራና ታዛዥነት፥ አዳኝ የሆነ እምነትና ክርስቶስን የሚከተል ደቀ መዝሙር እውነተኛ ፍሬ ምስክር ነው። መልካም ሥራና ታዛዥነት የደኅንነት ውጤቶች ናቸው። እውነተኛና ዳግም በክርስቶስ የተወለዱ አማኞች እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘትና ለእርሱም መታዘዝን ይወዳሉ። እንደዚሁም በእውነት ዳግም በክርስቶስ የተወለዱ አማኞች ከኃጢአት ተመልሰው፥ ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ጸጋ ያድጋሉ። ቲቶ 2፡11–13 ያለው ክፍል የእግዚአብሔር ጸጋ የተቀበሉትን የሥጋ ምኞትና ኃጢአተኝነትን እንዲክዱ ያስተምራቸዋል ይላል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ በሚቀበሉበት ጊዜ፥ «አሁን ለዘላለም የዳንሁ በመሆኔ፥ የፈለግኩትን ያህል ኃጢአት ልሠራ እችላለሁ» በማለት ማሰብ አይጀምሩም። ከዚህ ይልቅ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያስተምራቸውን ማድመጥ ይጀምራሉ። ይህም ድምፅ «ኃጢአትና የሥጋ ምኞት ለእናንተ አይጠቅሙአችሁም፥ ስለዚህ ያጠፉአችኋል። አሁኑኑ ካዱዋቸው» ይላቸዋል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ በሚቀበሉበት ጊዜ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ድምፅ እንዲህ ሲል የሚያስተምራቸውን ድምፁን ያዳምጣሉ። ይህ ድምፅም፥ «እግዚአብሔርን በማወቅና እርሱን በማስደሰት በሕይወትህ ውስጥ የምታሳልፈው ጊዜ ትልቁ ጊዜ ነው። ስለዚህ ራስህን በመቆጣጠር፥ በጽድቅና እርሱን በመፍራት ጊዜህን በቁም ነገር ላይ ብታውል፥ እግዚአብሔርን ለማወቅና እርሱን ለማስደሰት ትችላለህ በማለት ያሳስባል። አማኞች እግዚአብሔርን የማስደሰትና እርሱንም የመታዘዝ ፍላጎት ያድርባቸዋል። በክርስቶስ በእውነት የሚያምኑና በእውነት ዳግም የተወለዱ አማኞች ቀድሞ የነበሩበትን ሕይወት እንዲለውጡ በእግዚአብሔር ጸጋ ይቀሰቀሳሉ።

ጳውሎስ በሮሜ 6 ውስጥ ይህንኑ የመሰለ ትምህርት ያቀርብልናል። አንዳንድ ሰዎች፥ ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ያስተላለፈው ትምህርት፥ ሰዎችን ወደ ኃጢአት ይመራቸዋል ይላሉ። ጳውሎስ ይህንን ለመሰለ የሐሰት ክስ ለሚያቀርቡ ሰዎች ሲመልስ፥ «የእግዚአብሔር ጸጋ በዝቶልን ኃጢአታችንን በመሸፈኑ ምክንያት (ሮሜ 5፡20)፥ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? በምንም ዓይነት ይህ ሊሆን አይገባም» በማለት ይናገራል። ጳውሎስ የሰጠው መልስ በግሪክኛው ቋንቋ አገላለጽ ጠንከር ያለ ስሜት አለው። የእግዚአብሔር አዳኝ የሆነው ጸጋ ወደ ኃጢአት ሰዎች እንዲያመሩ ያበረታታል የሚለውን የሐሰት ክስ ሐዋርያው በኃይል ይቃወማል። የእግዚአብሔርን ጸጋ የተቀበሉ ሰዎች አሮጌው ሕይወታቸው የሞተ መሆኑን አበክረው ሊገነዘቡት ይገባል ይላል። ለእነርሱ እግዚአብሔር አዲስ ሕይወትን ሰጥቷቸዋል። እንዴት አድርገው ወደ አለፈው አሮጌ ሕይወት ለመመለስ ያስባሉ? በአሮጌው ሕይወታቸው ጊዜ የኃጢአት ባሮች ነበሩ ይላል ጳውሎስ በሮሜ 6፡15–18 ባለው ክፍል። አሁን ግን ከኃጢአትና ከሞት ነፃ ስለሆኑ የጽድቅ ሕይወትን ሊኖሩ ይችላሉ። በእውነት ይህን እግዚአብሔር በጸጋው

የሚሰጠውን ሕይወት የተቀበሉ ሁሉ ጽድቅን ማገልገል እንጂ ለኃጢአት መገዛትን አይሹም ይላል።

39ኛ ጥያቄ፦ ለዘላለም ደኅንነታችሁ የተረጋገጠላችሁ መሆኑን ማወቃችሁ፥ ጌታን ለመታዘዝና እርሱን ለማገልገል እንድትፈልጉ እንዴት ሊያደርጋችሁ ይችላል?

ለዘላለም ደኅንነታችን የተረጋገጠ መሆኑን ስንገነዘብ፥ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ያድጋል። እንዲሁም በደኅንነታችን ረገድ የሰጠንን አስደናቂ በረከት ሁሉ ማየት እንችላለን። በተጨማሪም እርሱን ለማወቅና እርሱን ለማፍቀር ፍላጎት ያድርብናል። እርሱን ለማፍቀርና እርሱን ለመውደድ ለእርሱ መታዘዝ ይጠበቅብናል። ስለዚህ ጊዜአችንን ከእርሱ ጋር ማሳለፍ አለብን። እንደዚሁም ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። ደኅንነታችን ለዘላለም የተረጋገጠና የተጠበቀ መሆኑን መገንዘባችን ወደ እግዚአብሔር በበለጠ እንድንቀርብ ያስችለናል። ከዚህ ጋር የዘላለማዊውን ደኅንነታችንን በረከት ስናስተውል፥ ከአሮጌው ሕይወታችን ይልቅ አዲሱ ሕይወታችን በክርስቶስ ውስጥ ጎልቶ ይታየናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ቀድሞው አሮጌ ሕይወታችን ዳግም ለመመለስ ጨርሶ አናስብም። በአዲሱ ሕይወታችን ውስጥ በምናገኛቸው መንፈሳዊ ጥቅሞችና በረከቶች ደስ ተሰኝተን መኖርን እንመርጣለን። ያገኘነው ዘላለማዊ ዋስትና በተቀበልናቸው በረከቶች ረክተን በአዲስ ሕይወታችን እንድንኖር ይቀሰቅሰናል። ልክ ልጆች በወላጆቻቸው ጥበቃና እንክብካቤ ውስጥ በመሆናቸው ምክንያት ወላጆቻቸውን ለማክበርና ለመታዘዝ ፍላጎት እንደሚያድርባቸው ሁሉ፥ እኛም በፍቅሩ ጥበቃ ውስጥ መሆናችንን በምንገነዘብበት ጊዜ፥ እግዚአብሔርን ለማክበርም ሆነ ለመታዘዝ በጣም እንፈልጋለን።

አራተኛ ቀን— የዘላለማዊ ዋስትና ማረጋገጫና የእግዚአብሔር ቅዱሳን ጽናት፥ ክፍል 3

ባለፉት ሁለት ቀናት ውስጥ በተከታተልነው ትምህርት ላይ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በእውነት ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ለዘላለም ዋስትናቸው የተጠበቀ መሆኑን እንደሚያስተምር ተገንዝበናል። እግዚአብሔር እነርሱን የማዳኑን ተግባር እነርሱ ከእርሱ ጋር የታረቁ መሆናቸውን በማሳወቅ ጀምሮአል፤ ይህንንም የጀመረውን የማዳን ተግባር በታማኝነት ከግብ ያደርሳል። በዚሁ መሠረት የመጨረሻው የደኅንነታቸው ዋስትና እንዲሆንም የራሱን መንፈስ ቅዱስ ሰጥቶአቸዋል፤ ይህንንም ሲያደርግ ማንም ከፍቅሩ ሊለያቸው እንደማይችል ተስፋውን አክሎ ሰጥቶአቸዋል። እነዚህ አማኞችም የክርስቶስ አካል ክፍል ስለሆኑ፥ ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ራሱ ይማልድላቸዋል። እነዚህ ሁሉ አስደናቂ የሆኑ እውነታዎች በእርግጥ ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች የደኅንነታቸው ነገር ዋስትና ያለውና የተረጋገጠ መሆኑን ያስገነዝበናል።

ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቲያኖች ደኅንነታቸውን የሚያጡ ዓይነት ትርጉም የያዙ የሚመስሉ ክፍሎች የሉምን? እንደዚሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደኅንነታቸውን ያጡ አማኞች ስለመኖራቸው በምሳሌነት

የሚጠቀስባቸው ክፍሎች የሉምን? እንግዲህ በዛሬው ትምህርታችን ውስጥ፥ አማኞች ደኅንነታቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ የሚመስሉ ክፍሎች ስለሚሰጡት ትምህርት እንመረምራለን። እነዚህን ክፍሎች ሁልጊዜ ልናስታውሳቸው ከሚገባን ሁለት መንፈሳዊ መመሪያዎች በመነሣት የምናጠና ሲሆን፥ መመሪያዎቹም፦ 1) በክርስቶስ ማመንን ለማመልከት የሚደረግ የሃይማኖት መግለጫ፥ በክርስቶስ ከሚኖረን እውነተኛ እምነት ጋር አንድ አይደለም። 2) እውነተኛ ክርስቲያኖች ኃጢአትን ይሠራሉ፥ ከዚህ በኋላም ዘላለማዊ ደኅንነታቸውን ሳያጡ ስለሠሩት ኃጢአት እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል።

1. በክርስቶስ ላይ ያለንን እምነት ማሳወቅ፥ በክርስቶስ ላይ ካለን እውነተኛ እምነት ጋር አንድ አይደለም።

40ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ዮሐ. 2፡19 አንብብ። ሰዎች የክርስትና እምነታቸውን ጨርሰው በሚተዉበት ጊዜ ይህ ምንን ያመለክታል?

41ኛ ጥያቄ፦ ዮሐ. 8፡31 አንብብ። ሰዎች በእውነት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለመሆናቸው ምልክቱ ምንድን ነው?

42ኛ ጥያቄ፦ ዕብ. 3፡14 አንብብ። ከክርስቶስ ጋር ወራሾች ለመሆናችን ምልክቱ ምንድን ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምናገኛቸው እውነታዎች መካከል እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነው፥ በክርስቶስ ማመንን መናገር፥ በክርስቶስ ላይ ካለ እውነተኛ እምነት ጋር አንድ አለመሆኑን በግልጽ የሚያስረዳው ነው። በ16ኛው ትምህርት ውስጥ እንደ ተመለከትነው፥ ሰዎች በክርስቶስ የሚያምኑ መሆናቸውን መግለጣቸው ብቻ ወይም እርሱን በአዳኝነት አምነው የተቀበሉ መሆናቸውን መናገራቸው ብቻ በቂ አለመሆኑን ተገንዝበናል። እንደዚሁ ሁሉ ሰዎች ከልብ ሳይሆን ላይ ላዩን ብቻ ክርስቶስን የተቀበሉ አስመስለው ቢጸልዩ ይህም በቂ አይደለም። ይህ ብቻም አይደለም፥ ሰዎች ሰይጣንን ከደውና ኮንነው ክርስቶስን መቀበላቸውን መናገራቸው ብቻም በቂ አይደለም። ስለዚህ ከልብ ሳይሆን በውጪአዊ ስሜት ላይ ብቻ የተመሠረተ በክርስቶስ ስለማመን የሚደረግ የአፍ መግለጫ ብቻም ማንንም ሊያድን አይችልም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከልባቸው አምነው የተቀበሉትን ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር የለያቸው መሆኑን የሚገነዘቡትና ለደኅንነታቸው በራሳቸው መልካም ሥራ ምንም ተስፋ ሳያደርጉ እርሱን የሚማጠኑትን እግዚአብሔር ያድናቸዋል። በኢየሱስ የሚመኩትንና እርሱን ተገን የሚያደርጉትን ብቻ እግዚአብሔር ያድናል።

እንደዚሁም ሰዎች ክርስቶስን ከልባቸው አምነው በመቀበላቸው ምክንያት፥ ለእርሱ ታማኞች ሆነው እንደሚኖሩ፥ በውጪአዊ ድርጊታቸው በምልክትነት የሚገልጡ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ አክሎ ያስተምረናል። ሰዎች በክርስቶስ የሚያምኑ መሆናቸውን በይፋ ከመግለጥ ቢቆጠቡ ደግሞም ቢያቆሙ ይህ ድርጊት በመጀመሪያ ደረጃ እውነት ዳግም ያልተወለዱ መሆናቸውን የሚያሳይ ምልክት ነው። 1ኛ ዮሐ. 2፡19 ውስጥ ብዙ ሐሰተኞች

የሆኑ ክርስቲያኖች የተቀበሉትን እምነትና ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያላቸውን አንድነት መተዋቸውን ይገልጻል። ዮሐንስ ሲናገር የተቀበሉትን እምነትና ከሌሎች አማኞች ጋር የነበራቸውን ኅብረት በተዉ ጊዜ፥ ይህ እምነታቸውን ከጠበቁት ጋር አንድነት የሌላቸው ለመሆኑ ምልክት ነው ይላል። ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አላወቁትም። ቀድሞውንም ቢሆን እውነተኞች ክርስቲያኖች አልነበሩም። እውነተኞች ክርስቲያኖች ቢሆኑ ኖሮ፥ ዮሐንስ በእምነታቸው ጸንተው በቆዩ እና ከሌሎች አማኞች ጋር የነበራቸው አንድነትም አብሮአቸው በዘለቀ ነበር ብሏል። ምንም እንኳን ሌሎች እንደ እውነተኛ ክርስቲያኖች ቆጥረው ቢቀበሉዋቸውም፥ በመጨረሻው ላይ የተቀበሉትን እምነት መተዋቸው የሚያስረዳው ጌታን በእውነት ያላወቁት መሆናቸውን ነው። ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ 8 ውስጥ ደቀ መዝሙሮቹ መሆናቸውን ሊገልጡለት ለሞከሩ ለተሰበሰቡ ብዙ አይሁዳውያን ሲናገር እንመለከታለን። በቁጥር 31 ውስጥ ኢየሱስ በእውነት እነርሱ ደቀ መዛሙርቱ ከሆኑ በቃሉ እንደሚኖሩ አስረዳቸው። በእውነት ዳግም በክርስቶስ የተወለዱ አማኞች እስከ መጨረሻው ድረስ ለኢየሱስ ቃል ታማኞች ሆነው ይኖራሉ። በምንም አኳኋን ክርስቶስን በመጨረሻው ጊዜ ሙሉ በሙሉ አይተዉትም።

፩ኛ ዮሐንስ 3፡14 እምነታችንን እስከ መጨረሻ አጽንተን ብንይዝ ከክርስቶስ ጋር ወራሾች ነን ሲል ይነግረናል። ይህ ጥቅስ የተገለጠበትን የግሥ ጊዜ በጥንቃቄ መመልከቱ አሳቡን ለመገንዘብ ይረዳናል። ቁጥሩ እምነታችንን እስከ መጨረሻው ድረስ አጽንተን ብንይዝ ከክርስቶስ ጋር ወራሾች እንሆናለን አይልም። እንዲህ ቢል ኖሮ የወደፊቱ ደኅንነታችን እምነታችንን አጥብቀን ለመያዝና ለመጽናት በምናደርገው ጥረት ላይ ይመሠረታል የሚል አንድምታ በያዘ ነበር። ታዲያ ይህ ጥቅስ ምን ይላል? ጥቅሱ የሚለው እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንይዝ፥ ከክርስቶስ ጋር ወራሾች ለመሆን ችለናል ነው። አስቀድመን በእውነት ድነናል፥ እንዲሁም በእውነት ዳግም ተወልደናል የሚለው አሳብ በክርስትና እምነታችን ውስጥ ጸንተን ከመቆየታችን አቅጣጫ የሚታይ እውነታ ነው። እንዲያው ብቻ በአንደበታቸው ክርስቲያኖች መሆናቸውን የሚለፍፉ ሁሉ፥ እውነተኞች ክርስቲያኖች አይደሉም። በእውነት ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ብቻ በክርስትና ግዴታቸው ጸንተው ባለማወላወል ይዘልቃሉ። እንዲህ ያሉ የልብ ክርስቲያኖች ቀደም ሲል በይፋ የገለጡትን እምነታቸውን በምንም ሁኔታ በመጨረሻው ላይ ተስፋ ቆርጠው አይተዉም።

43ኛ ጥያቄ፡- ግቴ. 7፡21-23 አንብብ። በኢየሱስ ስም ታላቅ ኃይል የታየበት ሥራ በፈጸሙ ሰዎች ላይ በፍርድ ቀን ምን ብይን ይሰጥባቸዋል?

44ኛ ጥያቄ፡- ግቴ. 10፡1፥4 አንብብ። ሀ) ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ምን ሥልጣንን ሰጣቸው? ለ) ዮሐ. 6፡70-71 አንብብ። ይሁዳ ገና ደቀ መዝሙር ሆኖ ጌታን ሲከተል በነበረበት ጊዜ፥ ኢየሱስ ስለ ይሁዳ ምን ተናገረ?

45ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዘኍል. 24፡15-16 አንብብ። የበለዓም ትንቢት በምን ራእይና ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ነበር? ለ) ኢያሱ 13፡22 አንብብ። የበለዓም ሙያ ምን

ነበር? ምን እየተባለ ይጠራ ነበር? ሐ) 2ኛ ጴጥ. 2፡1፥15 አንብብ። ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ በለዓም ሲናገር እንዴት ያለ ሰው ነበር አለ?

ብዙ ሰዎች ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖችን እንደሚያውቁና እነዚህም ክርስቲያኖች ኋላ ላይ በክርስቶስ የነበራቸውን እምነት እንዳቋረጡ ይናገራሉ። እነዚህ ይህን የሚሉ ሰዎች፥ እነዚያ ክርስቲያኖች በእንቅስቃሴአቸው መልካም የሆነ የክርስትናን ሕይወት የኖሩ ስለሚመስሉ በእርግጥም ዳግም የተወለዱ እንደሆኑ አድርገው ያውቋቸው ነበር። ምናልባትም እነዚህ ሰዎች ኃይለኞች ወንጌላውያን ሆነው ይሆናል፤ ወይም ታምራትን ይሠሩና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚከናወኑ ተግባራትንም ሲያከናውኑ ይታዩ ነበር። ምናልባትም ታላላቅ ክርስቲያናዊ መሪዎች ነበሩ። ኋላ ግን የክርስትና እምነታቸውንና ሕይወታቸውን ትተዋል። እነዚህ ሰዎች ደኅንነታቸውን ያጡ የእውነተኞች ክርስቲያኖች ምሳሌ ሊመስሉ ይችሉ ይሆናል። በዚሁ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ስለሚመስሉ ሰዎች አያሌ ምሳሌዎችን ያቀርባል። እነዚህ ሰዎች እውነተኞች አማኞች አለመሆናቸውን በመጨረሻው ተግባራቸው ያሳዩ ናቸው። ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ 7፡21–23 ሲናገር ብዙዎች በሰሙ ትንቢትን እንደሚናገሩ፥ ተአምራትን እንደሚያደርጉና አጋንንትን እንደሚያወጡ ገልጾአል። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች እርሱ በፍጹም ስለማያውቃቸው፤ በመጨረሻው ቀን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገቡም። ምንም እንኳ እነዚህ ሰዎች በሚያደርጉዋቸው ድንቅ በሆኑ መንፈሳዊ ተግባራት የኢየሱስ ተከታዮች መስለው ቢታዩም፥ በውስጣቸው ግን ዳግም የተወለዱ አማኞች አልነበሩም። ማስተዋል ያለባችሁ ነገር ኢየሱስ አንድ ጊዜ አውቃቸዋለሁ አለማለቱና የእነርሱም ደኅንነትን የማጣት ሁኔታ ነው። ጌታም፤ በፍጹም አላውቃችሁም ነው ያላቸው። በእውነትም፥ የተረጋገጠላቸው በክርስቶስ የሚታመኑ አማኞች አልነበሩም።

ይሁዳ እንዲህ ያለ ሰው ነበር። ማቴዎስ 10፡1 እንደሚነግረን፤ ጌታ ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት የመፈወስንና አጋንንትን የማውጣት ሥልጣንን ሰጥቷቸው ነበር። በተለይ ቁጥር 4 እንደሚለው፤ ይሁዳ ከአሥራ ሁለቱ መካከል አንደኛው ነበር። ስለዚህ ይሁዳ በኢየሱስ ስም አጋንንትን ያወጣና ደግሞም ይፈውስ ነበር። ነገር ግን ይሁዳ በጭራሽ በክርስቶስ የሚያምን እውነተኛ አማኝ አልነበረም። በዮሐንስ 6፡70–71 ውስጥ፥ ይሁዳ በውጪአዊው ሁኔታው የኢየሱስ ተከታይ በነበረበት ጊዜ፥ ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን የመረጠ ቢሆንም፥ አንደኛው (ይሁዳ) ግን ዲያብሎስ እንደ ነበረ ተናግሮአል። በዚያን ጊዜ ገና ይሁዳ ሐሰተኛ ደቀ መዝሙር መሆኑን ኢየሱስ አመልክቷል። ቢሆንም ከደቀ መዛሙርቱ መካከል አንዳቸውም እንኳን ይሁዳ ሐሰተኛ ደቀ መዝሙር መሆኑን የጠረጠረ አልነበረም። ኢየሱስና ይሁዳ ራሱ ብቻ ይህን ያውቁ ነበር። ነገር ግን በ1ኛ ዮሐ. 2፡19 ውስጥ እንደምናነበው፥ በመጨረሻው ላይ ይሁዳ በልቡ ውስጥ ተሰውሮ የነበረውን ተናገረ። በዚህም ክርስቶስን አሳልፎ ሰጠ፥ ደግሞም በይፋ ገልጦት የነበረውን እምነቱንም ካደ።

በለዓም የሕያው እግዚአብሔር ተከታይ ይመስል የነበረ ሰው ሌላ ምሳሌ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰጠውን ታላላቅ ቃላት ይናገር ነበር። ኦሪት ዘኍልቁ 24፡15-16 በለዓም እግዚአብሔር በገለጠለት ራእይና እውቀት ላይ የተመሠረተ ትንቢት መናገሩን ይጠቅሳል። ኢያሱ 13፡22 ደግሞ በለዓም የጥንቆላ ተግባር ይፈጽም እንደ ነበረ ያስገነዝባል። ምንም እንኳ በለዓም የእግዚአብሔር ነቢይ መስሎ ቢታይም፥ እንዲሁም እግዚአብሔር በሞዓብ ተራራ ላይ በእርሱ አማካይነት ቢናገርም፥ በለዓም ግን በእርግጥ ጠንቋይ ነበር! ጴጥሮስም ይህ ሰው ሐሰተኛ የሆነ ነቢይ መሆኑን ያረጋግጣል። በ2ኛ ጴጥሮስ ውስጥ ሐዋርያው ስለ ሐሰተኞች ኽሊያትና መምህራን በሚያስጠነቅቅበት ጊዜ፥ በለዓምን እንደ አንደኛው ምሳሌ አድርጎ ጠቅሶታል። እንግዲህ በለዓም በእግዚአብሔር እውነተኛ ነቢይ ተመስሎ ቀርቧል፥ እግዚአብሔርም በእርሱ አንደበት አማካይነት የራሱን ቃል ተናግሮአል። ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆን፥ በለዓም እውነተኛ የእግዚአብሔር ተከታይ አልነበረም። እርሱ ሐሰተኛ የሆነ ነቢይና ጠንቋይም ነበር።

በክርስቶስ ማመንን በቃል ማስታወቅ ብቻ እውነተኛ የሆነ በክርስቶስ የጸና እምነት በልብ ውስጥ መኖሩን አይገልጽም። እውነተኛና በክርስቶስ ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች በምንም ኣኳኋን በመጨረሻው ጊዜ ለክርስቶስ የገቡትን የእምነት ቃል ኪዳን አፍርሰው ከእርሱ አይለዩም። አንዳንድ እግዚአብሔር የሚገለገልባቸው የሚመስሉ ሰዎች እውነተኞች የልብ ክርስቲያኖች ሊሆኑ የማይችሉበት ጊዜ አለ። ይሁዳ እንዳደረገው ሁሉ፥ በክርስቶስ የነበራቸውን እምነት በሚክዱበት ጊዜ፥ ይህ ድርጊታቸው ቀድሞውኑ ክርስቶስን በእውነት ከልባቸው አያውቁት እንደ ነበረ ይገልጣል።

2. እውነተኞች ክርስቲያኖች ኃጢአት ቢሠሩም ከእግዚአብሔር ዘንድ ግሣፄአቸውን ይቀበሉና ዘላለማዊ ደኅንነታቸውን አያጡም።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልንረዳው የሚገባን ሁለተኛውና ጠቃሚ እውነታ፥ አማኞች ኃጢአትን እንደሚሠሩና እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው፥ እንዲሁም በእግዚአብሔር እጅ ክፉኛ ቢቀጡም ዘላለማዊ ደኅንነታቸውን እንደማያጡ ነው።

46ኛ ጥያቄ፡- ሉቃስ 22፡31-32 አንብብ። ሀ) ጴጥሮስ ንስሐ ከገባ በኋላ ኢየሱስ ምን አለው? ለ) ሉቃስ 22፡62 አንብብ። ጴጥሮስ ኢየሱስን ከክዳ በኋላ ምን አደረገ?

47ኛ ጥያቄ፡- ዮሐ. 21፡17 አንብብ። ሀ) ኢየሱስ ጴጥሮስን መላልሶ «ትወደኛለህን» ብሎ በጠየቀው ጊዜ የጴጥሮስ መልስ እንዴት ነበር? ለ) ጴጥሮስ መልስ ከሰጠ በኋላ፥ ኢየሱስ ምን አለው?

48ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ሳሙ. 12፡13-14 አንብብ። ሀ) ነቢዩ ናታን ወደ ዳዊት ዘንድ ሄዶ ማመንዘሩንና ኬጢያዊ የነበረውን ኦርዮንን ማስገደሉን፥ በዚህም ኃጢአት መሥራቱን በነገረው ጊዜ ዳዊት ምን ብሎ መለሰ? ለ) እግዚአብሔር ለዳዊት ምን ሲል መለሰለት? ሐ) ዳዊት በሠራው ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ ቀጣው?

49ኛ ጥያቄ፡– 1ኛ ቆሮ. 11፡29–30 አንብብ። አንዳንድ የቆሮንቶስ አማኞች በምን ምክንያት ታምመው ሞቱ?

50ኛ ጥያቄ፡– 1ኛ ቆሮ. 3፡12 –15 አንብብ። ሀ) አንድ ሰው ሕይወቱን በወርቅ፥ በብርና በከበረ ድንጋይ ቢገነባ ምን ይሆናል (ቁ. 14)? ለ) አንድ ሰው ሕይወቱን በእንጨት፥ በገለባና በድርቆሽ ቢገነባ ምን ይሆናል (ቁ. 15)?

በጎጢአት ወድቀው በኋላ ጎጢአተኝነታቸው ስለ ተሰማቸው ንስሐ ገብተው ወደ ቀድሞ መልካም ሕይወታቸው በመመለስ እውነተኛ አማኞች መሆናቸውን ያሳዩ፥ በዚህም ተግባራቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የታወቁ አርአያ የሆኑ ሁለት ሰዎች ጴጥሮስና ዳዊት ነበሩ። ጴጥሮስ ኢየሱስን ሦስት ጊዜ ካደው። ከመካዱም በፊት ተጸጽቶ ንስሐ እንደሚገባ ኢየሱስ ከነገረው በኋላ፥ በሚመለስበት ጊዜ ወንድሞቹን እንዲያጽናናቸው አሳስቦታል። እንደዚሁም ከመክዳቱ በፊት ኢየሱስ ሌሎች ደቀ መዛሙርትን የጴጥሮስ ወንድምች በማለት ጠርቷቸዋል። ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስ በጎጢአት ውስጥ እንደሚወድቅ የሚያውቅ ቢሆንም፥ ጴጥሮስ በውስጡ የነበረውን እውነተኛ እምነት ኢየሱስ ያረጋግጥለት ነበር። ጴጥሮስም በኢየሱስ ላይ የነበረውን እምነት ልባዊ በሆነ ንስሐ ገልጦታል። ኢየሱስም የጴጥሮስን እውነተኛ እምነት፥ እንደሚወደው በነገረው ጊዜና እንዲያገለግለው ባሳሰበው ወቅት መስክሮለታል (ዮሐ. 21፡17)። ዳዊት ደግሞ ጎጢአት በመሥራቱ ምክንያት በእግዚአብሔር የተገሠጸ ሌላው ሰው ነው። ዳዊት አመንዝሯል፥ ደግሞም ኬጢያዊውን አርዮንን አስገድሏል። ነገር ግን ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ ዘንድ ቀርቦ ስለፈጸመው ጎጢአት በነገረው ጊዜ፥ ወዲያውኑ ጎጢአቱን በመናዘዝ በእግዚአብሔር የሚያምን እውነተኛ ሰው መሆኑን አሳየ። እግዚአብሔርም በናታን አማካይነት ጎጢአቱ የተሰረየለት መሆኑን አበሠረው። መዝሙር 51 ዳዊት ለእግዚአብሔር ያቀረበው የንስሐ ጸሎት ነው። ይህ የንስሐ ጸሎት ምንም እንኳን ጎጢአት ቢሠራ፥ በጎጢአቱ ተጸጽቶ በእውነት በንስሐ የሚመለስ ሰው መሆኑን መስክሮለታል። እግዚአብሔር ዳዊት፥ ከቤርሳቤህ የወለደው ልጅ እንዲሞት በማድረግ በሠራው ጎጢአት ገሥጾታል (2ኛ ሳሙ. 12፡14–18)። ትዕማር የምትባለው ልጃገረድ ተገድዳ መደፈርዋና አቤሰሎም ያስከተለው ዐመፅ ሁሉ ዳዊት የፈጸመው የግብዝነት ጎጢአት ውጤት ነበር። በእርግጥ ዳዊት በጎጢአቱ ምክንያት ክፉኛ ተሠቃይቷል። ነገር ግን ደኅንነቱን አላጣም።

በቆሮንቶስ በነበረች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጎጢአት የሠሩና ፍርዳቸውን የተቀበሉ የዚህ ምሳሌ የሚሆኑ ብዙ አማኞች ነበሩ። ምንም እንኳን እነዚህ ምእመናን ደኅንነታቸውን በዚህ ምክንያት ባያጡም፥ በጎጢአታቸው ምክንያት የእግዚአብሔርን ተግሣጽ ተቀብለዋል። በ1ኛ ቆሮ. 11፡29–30 ባለው ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር፥ ከእነርሱ መካከል አንዳንዶቹ የታመሙት፥ ሌሎች ደግሞ የሞቱት የጌታን ሥጋና ደም ሳይገባቸው ስለተቀበሉ እንደ ነበረ አስጠንቅቋቸዋል። ክርስቶስን በማዕከልነት በመመልከትና ለክርስቲያን ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው በማሰብ ፈንታ፥ የጌታን ቅዱስ እራት ለራሳቸው ሥጋዊ እርካታና ለስካር አደረጉ። ስለዚህ እግዚአብሔር በበሽታና በሞት ቀጣቸው። ግን ቀጣቸው እንጂ ደኅንነታቸውን

አላሳጣቸውም። በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወታቸውን በወርቅ፥ በብርና በከበረ ድንጋይ የሚሠሩ አማኞች በክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት በሚቀርቡበት ጊዜ ስለሚቀበሉት ሽልማት ይናገራል። እነዚህ ሁሉ በክርስቶስ ኃይልና ስለ ክብሩም የሚደረጉ የአገልግሎት ምልክቶች ናቸው። ሌሎች ደግሞ ሕይወታቸውን በእንጨት፥ በገለባና በድርቆሽ ይሠራሉ። እነዚህ ደግሞ በራሳችን ኃይልና ለራሳችን ክብር የሚሠሩ ሥራዎች ምልክቶች ናቸው። ጳውሎስ እነዚህ ለራሳችን የሚከናወኑ ተግባራት በክርስቶስ ዙፋን ፊት ይቃጠላሉ ይላል። ለራሳቸው የሚኖሩ አማኞች፥ በክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት የዘላለም ሕይወት ስለማይኖራቸው ሽልማትንም ሊያገኙ አይችሉም። ነገር ግን አሁንም የመዳን ዕድል አላቸው። ኑሮአቸው ኪሳራ ብቻ ይሆናል፤ ነገር ግን ዘላለማዊ ደኅንነታቸውን አያጡም።

3. ክርስቲያንነታቸውን በመናገር በአንጻሩ የእውነተኞች ክርስቲያኖችን ሕይወት የማይኖሩ ሰዎች፥ ዳግም የተወለዱ ወይም ያልተወለዱ መሆናቸውን ሌሎች አማኞች ለይተው ሊያውቁ አይችሉ ይሆናል።

51ኛ ጥያቄ፡– 2ኛ ቆሮ. 13፡5 አንብብ። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ምን እንዲያደርጉ ነገራቸው?

እያንዳንዱ ግለሰብ በእውነት ዳግም የተወለደ ክርስቲያን መሆኑንና አለመሆኑን በእርግጥ ያውቃል። እኛም ብንሆን በክርስቶስ የምናምን ወይም የማናምን መሆናችንን እናውቃለን። እግዚአብሔርም በሰጠው ተስፋ፥ ወልድ ያለው ሕይወት አለው ብሏል (1ኛ ዮሐ. 5፡12)። ሆኖም፥ አንድ ክርስቲያንነቱን ያሳወቀ ግን በኃጢአት ውስጥ የሚኖር፥ በዚህም ለክርስቶስ የገባውን ቃል ኪዳን ያፈረሰ ሰው በእውነት ዳግም የተወለደ ይሁን አይሁን መሥፈርታችንን በቀኖና ላይ በማድረግ እንኳ ለማወቅ አንችልም። እንደዚሁም አንድ ሰው ክርስቲያንነቱን ያሳውቅ፥ ግን ዳግም ያልተወለደ ወይም እውነተኛ ክርስቲያን ሆኖ ወደ ኃጢአት ሸርተት ያለ፥ ግን በመጨረሻ ንስሐ ገብቶ የሚመለስ መሆኑን ለይተን በእርግጠኝነት መናገር አንችልም። ከዚህም በስተቀር ወንድም ወይም እኅት በክርስቶስ የነበሩ፥ ኋላ ግን ከጌታ የራቁ፥ በይሁዳ ወይም በጴጥሮስ ደረጃ ይመደቡ ወይ አይመደቡ ፍጹም ልናውቅ አንችልም።

በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡5 ውስጥ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲናገር፥ በእምነት ቆመው እንደሆነ ራሳቸውን እንዲመረምሩ ያስጠነቅቃቸዋል። ጳውሎስ በቆሮንቶስ ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሏል። በግልም በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ አብዛኛዎቹን ምእመናን ያውቃቸው ነበር። ሁሉም ራሳቸውን ክርስቲያን አድርገው የሚቆጥሩ መሆናቸውን ያውቅ ነበር። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ወደ ብዙ ዓይነት ኃጢአት ተንሸራትታ ገብታ ነበር። እነዚህም መከፋፈል፥ የሞራል ውድቀት፥ ስካርና በጸጋ ስጦታዎች አላግባብ መጠቀም ነበሩ። እርሱም ከንስሐቸውና ሁለት መልእክቶችን ከጻፈላቸው በኋላ፥ በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡5 ውስጥ ከመካከላቸው

እነማን ዳግም እንደ ተወለዱና ማንኛቸውም ራሳቸውን እንደ ክርስቲያን እንደሚቆጥሩ የማያውቅ መሆኑን ይጠቅሳል። ስለዚህ በአጠቃላይ በእውነት ጌታ እንደ መድኅናቸው አድርገው በእውነት ያውቁት እንደሆነ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲመረምሩ ያሳስባቸዋል። ጌታ ኢየሱስ በውስጣቸው ስለሚኖር ንስሐ እንዲገቡ ያስጠነቅቃቸዋል። ጳውሎስ ራሱ እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ከቆሮንቶስ ምእመናን ውስጥ የትኞቹ በእውነት ዳግም የተወለዱና በአንጻሩ በጋጢአት ውስጥ የሚኖሩ ሐሰተኞች ክርስቲያኖች እንደሆኑ አያውቅም ነበር።

52ኛ ጥያቄ፡– ቢያንስ አንድ ራሱን እንደ ክርስቲያን የሚቆጥርና ግን እንደ እውነተኛ ክርስቲያን የማይኖር የምታውቀውን ሰው ስም ጻፍ። እንዲህ ካለው ሰው ጋር እንዴት አድርገህ ልትወያይ ትችላለህ?

ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስን ምእመናን ሁኔታ በታዘበ ጊዜ የተሰማው ስሜት፥ ክርስቲያን ነኝ እያለ በጋጢአት ውስጥ የሚኖር ክርስቲያን በሚያጋጥመን ጊዜ እኛንም የሚሰማን ስሜት ነው። ስለዚህ እኛም ራሳቸውን እንዲመረምሩ ልንለምናቸው ይገባል። ስለዚህ እንዲህ እንበላቸው፥ ወንድም (እኅት) ክርስቲያን ነን ትላላችሁ። ነገር ግን እንደ ክርስቲያን አትኖሩም። ራሳችሁን ደህና አድርጋችሁ መርምሩ! በእውነት ክርስቲያኖች ከሆናችሁ ጌታ ኢየሱስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን? ንስሐ መግባት አለባችሁ፥ በዚህም ራሳችሁን ከእርሱ ጋር ማስታረቅና ሰላማውያን መሆን ይኖርባችኋል። ግን ወንድሜ (እኅቴ) በእርግጥ ልትገነዘቡት የሚገባችሁ ቁም ነገር በእውነት ዳግም ተወልዳችሁ እንደሆነ ነው። ስለዚህ ለክርስቲያኖች በተፈቀደው ሁኔታ ስለማትኖሩ፥ ክርስቶስን በእምነት እንደ ግል መድኃኒታችሁ ተቀብላችሁ የምትኖሩ ስለ መሆናችሁ ራሳችሁን ልትመረምሩና እርግጠኞች ልትሆኑ ይገባል።»

4. እምነታቸውን በይፋ በማሳወቅ፥ ራሳችውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ፥ በእውነት አማኞች መሆናቸውን እንዲመራምሩ፥ ወይም ክርስቲያኖች በእምነታቸው እንዲጠነክሩ እንጂ ወደ ጋጢአት እንዳይወድቁ፥ ማስጠንቀቂያ የሆነ ትምህርትን የሚሰጡ ጥቅሶች።

4.1 ክርስቲያኖች ደኅንነታቸውን የሚያጡ የሚመስል ትምህርት ለክርስቲያኖች የሚያቀርቡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍለ ምንባቦች፥ ለክርስቲያኖች ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ ናቸው።

53ኛ ጥያቄ፡– 1ኛ ቆሮ. 9፡27 አንብብ። ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስትና አገልግሎቱ ላይ ከውድድር ውጪ እንዳይሆን በሰውነቱ ላይ ምን ማድረግ ነበረበት?

54ኛ ጥያቄ፡– 1ኛ ቆሮ. 10፡11–13 አንብብ። ሀ) ተረጋግተው የቆሙ የሚመስላቸው አማኞች ምን ዓይነት ስሜት አላቸው? ለ) አማኞች በሚፈተኑበት ጊዜ፥ ፊታቸውን ወዴት ይመልሱ?

55ኛ ጥያቄ፡– ዮሐ. 15፡1–8 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ፍሬ የማያፈሩትን ቅርንጫፎች ምን ያደርጋቸዋል? (ቁጥር 2ና 6) ለ) ደቀ መዛሙርት ፍሬ እንዲያፈሩ

ክርስቲያኖች ደኅንነታቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ የሚያስተምሩ አንዳንድ ክፍለ-ምንባቦች፥ ክርስቲያኖች የንጽሕናና የቅድስና ሕይወት እንዲኖሩ እንጂ ወደ ኃጢአት እንዳይወድቁ፥ ከዚህም በስተቀር፥ በእምነታቸው እንዲጠነክሩ የሚያስጠነቅቁ ናቸው። እንደዚሁም በሚሠሩት ኃጢአት እግዚአብሔር ክፉኛ ስለሚገሣቸው የሰማይ ሽልማታቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ የሚያሳስቡ ናቸው።

በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 9 ውስጥ ጳውሎስ ስለተጣለበት የኃላፊነት ተግባር ይናገራል። እርሱም ምንም እንኳን ብዙ መብቶች ቢኖሩትም፥ በወንጌላዊነት ሥራው የበለጠ ውጤታማ ለመሆን በመምረጥ በመብቶቹ ሁሉ መጠቀምን አልፈለገም። በቁጥር 27 ውስጥ፥ እርሱ ኃላፊነትና የአገልግሎት ተግባሩን ከሩጫ ተወዳዳሪ ተግባር ጋር አመሳስሎታል። አንድ ሯጭ አካሉን በጠንካራ ሥልጠና ሥር እንደሚያስገዛ ሁሉ፥ ስለ ጌታ የሚያደርገው ምስክርነት ወደፊት ገፍቶ ውጤታማ ይሆንለት ዘንድ፥ ሐዋርያው ራሱን በመቆጣጠር ከሌላው ነገር ሁሉ ሊወስነው ችሏል። በክርስትና ሕይወቱ ውስጥ ራሱን መቆጣጠርና በሥርዓት መያዝ ቢያቅተው ኖሮ፥ ከውጤታማ ወንጌላዊነትና ሐዋርያነት ተግባር ብቃት አጥቶ ከውድድር ውጭ በሆነ ነበር። በዚህ ፈንታ ጳውሎስ አቅሙ የፈቀደለትን በከፍተኛ ደረጃ ለክርስቶስ አገልግሎቱን ለማቅረብ እንዲችል፥ በሕይወቱ ሁሉ ራሱን በሥነ ሥርዓት በመምራት ራሱን ለጌታ አስገዛ።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡11-13 ውስጥ፥ ጳውሎስ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ውስጥ ትምክህት እንዳይኖርባቸው አስጠነቀቃቸው። ከቁጥር 1-10 ባለው ጥቅስ እንደተገለጠው እስራኤላውያንን ምሳሌ በማድረግ እነርሱም ቢሆኑ በኃጢአት ውስጥ ወድቀው፥ እንደ እስራኤላውያን ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ተግሣጽ ሊደርስባቸው እንደሚችል አስጠንቅቋቸዋል። እዚህ ላይ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ባስጠነቀቃቸው ጊዜ፥ እነርሱ በኃጢአት ውስጥ ቢወድቁ ያገኙትን የደኅንነት በረከት የሚያጡ መሆናቸውን አልተናገራቸውም። ነገር ግን ተግሣጽ ሊደርስባቸው እንደሚችል አሳስቦአቸዋል። ሲያስጠነቅቃቸውም በኃጢአት ውስጥ በመውደቅ ፈንታ እግዚአብሔር በሚያዘጋጅላቸው መንገድ ከሚያጋጥማቸው ፈተና ለመውጣት መሞከር እንዳለባቸው አበክሮ ነግሮአቸዋል።

በዮሐንስ ምዕራፍ 15 ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ፍሬ ለማፍራት ቢፈልጉ በእርሱ ጸንተው መኖር እንዳለባቸው አሳስቦአቸዋል። በክርስቶስ ጸንቶ መኖር ማለት፥ ቃሉን በማጥናትን በጸሎት ጊዜን ማሳለፍ ማለት ነው። ደግሞም በምናደርገው ተግባር ሁሉ በእርሱ ላይ መደገፍ፥ ቃኑን ሙሉ ስለ እርሱ ማሰብና ከእርሱ ጋር መነጋገርና ያለማቋረጥም ለእርሱ መታዘዝ ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ በኢየሱስ ጸንተው የማይኖሩ ደቀ መዛሙርት ምንም ዓይነት ፍሬ አፍርተው ሊታዩ አይችሉም። በሕይወታቸውም ውስጥ የክርስትና ባሕሪ ማለትም እንደ መንፈስ ፍሬ ያለ

ተካትቶበት ሊገኝ አይችልም (ገላ. 5፡22-24)። እንዲሁም ለክርስቶስ በሚያደርጉት አገልግሎት ውስጥ የተቃና ውጤት ለማየት አይችሉም። እንዲህ ባሉ አማኞች ላይ ምን ይደርስባቸዋል? ጌታ ኢየሱስ እንደሚለው «ይቆረጣሉ» (ቁጥር 2)፤ ከዚያም ወደ «እሳት» ይጣላሉ (ቁጥር 6)። እዚህ ላይ ጌታ ኢየሱስ እነዚህ ሰዎች ያገኙትን ደኅንነት ያጣሉ፤ ወይም በገሃነም ውስጥ ተጥለው ይቃጠላሉ አላለም። ስለ ወይኑ ግንድና ስለ ቅርንጫፎቹ የጀመረውን ትምህርት ይቀጥላል። በንግግሩም ለአገልግሎት ስለማይበጁ በእግዚአብሔር ይገሠጻሉ፥ እንዲሁም እግዚአብሔር ወደ ጎን አድርጎ ያስቀምጣቸውና ከፈለገም ሕይወታቸውን ይወስዳል ነው ያለው። በአንጻሩም፤ ኢየሱስ የተናገረው በእርሱ ጸንተው የሚኖሩና ፍሬ የሚያፈሩ ደቀ መዛሙርት ፥ ለሌሎች እውነተኞች ደቀ መዛሙርቱ መሆናቸውን እንደሚያሳዩ ነው (ቁጥር 8)። እንዲሁም ለጌታ ኢየሱስ ታማኞች መሆናችን የሚያሳየው ሌላው ነገር እኛ የእርሱ እውነተኞቹ ደቀ መዛሙርት እንደሆንና በዚህም ለአገልግሎት የሚጠቅሙ ብዙ ፍሬዎችን የምናፈራ መሆናችንን ነው። ሆኖም፤ በኢየሱስ ጸንተው የማይኖሩ አማኞች፥ ለእግዚአብሔር የሚጠቅም ምንም ዓይነት ተግባር ሊያከናውኑ አይችሉም። እንዲህ ያሉት ልክ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 3፡12-15 በገለጻቸው አማኞች ይመሳላሉ። እነዚህ ሰዎች ከጌታ አገልግሎት ተገልለው እንዲቀመጡ ይደረግና ኋላም ተግሣጹውን ይቀበላሉ።

56ኛ ጥያቄ፡- ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒታችሁ ተቀብላችሁት ከሆነ፥ እግዚአብሔር በየትኛው የሕይወታችሁ ክፍል ነው ፈተናን ለመቋቋም የእርሱን ኃይል እንድትሹ፥ እንዲሁም በመላ አቅማችሁ እንድታገለግሉትና በጥንቃቄም በእርሱ ጸንታችሁ እንድትኖሩ የሚያስጠነቅቃችሁ? በዚህ አኳኋን እግዚአብሔር የሚያደርግላችሁን ማስጠንቀቂያ በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

4.2 ክርስቲያኖች ደኅንነታቸውን የሚያጡ የሚመስል አሳብ የሚያስተምሩ ከፍለ ምንባቦች ክርስቲያኖች ነን በማለት የሚናገሩ ሰዎች፥ በእርግጥ ክርስቶስን እንደ መድኃኒታቸው አድርገው በመቀበል አምነውበት እንደሆነ ራሳቸውን እንዲመረምሩ ለማስጠንቀቅ ነው።

57ኛ ጥያቄ፡- ዕብ. 6፡4-6 አንብብ። ሰዎች የእግዚአብሔርን ኃይልና ቃሉን ቀምሰውና መንፈስ ቅዱስንም ተቀብለው ኋላ ቢወድቁ ምን ይደርስባቸዋል?

58ኛ ጥያቄ፡- ራእይ 3፡1፤5 አንብብ። ሀ) የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ዝና ምን ነበር? ለ) የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ሁኔታ እንዴት ነበር? እግዚአብሔር አሸናፊ ለሆነው ምንን ይሰጠዋል?

59ኛ ጥያቄ፡- ራእይ 3፡17፥ 20 አንብብ። ሀ) በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ምእመናን ስለ ራሳቸው ምን ያስቡ ነበር? ለ) ስለ መንፈሳዊ ሁኔታቸው፥ እርግጠኛው ነገር ምን ነበር? ሐ) ጌታ ኢየሱስ ልባቸውን ለሚከፍቱለት ምን ያደርግላቸዋል?

ክርስቲያኖች ደኅንነታቸውን ሊያጡ ይችላሉ የሚል ትምህርት የሚያስተምሩ የሚመስሉ አንዳንድ ከፍለ ምንባቦች፥ ክርስቲያኖች ነን

እያሉ፥ ግን ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው ላላመኑት፥ በእውነትም ማስጠንቀቂያዎች ናቸው። ውድቀታቸው የሚያሳየው፥ ገና ወደ ተሟላና እውነተኛ ወደ ሆነ የደኅንነት ተሞክሮ እንዳልደረሱ ስለሆነ፥ ወደተሟላው የደኅንነት ተሞክሮ ለመድረስ በጥንቃቄ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ነው።

የዕብራውያን መልእክት አንባቢዎች ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው ያሳወቁ አማኞች ነበሩ፤ ጸሐፊውም እንደ አማኞች ቆጥሮ ጽፎላቸዋል። ነገር ግን ካሉበት ደረጃ ቢወድቁ፥ ይህ ቀድሞውንም በክርስቶስ አለማመናቸውን የሚያሳይ ምልክት መሆኑን በመንገር ያስጠነቅቃቸዋል። ስለዚህ በእምነታቸው በመጽናት፥ በእውነት በክርስቶስ መሆናቸውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። በዕብራውያን 6፡4–6 ስለ እግዚአብሔር እውነትና ኃይል ብዙ ተሞክሮ የነበራቸውና ኋላ ግን ከክርስቶስ ተለይተው የወደቁትን፥ ደግሞም በንስሐ ታድሰው ሊለወጡ ለሚችሉበት ዕድል ልባቸውን ያደነደኑትን ነበር ደራሲው የማስጠንቀቂያ ቃል የተናገረው፥ «ብርሃን ስለ በራላቸው፥ የመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች ስለ ሆኑና ስማያዊውንም ስጦታ ስለ ቀመሱ፥ እንዲሁም የእግዚአብሔርን መልካም ቃልና የሚመጣውን ዓለም ኃይል ለቀመሱ» ሰዎች ነበር። እዚህ ላይ አንድ ማስተዋል ያለባችሁ ነገር፥ ጸሐፊው ሲናገር እነዚህ ሰዎች አምነዋል፥ ንስሐ ገብተዋል፥ ወይም ወደ እግዚአብሔር ተመልሰዋል አላለም። እነዚህ ሰዎች እውነተኛ ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ናቸውም አላለም። «መቅመስ» የሚለው ቃል አንድ ምግብን መቅመስ እንጂ መዋጥን አያመለክትም። አንዱን ምግብ መቅመስና መትፋት ሊሆን ይችላል። ጸሐፊው ሰዎች የእግዚአብሔር እውነት ቢቀምሱና ራሳቸውን ከክርስቲያኖች ጋር ከቆጠሩ በኋላ የተማሩትንና የተገነዘቡትን ቢተዉ፥ ልባቸውን ለወንጌል የዘጉ በመሆናቸው ሊቀበሉ አይችሉም ማለቱ ነው። ሰዎች ፈውስን በማግኘት፥ የትንቢትን ቃል በመስማት፥ ወይም መንፈስ ቅዱስ ለንስሐ በልባቸው ውስጥ ሲሠራ እየተሰማቸው ኋላ ችላ ብለው በተዉትና ወደ ውድቀት ቢሄዱ፥ ልባቸውን ያጸኑ በመሆናቸው ንስሐ ሊገቡና ወደ ክርስቶስ ሊመጡ ከቶ አይችሉም። ስለዚህ የዕብራውያን ምዕራፍ 6 ቃል፥ ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ሁሉ ከኃጢአታቸው በንስሐ ተመልሰው ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው ለመቀበላቸው እርግጠኞች ሊሆኑ ይገባል።

በራእይ 3፡5 ውስጥ ኢየሱስ ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ጠበቅ አድርጎ ይናገራል። ምንም እንኳን ብዙዎቻቸው ክርስቲያንነታቸውን የሚናገሩ ቢሆኑም (የቤተ ክርስቲያኒቱም አባላት ነበሩ)፥ ኢየሱስ ግን ብዙዎቻቸው በመንፈስ ሙታን እንደ ነበሩ ነግሮአቸው ነበር። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የነቁና ዝናን ያተረፉ ይመስሉ ነበር፤ ሐቁ ግን አብዛኛዎቹ በመንፈስ ሙታን ነበሩ። ምንም እንኳን በዚያች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው ያውቁ የነበሩ ጥቂቶች ሰዎች ቢሆኑም (ቁጥር 4)፤ አብዛኛዎቻቸው ድል መንሣት ያስፈለጋቸው፥ ስሞቻቸው ከሕይወት መጽሐፍ እንዳይደመሰሱ ነበር። በራእይ ከምዕራፍ 2–3 ድረስ ባሉት ክፍሎች «ድል የነሡት» የሚለው ቃል በተለይ የሚያመለክተው በእውነት ዳግም ለተወለዱ ክርስቲያኖች ነበር። እንዲያው ብቻ የተለያዩ መንፈሳውያን

የክርስቲያን ቡድኖች ለማመልከት ሳይሆን በጥቅም ላይ የዋለው፥ ዓላማው በእውነት ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ላወቁት ክፍሎች ነበር (ራእይ 2፡7፥ 11፥ 17፥ 26፤ 3፡5፥ 12፥ 21 ተመልከት)። ጌታ ኢየሱስ ድል የነሡ ስሞቻቸው ከሕይወት መጽሐፍ አይደመሰሱም ሲል ምን ማለቱ ነው? ከዳኑና በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ከተጻፉ በኋላ ያንን ደኅንነት ማጣት ይቻላል ማለቱ ነው? ኢየሱስ ከሕይወት መጽሐፍ ላይ ስለ መደምሰስ የሚናገረውን አሳብ ያገኘው ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ነው። ይህ ከሕይወት መጽሐፍ ላይ መደምሰስ የሚለው አሳብ፥ አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር አድርገው ነገር ግን በእውነት ከእነርሱ ጋር ያልሆኑትን የሚጠቁም ምሳሌያዊ አሳብ ነው። ዳዊትም በመዝሙር 69፡28 ላይ በውጫዊው ሁኔታዎች የእግዚአብሔር ሰዎች መስለው፥ በውስጣዊ ሕይወታቸው ግን ጨርሶ የእግዚአብሔር ወገኖች ስላልነበሩት ሲገልጽ፥ በተመሳሳይ ምሳሌያዊ ሃሳብ ተጠቅሞአል። በኦሪት ዘጸአት 32፡33 ደግሞ እግዚአብሔር፥ ከእስራኤል ጋር ከግብፅ ወጥተው የመጡና በውጪአቸው የእግዚአብሔር ሰዎች የሚመስሉ፥ በተቃራኒው ግን በውስጣቸው ራሳቸውን የእርሱ ያላደረጉትን ወገኖች ከመጽሐፉ እንደሚደመሰሳቸው ለሙሴ ነግሮት ነበር። በተመሳሳይ መንገድ፥ በሰርዴስ ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር ያመሳስሉ የነበሩ፥ ግን የእግዚአብሔር ሰዎች ያልሆኑ ነበሩ። በዚህ በሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ሰዎች በክርስቶስ አምነው እርሱን እንደ መድኃኒታቸው የተቀበሉ ለመሆናቸው ራሳቸውን እንዲመረምሩ እንጂ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል በመሆን ብቻ ራሳቸውን ከሌሎቹ ምእመናን ጋር በማመሳሰል ብቻ እንዳይኖሩ ያስጠነቅቃቸዋል።

ራእይ 3፡16 ስለ ተመሳሳይ እውነት ያስተምራል። በራእይ 3፡14-22 ውስጥም በአብዛኛው ከሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተመሳሳይ ለሆነችው ለሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያንም ኢየሱስ ይናገራል። በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ምእመናን በመንፈሳቸው የበለጸጉ ይመስላቸው ነበር። ነገር ግን እውነቱ፥ በመንፈሳቸው ድሆች፥ ዓይነ-ሥውራን እና የተራቆቱ ነበሩ (ቁጥር 17)። በመንፈሳቸው ሙቅ (ጋል ያሉ) ወይም ቀዝቃዛ (አርኪ) አልነበሩም። ያም ሆኖ ትዕቢተኞችና በራሳቸው የሚመኩ ስለነበሩ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ነገር እንደማያስፈልጋቸው አድርገው ያስቡ ነበር። ምንም እንኳን በውጪአቸው ቤተ ክርስቲያን ቢመስሉም፥ በውስጣቸው ግን እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን አልነበሩም። ፍላጎታቸውን ብቻ የሚያውቁ፤ ራሳቸውን ክርስቲያኖች ነን የሚሉና ራሳቸውን በትሕትና በጌታ ፊት የሚያቀርቡ፥ ጌታ ኢየሱስንም ወደ ልባቸውና ወደ ሕይወታቸው እንዲገባ የሚጋብዙ ናቸው (3፡20)። ጌታ ኢየሱስን ወደ ልባቸው ባይጠሩትና ድል አድራጊዎች ባይሆኑ ኖሮ፥ ሊድኑ አይችሉምና እግዚአብሔርም ይጥላቸው ነበር።

60ኛ ጥያቄ፡- እስቲ ትንሽ ቆም ብላችሁ ስለ ራሳችሁም ሕይወት አስቡ። ክርስቶስን በእውነት ተቀብላችሁ፥ አዳኛችሁ አድርጋችሁታል፥ ወይስ ራሳችሁን የቤተ ክርስቲያን አባል በማድረግ ብቻ በማስመሰል ትኖራላችሁ? ክርስቶስን በእውነት አምናችሁ በመቀበል መድኃኒታችሁ አድርጋችሁት ከሆነ፥ እግዚአብሔርን አመስግኑት፥ አወድሱት! በሌላ በኩል በውጫዊው በኩል ክርስቲያን በመምሰል ወደ

ቤተ ክርስቲያን የምትመላለሱ ከሆናችሁና በእውነት በክርስቶስ አምናችሁ እንደ አዳኛችሁ በማድረግ ያልተቀበላችሁት ከሆነ፥ ባለፈው ጊዜ ወደ አጠናችኋቸው አራት ትምህርቶች ተመለሱና አሰላስሉ። በመሆኑም አሁኑኑ ክርስቶስ አዳኛችሁ መሆኑን እመኑ!

4.3 ክርስቲያኖች ደኅንነታቸውን የሚያጡ የሚመስል ትምህርት የሚያቀርቡ አንዳንድ ክፍለ ምንባቦች የሚያስተምሩት ጽናት በእውነት የዳኑ ሰዎች ምልክት መሆኑን ነው።

61ኛ ጥያቄ፡– ቆላ. 1፡21–23 አንብብ። ሀ) የቆላስይስ ሰዎች ቀድሞ በምን አኳኋን ይኖሩ ነበር? (ቁጥር 21) ለ) እግዚአብሔር ምን አደረገላቸው? (ቁጥር 22) ሐ) የቆላስይስ ሰዎች በእውነት የታረቁ ለመሆናቸው ምስክሩ ምን ነበር? (ቁጥር 23)

62ኛ ጥያቄ፡– ማቴ. 24፡12–13 አንብብ። ሀ) በታላቁ መከራ ጊዜ በብዙዎች ላይ ምን ይደርሳል? ለ) እስከ መጨረሻው ድረስ የሚጸኑ ምን ይሆናሉ?

አንዳንድ ክርስቲያኖች ደኅንነታቸውን እንደሚያጡ ዓይነት የሚያስተምሩ ከፍለ ምንባቦች የሚያስተምሩት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ጽናትና ታማኝነት፥ በእውነት ዳግም የተወለዱትና የዳኑት ምልክት መሆኑን ነው።

በቆላስይስ 1፡21–23 ውስጥ ጳውሎስ፥ የቆላስይስ ሰዎች በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር ተለይተው እንደ ነበሩ ያስታውሳቸዋል። አሁን ግን ስለ ታረቁ በእግዚአብሔር ፊት ቅዱሳንና ጻድቃን ሆነው ቀርበዋል። ሆኖም በእርግጥ የታረቁ ለመሆናቸው እና ቅድስናንና ጽድቅን ለማግኘታቸው ማስረጃው ምንድን ነው? በእምነታቸው ይቀጥላሉ። በክርስትና ሕይወታቸው መጽናታቸው ራሱ ከእግዚአብሔር ጋር የመታረቅ ምልክታቸው ነው። ማስታወስ ያለባችሁ ጳውሎስ በእምነታቸው ቢቀጥሉ ይታረቃሉ አለማለቱን ነው። ሐዋርያው ያለው የቆላስይስ ሰዎች በእምነታቸው ቢቀጥሉ አስቀድመው ድነዋል ነው። ቁጥር 23 ለመዳን በእምነታቸው መቀጠል አለባቸው ሳይሆን የሚለው፤ በእምነት መጽናታቸው፥ እግዚአብሔር ያዳናቸው ለመሆኑ ማስረጃ ነው፥ ነው። በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ጽናት ሰውን አያድነውም፥ በመሠረቱ ጽናት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አንድ ሰው የመዳኑና በእውነት ዳግም የመወለዱ ምልክት ነው።

በማቴዎስ 24፡12–13 ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ተመሳሳይ አሳብ ያስተምረናል። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24–25 ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ወደፊት ሊመጣ ስላለው የመከራ ጊዜ ይናገራል። በሚመጣው የመከራ ጊዜ፥ ብዙ ክርስቲያኖች ነን ሲሉ የነበሩ ሰዎች ከክፋታቸውና የክርስቶስን ፍቅር በማጣታቸው ጌታን አለማወቃቸውን እንደሚገልጹ ጌታ ተናግሯል። ነገር ግን በክርስቶስ ታምነው የጸኑትና እርሱን የሚያውቁት ይድናሉ። በክርስቶስ ታምኖ መኖር ራሱ አንድ ሰው በእውነት የዳነ ለመሆኑ ምስክር ነው።

አምስተኛ ቀን

የሳምንቱን ትምህርት በመከለስ፥ ለሳምንቱ ስብሰባ ተዘጋጁ።

ሳምንታዊ የስብሰባ ጊዜ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ፡– መሪው ከዚህ ሳምንት ትምህርት ወይም ጥቅስ ላይ ወስዶ ከአምስት እስከ አሥር ደቂቃ የሚደርስ የጸሎት ዝግጅት ያድርግ።

2. ሳምንታዊ የጸሎት ጊዜ – የአሥር ደቂቃ ጊዜ ለጸሎት አውሉ። በተለይም እንደ ገና ለመወለድ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ለሚሹ ለምታውቋቸው ሰዎች ጸልዩ።

3. ከለሳ፡– በዚህ ሳምንት ውስጥ በተማራችኋቸው ትምህርቶች ውስጥ መልሳቸው አስቸጋሪ የነበሩ ጥያቄዎችንና እያንዳንዱ ተማሪ ስለ ተማረው ትምህርት ለማስተዋል፥ የአሥራ አምስት ደቂቃ ጊዜ ለክለሳ አውሉ።

4. ውይይት

4ሀ. የታመሙትን ወይም የተሠቃዩትን ሰዎች ለማጽናናት የክብርን ወይም የመከበርን እውነት እንዴት ትጠቀሙበታላችሁ? እንደዚሁም ስለ ሞት የሚፈሩትን፥ ወይም የሚወዱትን ሰው በሞት ያጡ ሰዎችን ለማጽናናት የክብርን (የመከበርን) እውነታ እንዴት ትጠቀሙበታላችሁ?

4ለ. ስለ አማኞች የዘላለማዊ ዋስትና ጉዳይ አንሥታችሁ ተወያዩ። እናንተ ወይም ሌሎች የተዋወቃችኋቸው ክርስቲያኖች የዘላለም ዋስትናን እውነታ ለመቀበል በምን ምክንያት ይከብዳቸዋል? በዚህ ሳምንት የተማራችሁት ትምህርት የዚህን ችግር ከፊሉን እንዴት ሊያስወግድላችሁ ይችላል?

4ሐ. የዘላለም ዋስትና አስተምህሮ እግዚአብሔርን በመፍራትና የተቀደሰ ሕይወትን ለመኖር እንዴት ሊቀሰቅሰን ይችላል?

4መ. «የዘላለም ዋስትና ሰዎችን ወደ ኃጢአት ይመራል» ለሚል ሰው ምን ትመልሳላችሁ?

4ሠ. ክርስቲያኖች ነን ሲሉ ቆይተው ወደ ኃጢአት ከወደቁ፥ እንዲሁም በክርስቶስ ላይ የነበራቸውን እምነት በመተው አዝማሚያ ላይ ካሉ ሰዎች ጋር እንዴት አድርገን እንወያያለን?

4ረ. ክርስቲያኖች ነን እያሉ ግን በእውነተኛው የክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ለማይኖሩ ሰዎች የሚጠቅም ምን የማስጠንቀቂያ መልእክቶችን በዚህ ትምህርት ውስጥ አገኛችሁ?

ትምህርት ሃያ

ደኅንነትን የመቀበል ጥያቄ

በትምህርት 16 ውስጥ፥ ክርስቶስ በመስቀል ላይና በትንሣኤው የሰጠንን ደኅንነት እንዴት ሰዎች በየግላቸው ሊያገኙ እንደሚችሉ ተምረን ነበር። በዚህም ለደኅንነት መሠረታዊ የሆነ አንድ ዋና ነገር፥ በሦስት የተለያዩ መንገዶች መገለጣቸውን ተመልክተናል። እነዚህም ሦስቱ ንስሐ፥ እምነትና ወደ እግዚአብሔር መመለስ ናቸው። ሰዎች ኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር ለይቶአቸው እንደ ነበረ መገንዘብና ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ በራሳቸው ሥራና በሌላም ነገር መታመን እንደሌለባቸው አውቀው፥ በአካያው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በሞቱና በትንሣኤ ብቻ ማመን አለባቸው። ስለዚህ በዚህ አኳኋን ሰዎች ከኃጢአታቸው በሚመለሱበትና ወደ ኢየሱስ ለደኅንነት በሚመጡበት ጊዜ፥ እግዚአብሔርም የደኅንነትን በረከቶች ይሰጣቸዋል። ይህንን አዳኝ የሆነ እውነተኛ እምነትን ያገኙ ሁሉ፥ ኢየሱስን የመከተልና የመታዘዝ የሕይወት ፈለግ ይኖራቸዋል። መልካም ሥራቸው የደኅንነታቸው ውጤትና ፍሬ ይሆናል።

ነገር ግን ሰዎች ደኅንነት እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ብዙ ጥያቄዎችን ይሰነዝራሉ። በዚህ ሳምንት ትምህርታችን ከእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ ጥቂቶችን ለመመለስ እንሞክራለን።

መጀመሪያ ቀን— እምነትና ጥምቀት

ክርስቲያኖች በክርስቶስ ያላቸውን እምነት በሰዎች መካከል ለመግለጥ ቢሹ፥ ሊያደርጉት የሚገባ አንዱና ዋናው ነገር፥ ቅዱስ ጥምቀትን መቀበል ነው። ምክንያቱም በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ ጥምቀትን እንዲቀበሉ ታዝዘዋል። በአዲስ ኪዳንም ውስጥ ቅዱስ ጥምቀት ከደኅንነት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ መሆኑን በመገንዘብ ደኅንነትን ለማግኘት መጠመቅ ነበረባቸው። በ16ኛው ትምህርት ውስጥ ለደኅንነት አስፈላጊ የሆነው አንዱ ዐቢይ ነገር በሦስት መንገዶች ተገልጧል። እነዚህም ሦስቱ መንገዶች፦ ንስሐ፥ እምነትና ወደ እግዚአብሔር መመለስ ናቸው። እንግዲህ የጥምቀት ሚና ምንድን ነው? ጥምቀት ለደኅንነት ግዳጅ በሁለተኛው ደረጃ ተፈላጊ ነገር መሆኑ ነው? ሰዎች እንደ መጀመሪያ የደኅንነት ክፍል አድርገው በማሰብ በክርስቶስ ይመኑና ከዚያ በኋላ እንደ ሁለተኛው የደኅንነት ክፍል ቅዱስ ጥምቀትን ይቀበሉ? በዛሬ ትምህርታችን ላይ ስለ ጥምቀት ስላሉዋችሁ ጥያቄዎች አንሥተን ሁሉንም በዝርዝር ልንወያይባቸው አንችልም። ሆኖም ቅዱስ ጥምቀት ደኅንነትን ለእኛ ለማስገኘት፥ ከንስሐና ከእምነት ጋር እንዴት ያለ ተዛምዶ እንዳለው፥ በሚነሡ ጥያቄዎች ላይ መልስ ለመስጠት እንጥራለን።

1. በአዲስ ኪዳን ውስጥ አማኞች በክርስቶስ እንዳመኑ ወዲያውኑ ያጠመቁ ነበር። ይህም ጥምቀት ውጫዊ ምልክትና የውስጣዊ እምነታቸው ማኅተም ነበር።

1ኛ ጥያቄ፡– ማቴ. 28፡19–20 አንብብ። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በምንሆንበት ጊዜ ምን ማድረግ ይኖርብናል?

2ኛ ጥያቄ፡– የሐዋ. ሥራ 2፡41 አንብብ። ጴጥሮስ በጴንጠቆስጤ ቀን በሰማው የምስክርነት ቃል ያመኑ ሰዎች ቃሉን መቀበላቸውን ለማሳየት ምን አደረገ?

3ኛ ጥያቄ፡– የሐዋ. ሥራ 8፡36–38 አንብብ። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በክርስቶስ ያመነ መሆኑን ለማረጋገጥ ምን ለማድረግ ፈለገ?

4ኛ ጥያቄ፡– የሐዋ. ሥራ 10፡47–48 አንብብ። ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ መች ተጠመቁ?

5ኛ ጥያቄ፡– የሐዋ. ሥራ 16፡14–15 አንብብ። ሊድያ መች ተጠመቀች?

6ኛ ጥያቄ፡– የሐዋ. ሥራ 16፡31–33 አንብቡ። ሀ) ሐዋርያው ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ወኅኒ ቤት ዘበኛ ደኅንነትን እንዲያገኝ ምን ማድረግ እንዳለበት ነገረው? ለ) የፊልጵስዩስ ወኅኒ ቤት ዘብ መች ተጠመቀ?

በጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ፥ በኢየሱስ ያመኑ ሰዎች ሁሉ፥ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መሆናቸውን ለማሳየት ወዲያውኑ ይጠመቁ ነበር። በማቴዎስ 28፡19–20 ላይ ኢየሱስ አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው ብዙ ደቀ መዛሙርትን እንዲያፈሩ አዝዞአቸው ነበር። ስለዚህ ሰዎች ኢየሱስን ለመከተል በሚወስኑበት ጊዜ የእርሱ ተከታዮች መሆናቸውን ለማስመስከር በመጀመሪያ የሚያደርጉት ነገር ቅዱስ ጥምቀትን መቀበል ነው። በጴንጠቆስጤ ቀን ሐዋርያው ጴጥሮስ ስብከቱን ለኢየሩሳሌም አይሁዶች ካሰማ በኋላ፥ በሐዋርያት ሥራ 2፡41 ላይ እንደተጻፈው፥ የሐዋርያውን መልእክት የተቀበሉ ሁሉ ተጠመቁ ይላል። በመሆኑም ኢየሱስን እንደ መሢሐቸውና ከኃጢአት እንደሚያድን መድኅን ከተቀበሉ በኋላ ሁሉም በአንድ ቀን ተጠመቁ። በሐዋርያት ሥራ 8፡26–38 ውስጥ ፊልጶስ በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 53 ውስጥ ስለ ክርስቶስ የተጻፈውን ቃል ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጋር ተወያየ። ወደ ውኃ በቀረቡ ጊዜም፥ ጃንደረባው በራሱ ፍላጎት ለመጠመቅ ጠየቀ። ጥምቀትን በመቀበል፥ በኢየሱስ የማመንና እርሱንም አዳኙ አድርጎ መቀበሉን ሕይወት አስመሰከረ። እግዚአብሔር የልድያንና የቤተሰቦችዋን ልብ እንደ ከፈተ፥ የኢየሱስ ተከታይ መሆንዋን ለማግለጥ ተጠመቀች (የሐዋ. ሥራ 16፡14–15)። ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት በሰበከ ጊዜና በኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ የኃጢአት ይቅርታ እንደሚያገኙ (የሐዋ. ሥራ 10፡43) ባብራራበት ወቅት ያዳምጡ በነበሩ ሰዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፥ (የሐዋ. ሥራ 10፡44)። ጴጥሮስም እነዚህ ሰዎች በልባቸው ክርስቶስን አምነው እንደ አዳኛቸው መቀበላቸውን ይህ ድርጊት ሊያረጋግጥለት ቻለ። እርሱም እነዚህ ሰዎች ምንም ቃል ሳይተነፍሱ ወዲያው እንዲጠመቁ አዘዘ።

ምናልባት አዲስ አማኞች በክርስቶስ እንዳመኑ ወዲያውኑ ይጠመቁ እንደ ነበረ ግልጽ ምሳሌ ሆኖ የሚጠቀሰው የሐዋርያት ሥራ 16፡31–33 ውስጥ ያለው ክፍል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ ከተማ በነበሩ ጊዜ ከአንዲት አገልጋይ ክነበረች ልጃገረድ ውስጥ ርኩስ መንፈስን ስላስወጡ

ታስረው ነበር። በሌሊትም እግዚአብሔር የምድር መንቀጥቀጥ እንዲሆን አደረገ፥ የታሰሩበት ሰንሰለትም ተፈታ፥ የእስር ቤቱ በርም ተከፈተ። የወኅኒ ቤቱ ዘብ በሩ መከፈቱን ባወቀ ጊዜ ራሱን ሊገድል ነበር። ይህን ያደረገበት ምክንያት እስረኞቹ ሁሉ ያመለጡ ስለ መሰለውና እርሱም በእነርሱ ገመድ እንደሚገባ ስለ ተሰማው ነው። ጳውሎስ ግን ድምፁን ከፍ አድርጎ እስረኞቹ ሁሉ በእስር ቤቱ ውስጥ መሆናቸውን ነገረው። የእስር ቤቱ ዘብ ይህን ጊዜ በደስታ ተውጦ ወደ ጳውሎስ በመምጣት፥ «ለመዳን ምን ማድረግ ይገባኛል?» ሲል ጠየቃቸው? ሐዋርያው ጳውሎስ ሰውዬው ለሚድንበት ሁኔታ ብዙ ነገር ለመዘርዘር አልፈለገም። አንድ ነገር ብቻ እንዲያደርግ መከረው፥ ይህም፥ «በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እመን።» በዚያን ምሽት የወኅኒ ቤት ዘበኛው ጳውሎስንንና ሲላስን ሊያስተናግድ ወደ ቤቱ ይዟቸው በሄደ ጊዜ ሐዋርያው ጳውሎስ እርሱንና ያመኑትን ቤተሰቦቹን አጠመቃቸው።

ይህ ታሪክ በሦስት ምክንያቶች ጠቃሚ ሆኖ ይገኛል። መጀመሪያ፥ ጳውሎስ ለደኅንነት ይበጃል ብሎ የተናገረው አንድ አስፈላጊ ነገር ነበር። እርሱም እምነት ነው። ሐዋርያው፥ የወኅኒው ጠባቂ ለመዳን መጠመቅ አለበት አላለም። ይህ እንግዲህ በትምህርት 16 ውስጥ የተማርነውን ያሳስበናል። ይህም ለደኅንነት አስፈላጊ የሆኑት ንስሐና እምነት ናቸው የሚለው ነው። ሁለተኛው ደግሞ፥ ምንም እንኳን በእምነታቸው ብቻ ድነው ቢሆኑም፥ ጳውሎስ የወኅኒ ቤቱን ዘበኛና ቤተሰቡን ወዲያው አጠመቃቸው። የአዲሱ እምነታቸው ውጪአዊ መገለጫ ጥምቀታቸው ነበር። ሦስተኛ፥ ዘበኛውና ቤተሰቡ ስለ አዲሱ እምነታቸው የሚያውቁት ጥቂት ቢሆንም ተጠመቁ። መሬት እስከ ተንቀጠቀጠበት ጊዜ ድረስ፥ የጥንታዊ ግሪክና የሮማ ጣዖታት ተከታዮች ነበሩ። ስለ ኢየሱስ የሚያውቁት ጥቂት ነበር። ስለ ብሉይ ኪዳን የአይሁድ እምነትም ግንዛቤአቸው አናሳ ነበር። የገባቸውና ያወቁት ኢየሱስ የደኅንነት መንገድ መሆኑን ስለነበረ፥ በእርሱ አመኑ። እምነታቸውንም ስለ ገለጡ ጳውሎስ ሊያጠምቃቸው ቻለ።

እነዚህ ቁጥሮች በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥምቀት የነበረውን ሚና እንድንረዳ ይረዱናል፥ ጥምቀት የውስጣዊው እምነት ውጫዊ መገለጫ (አዋጅ) ነው። ሰዎች ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው፡ ሲያምኑት፥ አሁን ክርስቶስን እንደሚያምኑና እንደሚከተሉ ለሰው ሁሉ ለማወጅ ይጠመቁ ነበር። ጥምቀት ወደ ደኅንነት የሚወስዳቸው መንገድ አልነበረም። ይልቁንም የደኅንነት መንገዶቻቸው ንስሐና እምነት ነበሩ። ነገር ግን ጥምቀት ሊሆን የተገባውና አፋጣኝ የሆነ የውስጣዊው እምነት ውጫዊ መገለጫ ነበር። ጥምቀት ውስጣዊውን እምነት ለሌሎች ለማሳየት የሚጠቅም ውጫዊ ሥርዓት ነበር። አንድ ሰው ባይጠመቅ እንዳላመነ ይቆጠር ነበር። አንድ ሰው ንስሐ ቢገባና ቢያምን ውስጣዊ እምነቱን ሊመሰክር እንደ ውጫዊ ምልክት አድርጎ በፍጥነት ይጠመቅ ነበር።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ጥምቀትን፥ የውስጣዊ እምነት ምልክትና ማጎተም ነው ይላሉ። አንድ ሰው እምነት ያለው ለመሆኑ፥ ጥምቀት ለሌሎች ምልክቱ ነው። እንደዚሁም ጥምቀት ይህንኑ እምነት

የሚያረጋግጥ ማኅተም ነው። ጥምቀት ለጥንት ቤተ ክርስቲያን ምን እንደ ነበረ አንድ ምሳሌ እነሆ፦ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚደረጉ የሠርግ ሥነ ሥርዓቶች ውስጥ አንዱ የቀለበት ሥነ ሥርዓት ነው። ሙሽራውና ሙሽራዋ የቃል ኪዳናቸው ምልክትና ማኅተም አድርገው ቀለበት ይለዋወጣሉ። በሕይወት ዘመናቸውም ቀለበቶቻቸውን እንደ ጋብቻ ቃል ኪዳን ምልክትና ማኅተም አድርገው፥ አንዳቸው የሌላው መሆናቸውን ለማሳየት በጣቶቻቸው ላይ እንዳጠለቋቸው ይኖራሉ።

ሰዎች ያለ ቀለበት ሥነ ሥርዓት ሊጋቡ ይችላሉ? አዎን፥ ሊጋቡ ይችላሉ። ነገር ግን ይህ የቀለበት ሥነ ሥርዓት፥ የጋብቻ ዋና የውጪአዊ ምልክትና እንዲሁም ሙሽሮቹ እርስ በርስ ለሚያደርጉት የቃል ኪዳን ማኅተም ነው። ሙሽሪትና ሙሽራው እርሱም የእርሷ እርሷም የእርሱ ለመሆናቸው የሚያሳዩበት ምልክት የቀለበት ማድረግ ሥነ ሥርዓት ስለሆነና ይህ ድርጊት ተለምዶ በመካሄድ ላይ በመሆኑ ሙሽራው ወይም ሙሽራይቱ አንዳቸው ቀለበት አናደርግም ቢሉ ምን ያህል አስከፊ ድርጊት እንደሚሆን ልትገምቱ ትችላላችሁ። እንደዚሁም፥ ሙሽራው ወይም ሙሽሪት አንዳቸው በሥነ-ሥርዓቱ ላይ ቀለበት አናደርግም ቢሉ ጋብቻቸው ከልብ ስለ መሆኑ የታደሙት ሰዎች ይጠራጠራሉ። በዚሁ አኳኋን በአዲስ ኪዳን ጊዜ የነበሩ አማኞች አንድ ሰው ካልተጠመቀ በስተቀር ራሱን ለክርስቶስ በእውነት አሳልፎ ሰጥቷል ብለው አይቀበሉም ነበር። ካለ ጥምቀት በስተቀር አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ የእርሱ ተከታይ መሆኑ ማረጋገጫ አልነበረም። *ለአዲስ ኪዳን አማኞች ጥምቀት የእምነት ክፍል ነበር።* የውጪአዊ ምልክትና የውስጣዊ እምነት ማኅተም ነበር። ከዚህ የተነሣ ነው፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ክፍለ ምንባቦች ጥምቀት ከእምነት ጋር በቅርብ የተጣመረው። የአዲስ ኪዳን አማኞች ጥምቀት የደኅንነታቸው መንገድ እንደ ነበረ አድርገው አልተገነዘቡም። እንደ እነርሱ ግንዛቤ እምነት ብቻ የደኅንነታቸው መንገድ ነበር (ማለትም በ16ኛው ትምህርት ውስጥ እንደ ተመለከትነው)። ነገር ግን ሰዎች በውጪአዊው ሁኔታ እምነታቸውን በጥምቀት ሳያሳውቁና ሳያሳዩ፥ በልባቸው ውስጥ በክርስቶስ ሊያምኑ እንደሚችሉ ምንም ግንዛቤ አልነበራቸውም።

2. ጥምቀት ለደኅንነት አስፈላጊ መሆኑን የሚያስተምሩ የሚመስሉ የጥቅስ ክፍሎች፥ ጥምቀት መከናወኑ ለውጪአዊ ምልክት ለውስጣዊው ደግሞ ማኅተም መሆኑን ያመለክታል።

7ኛ ጥያቄ፦ ማር. 16፡15–16 አንብብ። ሀ) የሚድነው ማን ነው? ለ) የሚኮነንስ ማን ነው?

8ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ጴጥ. 3፡21 አንብብ። ሀ) ጴጥሮስ ምን ያድናል አለ? ለ) ጴጥሮስ ይህ አይደለም ያለው ምንድን ነው? ሐ) ጴጥሮስ ይህ ነው ያለው ምን ነው?

9ኛ ጥያቄ፦ የሐዋ. ሥራ 2፡28 አንብብ። ጴጥሮስ ኢየሱስን የሰቀሉ አይሁዶች የኃጢአት ይቅርታን ለማግኘት ምን ያደርጉ አለ?

ጥምቀት የደኅንነትን ማኅኛ መንገድ እንደሆነ የሚመስሉ ብዙ ክፍሎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ። ሆኖም እነዚህን ክፍለ ምንባቦች በጥንቃቄ በዚህ እምነት ከተመለከትናቸው ትምህርቶች አኳያ በጥንቃቄ በምናጠናቸው ጊዜ፥ ሰዎች በመጠመቃቸው ብቻ ይድናሉ አለማለታቸውን እንገነዘባለን። በዚህ ፈንታ እነዚህ የጥቅስ ክፍሎች የሚያሳዩት የጥንት አማኞች ጥምቀትን ከንስሐና ከእምነት ጋር ያያይዙት እንደ ነበረ ነው። እነዚህ የጥቅስ ክፍሎች የሚያመለክቱት የጥንት አማኞች በውስጡ በልቡ በክርስቶስ ያመነ ሰው ወዲያውኑ በመጠመቅ እምነቱን ለሌሎች እንዲገልጥ ይፈልጉ ነበር።

በማርቆስ 16፡15–16 ውስጥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ወንጌልን እንዲሰብኩ አዝዟቸዋል። በዚህ ትእዛዝም ላይ ያመኑ የተጠመቁ ይድናሉ ብሏል። ስለዚህ የእርሱ ፈቃድ ያመኑ ሁሉ ወዲያውኑ እንዲጠመቁ ነው። በአንጻሩ ደግሞ የማያምኑ እንደሚኮነኑ ተናግሮአል። ማስተዋል ያለባችሁ ያልተጠመቁ ይኮነናሉ አለማለቱን ነው። ሰውን የሚያስኮንነው አለማመኑ ነው። ኢየሱስ በምን ምክንያት ነው፥ ሰው ለመዳን «አምኖ መጠመቅ አለበት» ያለው? መጠመቅ የውስጣዊ እምነት ምልክትና ማኅተም ነው። ያመኑ ሁሉ እንደ እምነታቸው ክፍል መጠመቅ እንዳለባቸው ይጠበቅ ነበር። ይህን ጥቅስ እንድንገነዘበው አንድ ማብራሪያ እነሆ፡– እኔ እናንተ ካላችሁበት ከተማ ተነሥቼ ወደ አዋሳ እንደምሄድ አድርጋችሁ ገምቱ። ወደ አውቶቡስ ጣቢያ ወስዳችሁ እንዲህ ትሉኛላችሁ፥ «አውቶቡስን ተሳፈርና ቁጭ በል፥ ዛሬውኑ አዋሳ ትገባለህ። በዚህ አውቶቡስ ላይ ባትሳፈር ግን ዛሬ አዋሳ ልትገባ አትችልም።» ታዲያ ይህን አውቶቡሱን ባልሳፈር ምን እሆናለሁ? አዋሳ አልደርስም። ወደ አውቶቡሱ ውስጥ ገብቼ ብቀመጥስ ምን ይሆናል? በዚያኑ ቀን አዋሳ እደርሳለሁ? ወደ አውቶቡስ ገብቼ ባልቀመጥ ምን እሆናለሁ? ይህን ባደርግ ከሞኝነት ይቆጠርብኛል። አይደለም? ወደ አዋሳ የሚሄድ አውቶቡስ ተሳፍሮ ሳይቀመጡ በዚያ ሁሉ ጉዞ ላይ ቆሞ አዋሳ መድረስ ከሞኝነትም ሞኝነት ነው። አውቶቡስ ተሳፍሮ ቁጭ ማለት የተለመደ ድርጊት ነው። በማርቆስ 16፡16 ውስጥ የተጠቀሰው ቃል ይህ አሁን የጠቀስነውን ምሳሌ ይመስላል። አውቶቡስ ተሳፍሮ መቀመጥ፥ በማመንና አምኖ በመጠመቅ ይመሰላል። በዚሁ ረገድ አውቶቡስን ተሳፍሮ መጓዝ የመቀመጥ ድርጊት ክፍል ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ጥምቀት ኢየሱስን የማመን ክፍል ወይም ድርጊት ነው። ቀጥሎም አውቶቡሱን አለመሳፈሬ ወደ አዋሳ ሊያደርሰኝ እንደማይችል ሁሉ፥ እንዲሁም አንድ ሰው በኢየሱስ አላመነም ማለት ይህ ሰው ይኮነናል ማለት ነው። ማርቆስ 16፡16 እንደሚናገረው፣ ጥምቀት ከኢየሱስ ተከታዮች የሚጠበቅ የውጪአዊ ምልክትና የውስጣዊ እምነት ማኅተም ነው።

1ኛ ጴጥሮስ 3፡21 ተመሳሳይ ጥቅስ ነው። ጴጥሮስ ለአንባቢያኑ ሲናገር፥ «ጥምቀት አሁን ያድነናል» ይላል። ስለዚህ እነዚህን ቃላት በየራሳቸው ብናነባቸው፥ በቀላሉ መጠመቅ በራሱ ብቻ ያድነናል ብለን እናስብ ይሆናል። እዚህ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቂት ቃላትን አውጥቶ ብቻ ከሌሎች የጥቅስ አሳብ ጋር ሳያስተያዩና ሳያብላሉ ማንበብ ሁልጊዜም ቢሆን ስሕተት ነው። ጴጥሮስ «ጥምቀት አሁን ያድነናል» ሲል የተናገረውን ወዲያውኑ

ሲያብራራ፥ «የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም» ብሏል። ሰዎች በውኃ ውስጥ ጠልቀው በመጠመቅ፥ ወይም በራሳቸው ላይ ውኃ በማፍሰስ ብቻ ይድናሉ አላለም። ጨምሮ ሲያስገነዝብ፥ «ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው» ይላል። እንግዲህ የልባችንና የአእምሮአችን (ማለትም የሕሊናችን) ውስጣዊው ለውጥ ነው የሚያድነን። ሆኖም ለጴጥሮስና ለሌሎችም አማኞች በአዲስ ኪዳን ጊዜ ለነበሩት ሁሉ፥ «እግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና» የመጣው በዚያኑ በሚጠመቁበት ጊዜ ነበር። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንደተመለከትነው፥ ሰዎች ክርስቶስ አዳኛቸው መሆኑን እንዳመኑ ወዲያውኑ ይጠመቁ ነበር። በውኃ የሆነ ሥነ ሥርዓት ሊያድን እንደማይችል ጴጥሮስ በግልጽ ተናግሮአል። ነገር ግን መታወስ ያለበት ሐዋርያው ይህን ሲናገር፥ አያያዙም የበጎ ሕሊና ልመና ያለው ሁሉ ከዚሁ ጋር ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ መጠመቅ እንዳለበት ማሳሰቡ አልቀረም።

ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ውስጥ ያለውን ስብከቱን ባሰማ ጊዜ፥ ለአዳመጡት ሰዎች ይህንኑ የመሰለ ቃል ተናግሮአል። የሰሙትም ሰዎች ኢየሱስን የመስቀላቸው ኃጢአት በተሰማቸው ጊዜ ጮኸው፥ «ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ?» (የሐዋ. ሥራ 2፡37) ሲሉ ጠየቁ። ጴጥሮስም መልሶ፥ «ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ» አላቸው። ይህ የሐዋርያው አነጋገር፥ ሰዎች የኃጢአታቸውን ይቅርታ ለማግኘት መጠመቅ ያለባቸው የሚመስል ትምህርት ሊሆን ይችላል። በጥንቱ ግሪክ ትርጉም ስለዚህ ጥቅስ፥ «ሁላችሁም ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይላችኋል፥ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፥ እያንዳንዳችሁም ተጠመቁ» የሚል ነው። በጥንቱ ግሪክ ላይ ንስሐ ከኃጢአት ስርየትና መንፈስ ቅዱስን ከመቀበል ጋር በቅርብ የተያያዘ ሊሆን፥ ጥምቀት ግን ለየት ያለ አሳብ ሆኖ ተገልጾአል። ጴጥሮስ የኃጢአት ይቅርታን እንዲቀበሉ ይጠመቁ አይልም። ነገር ግን እንዲጠመቁ ያዝዛቸዋል። እንግዲህ እነዚሁ ሰዎች ነበሩ ከሰባት ሳምንታት በፊት በጴንጤናዊ ጲላጦስ ፊት ኢየሱስን «ስቀለው» እያሉ ይጮኹ የነበሩት። ስለ ሠሩት ኃጢአት አሳባቸውንም ሆነ ልባቸውን እንዲለውጡ ብቻ ሳይሆን፥ ንስሐ መግባታቸውን በኢየሱስ ስም በመጠመቅ ኢየሱስን እንደ መሢሕና እንደ አዳኛቸው አድርገው መቀበላቸውን በዚህ ውጪአዊ ድርጊት ማሳየት ነበረባቸው።

ጥምቀት የውስጣዊ እምነት ውጫዊ ምልክትና ማኅተም ነው። ክርስቲያን የመሆን ሁለተኛው ደረጃ አይደለም። እያንዳንዱ ክርስቲያን እንዲህ በማለት ሊገልጸውና ሊያሳውቅ የሚገባው፣ «ለደኅንነቴ ኢየሱስን ብቻ አምናለሁ። እንደ ሕይወቴ ጌታ፥ እርሱን ብቻ እከተላለሁ» የሚለውን ነው።

3. ውጪአዊው የንስሐ ሁኔታ፥ ሁልጊዜ በውስጣዊው እምነት ሊታጀብ ይገባል።

10ኛ ጥያቄ፡– ሮሜ 10፡9–10 አንብብ። ለመዳን ምን እናድርግ?

ሮሜ 10፡9–10 ያለው ክፍል በግልጽ ስለ ጥምቀት አይናገርም። ነገር ግን ስለ ውስጣዊ እምነትና ስለ ውጫዊ ምስክርነት የሚናገር አስደናቂ ክፍል ነው። ጳውሎስ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን እንዳስነሣው ብናምን፥ እንደዚሁም፥ እርሱ ጌታ እንደሆነ በአፋችን ብንመሰክር እንድናለን ይላል። በልባችን ማመን ሲባል እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት እንዳነሣውና በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ እንደምንድን ማመን ነው። ኢየሱስ ጌታ መሆኑን በአፋችን መመስከር ማለት ኢየሱስ ሁሉን ቻይ የሆነ የዓለም ሁሉ ጌታ ስለሆነ በሕይወታችን ውስጥ ልናመልከውና ልንታዘዘው እንደሚገባ ለሁሉ በይፋ ማሳወቅ ማለት ነው። ጳውሎስ ውስጣዊውን እምነት በአፍ ከመመስከር ሁኔታ አልለየውም። ሁለቱም እንደሚፈጸም ያምናል። በእውነት ንስሐ ገብተው በልባቸውና በአሳባቸው ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው የሚቀበሉ ሁሉ በይፋ በአፋቸው መመስከር ይገባቸዋል። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንደተመለከትነው፥ እግዚአብሔር እያንዳንዱ አማኝ ይህን ምስክርነት በጥምቀት እንዲያረጋግጠው ይፈልጋል።

> 11ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በዛሬው ትምህርታችን ላይ አዲስ ኪዳን በጥምቀትና በእምነት መካከል ስላለው ግንኙነት የለጠው ማብራሪያ፥ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ካሉ አብዛኛዎቹ ምእመናን ግንዛቤ ጋር ምን ያህል ይስማማል? ደግሞስ ይቃረናል? ለ) ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የእምነትና የጥምቀት አስተሳሰብ፥ እንዴት ታብራሩታላችሁ?

ዛሬ ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ስለ ጥምቀት የተመዛዘነ አስተሳሰብ የላቸውም። አንዳንዶች እንደሚያምኑት፥ በመጠመቃቸው ብቻ የኃጢአት ይቅርታን የሚያገኙ ይመስላቸዋል። ነገር ግን የጥምቀት ሥነ–ሥርዓት ማንንም ክርስቲያን አያደርግም። እንዲሁም የጥምቀት ሥነ ሥርዓት የማንንም ኃጢአት ሊያስተሰርይ አይችልም። ደኅንነትና የኃጢአት ይቅርታ የሚገኘው ንስሐ በመግባትና በእምነት ብቻ እንጂ በመልካም ሥራ አይደለም። ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ ለጥምቀት ጨርሶ ክብደት አይሰጡትም። ጥምቀት ክርስቲያኖች ከዳኑ በኋላ በገዛ ፈቃዳቸው የሚፈጽሙት ሥነ ሥርዓት ነው እስከ ማለት ይደርሳሉ። ይህን በማድረግም፥ ሰዎች በውስጣቸው ስለ ክርስቶስ እምነት ካላቸው፥ ስለ ጥምቀት ይህን ያህል ሊጨነቁበት አይገባም የሚል ትምህርት የሚያስፋፉ ይመስላሉ። ነገር ግን ዛሬ እንደተመለከትነው፥ የአዲስ ኪዳን ትምህርት እንደዚህ ወሰን የዘለለ አስተሳሰብ አይደለም። በመሆኑም ወደ ደኅንነት የመድረሻው መንገድ ንስሐና እምነት ብቻ ነው። ሆኖም አዲስ ኪዳን ጥምቀትን፥ የውስጣዊ እምነት ውጫዊ ምልክትና ማኅተም እንደሆነ አድርጎ ይመለከተዋል። አማኞች የሆኑ ሁሉ፥ ለመላው ዓለም እምነታቸውን የሚያሳውቁት በጥምቀት አማካይነት ነው።

ሁለተኛ ቀን– ሌሎች ጥያቄዎች

በዚህ ሳምንት ደኅንነት ስለ መቀበል ስለሚነሡ አስቸጋሪ ጥያቄዎች እናጠናለን። በትናንትናው ዕለት በእምነትና በጥምቀት መካከል ስላለው ግንኙነት መርምርን ነበር። ዛሬ ደግሞ ደኅንነትን በሚመለከት ስለሚነሡ ሦስት ጥያቄዎች እንወያያለን።

1. ቅዱስ ቁርባንን መቀበል፥ ደኅንነት ያስገኛል?

12ኛ ጥያቄ፡- ዮሐ. 6፡53-54 አንብብ። ሀ) ጌታ ኢየሱስ፥ አንድ ሰው ሕይወትን ማግኘት ከፈለገ ምን ያድርግ ይላል? ለ) ጌታ ኢየሱስ አንድ ሰው ሥጋውን ቢበላና ደሙን ቢጠጣ ምንን ያገኛል አለ?

13ኛ ጥያቄ፡- ዮሐ. 6፡35 አንብብ። ጌታ ኢየሱስ አንድ ሰው እንዳይራብ ወይም እንዳይጠማ ምን ያድርግ አለ?

ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ ተቀብለው ለመዳን ሲሉ ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ይፈልጋሉ። ሌሎች ደግሞ ካልቆረቡ በስተቀር ሊድኑ እንደማይችሉ ይሰማቸዋል። የተቀሩት ሰዎች ደግሞ፥ የቅዱስ ቁርባን ተካፋዮች በመሆን የእግዚአብሔርን ጸጋ በመቀበል መዳናቸውን እንደሚያረጋግጡ ያምናሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እነዚህ ሰዎች በቅዱስ ቁርባን ላይ መሳተፍ በዮሐንስ 6፡53-54 ውስጥ እንደተጻፈው የእግዚአብሔርን የማዳን ጸጋ የሚያሰጣቸው መሆኑን ለአሳባቸው ድጋፍ አድርገው ያቀርባሉ። በዚህ ክፍል ኢየሱስ የሚናገረው፥ ሰዎች «ሥጋውን በልተው፥ ደሙን የሚጠጡት» ሕይወትን ለማግኘት ስለሆነ፥ ማንም ሰው ሥጋውን የሚበላና ደሙን የሚጠጣ ሁሉ የዘላለም ሕይወትን ያገኛል። ለአንዳንድ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ስለ ቅዱስ ቁርባን የተናገረ ይመስላቸዋል። በመጀመሪያ ጊዜ፥ ኢየሱስ ቅዱስ ቁርባንን ለደቀ መዛሙርቱ በሰጠ ጊዜ፥ «ይህ ለእናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ ነው። ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰሰው ደሜ የሚፈጸም አዲስ ኪዳን ነው» አላለምን? (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡24-25። እነዚህ ሰዎች በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ጎብስቱን መብላትና ከጽዋው መጠጣት የዘላለምን ሕይወት የሚሰጣቸው አድርጎ ኢየሱስ የተናገረ አድርገው ያምናሉ።

ሆኖም፣ ደቀ መዛሙርቱ ሥጋውን እንዲበሉና ደሙንም እንዲጠጡ ኢየሱስ ሲነግራቸው ምን ማለቱ እንደሆነ በጣም የተሻለ ማብራሪያ አለ። በዮሐንስ 6፡53-54 ውስጥ ኢየሱስ ስለ ጎብስት ከአይሁዶች ጋር ያደረገው ረጅም ውይይት ከፊሉ ይገኛል። የመጽሐፍ ቅዱስን አንድ ክፍለ ምንባብ ትርጉም የመተንተን የመጀመሪያውና እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነው መመሪያ፥ የክፍለ ምንባቡን ጭብጥና ይዘት ማጥናት ነው። ኢየሱስ በዮሐንስ 6፡52-53 ውስጥ ስለተናገረው ጥቅስ ትርጉም ለመተንተን የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 መላውን ክፍል ማጥናት ይገባናል። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 በመጀመሪያዎቹ ጥቅሶች ላይ ኢየሱስ አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣዎችን ለአምስት ሺህ ሰዎች እንደ መገበ እንገነዘባለን። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሕዝቡን ተለይቶ ሄደ። ወዲያው ግን አገኙት (ዮሐንስ 6፡25)። ሕዝቡ ኢየሱስን ባገኙት ጊዜ፥ እንጀራ ስላበላቸው የፈለጉት መሆናቸውን ነገራቸው። ቀጥሎም፥ ለሚጠፋ ምግብ አትሥሩ፥ የዘላለም ለሚሆን ምግብ ሥሩ አላቸው (ዮሐንስ 26፡27)። ነገር ግን አይሁዶቹ በሥጋዊ ምግብ ፍላጎት ስላየለባቸው፥ ኢየሱስ እነርሱን ለመመገብ ሌላ ተአምር እንዲፈጽም ጠየቁት (ዮሐ. 6፡31-32)። ከዘላለም ሕይወት ይልቅ ምግብን አስበልጠው ስላዩ፥ እርሱ ከሰጣቸው ሥጋዊ ምግብ ይልቅ እርሱን እንዲሹ አሳሰባቸው። እውነተኛ የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የመጣው መሆኑን ነገራቸው (ዮሐ.

6፡33)። ሰዎቹ ግን አሁንም ኢየሱስ ስለ ዓለማዊ እንጀራ የሚናገር መሰላቸው። ይህን እንጀራ እንዲሰጣቸው ጠየቁት (ዮሐ. 6፡34)። በጣም ጠቃሚ በሆነ ጥቅስ አማካይነት ኢየሱስ ስለሚናገረው በትክክል ያስገነዝባቸዋል። በዮሐንስ 6፡35 ውስጥ ኢየሱስ ራሱ ከሰማይ የመጣ እንጀራ መሆኑንና ወደ እርሱ የሚመጣ ጨርሶ እንደማይራብ፥ የሚያምንበትም የማይጠማ መሆኑን ይነግራቸዋል። ኢየሱስ የመንፈስን ምግብና መጠጥ የማግኘቱ መንገድ ወደ እርሱ ዘንድ መምጣትና በእርሱ ማመን መሆኑን በማስረዳት፥ ወደ እርሱ ዘንድ ቢመጡ እርሱ ከሰማይ የሞጣ እንጀራ ስለሆነ በፍጹም የማይራቡና በመንፈስም የማይጠሙ መሆናቸውን አስገንዝቦአቸዋል። ኢየሱስ ከሰማይ ስለ መምጣቱ በተናገረ ጊዜ አይሁዶች አጉረመረሙ (ቁጥር 41–42)። ምክንያቱም እርሱ የተናገረው ቃል አልገባቸውም ነበር። ኢየሱስ በመመገብ ሥጋዊ ፍላጎታቸውን የፈጸመላቸው፥ መንፈሳዊ ትምህርትን ሊያስተምራቸው እንደነበረ አልገባቸውም ነበር። ኢየሱስም አያይዞ፥ ሰዎች ሊመጡበት የሚገባ ከሰማይ የመጣ እንጀራ መሆኑን ስለ ራሱ ተናገረ (ዮሐ. 6፡50–51)። ሰዎች ሥጋውን እንዲበሉና ደሙን እንዲጠጡ ሲናገራቸው (ዮሐ. 6፡53–54)፥ በቁጥር 32 ውስጥ በተናገረው ስልት ዓይነት ነበር አሳቡን የገለጸው። ኢየሱስ ሊናገር የፈለገውን የአነጋገር ስልትና ምሥጢር ቁጥር 35 ውስጥ ትርጉሙን አብራርቶታል። ሥጋውን መብላትና ደሙን የመጠጣት ምሥጢር ወደ ኢየሱስ የመምጣትና በእርሱ የማመን ምሥጢር ነው። ኢየሱስ ለአይሁዶች ሲናገር፥ የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ቢሹ ወደ እርሱ ዘንድ መጥተው በእርሱ ማመን እንዳለባቸው አሳስቦአቸዋል።

ቅዱስ ቁርባን በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነ ሥነ ሥርዓት ነው። ቅዱስ የሆነ የአምልኮ ጊዜ ነው። በዚህን ጊዜ አማኙ ኃጢአቱን ይናዘዛል፥ የክርስቶስን ሞት ያስባል፥ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ምእመናን ጋር ይገናኛል። ደግሞም ኢየሱስ ደኅንነትን ሊሰጠው ስለ ፈጸመው ሁሉ ምሥጋና ያቀርባል፥ እርሱንም ያመልካል። ሆኖም ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ማንንም ሊያድን ወይም የዘላለም ሕይወትን ሊሰጥ አይችልም። የዘላለምን ሕይወት የምናገኘው፥ ወደ ኢየሱስ ዘንድ በእምነት በመምጣት ነው። ይህንንም ራሱ በዮሐንስ 6፡35 ውስጥ ተናግሮአል።

2. የሚሞቱ ሕፃናት ይድናሉ?

ሕፃናት በሚሞቱበት ጊዜ የሚድኑ ወይም የማይድኑ ስለመሆናቸው ብዙ ሰዎች ጥያቄዎችን ይሰነዝራሉ። ይህ ጥያቄ ሕፃናት ለሚሞቱባቸው ክርስቲያን ለሆኑ ወላጆች በተለይ ጠቃሚ ነው። ሕፃናት የሚሞቱባቸው ወላጆች በጣም ያዝናሉ። ከዚህም በላይ የሚያስጨንቃቸው ጥያቄ፡– «ልጄን በሰማይ አገኘዋለሁን?» የሚለው ነው።

የሚሞቱ ሕፃናት በቀጥታ ወደ ሰማይ ይሂዱ ወይም ይቅሩ መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ መልስ አይሰጥም። ሆኖም፣ ለዚህ ጥያቄ መልስ እንድናገኝ የሚረዱን ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አሉ።

14ኛ ጥያቄ፡– ሀ) 2ኛ ሳሙ. 12፡22–23 አንብብ። ሀ) ዳዊት ሕፃኑ ከሞተ በኋላ ምን ግጽናኛ አገኘ? ለ) መዝሙር 23፡6 አንብብ። ዳዊት ለዘላለም የት እንደሚኖር ይገነዘብ ነበር?

15ኛ ጥያቄ፡– ማር. 10፡13–16 አንብብ። ሀ) ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንግሥት የማን ነው አለ? ለ) ሕፃናትን ወደ ኢየሱስ ባመጡ ጊዜ ምን አደረገላቸው?

16ኛ ጥያቄ፡– ማቴ. 18፡1–4 አንብብ። ሀ) በእግዚአብሔር መንግሥት ታላቁ ማን ነው? ለ) ማቴዎስ 18፡10–14 አንብብ። እነዚህ ትንንሽ ልጆች በሰማይ ምን ያገኛሉ? (ቁጥር 11) ሐ) እግዚአብሔር ስለ ትንንሽ ልጆች ያለው ስሜት እንዴት ነው (ቁጥር 14)?

በ2ኛ ሳሙ. ምዕራፍ 12 ውስጥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር በማመንዘርና አርዮንን በማስገደል፥ ስለ ሠራው የከፋ ኃጢአት ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ ዘንድ ቀርቦ ነገረው። ዳዊትም ወዲያው ጥፋቱን በኑዛዜ አስታወቀ (ቁጥር 13)። ሆኖም ናታን ዳዊት ለፈጸመው ኃጢአት ተግሣጽ ይሆን ዘንድ ከቤርሳቤህ የተወለደው ሕፃን እንደሚሞት አረዳው። ዳዊትም እግዚአብሔር ምሕረት አድርጎለት ልጁን ከሞት እንዲያተርፍለት በማሰብ በጾምና በጸሎት ራሱን አስገዛ። ግን በሰባተኛው ቀን ሕፃኑ ሞተ። ዳዊትም ሕፃኑ መሞቱን እንደ ሰማ፥ ጾሙን አቆመና ፊቱን ታጠበ፥ ልብሱንም ቀየረ፥ ከዚያም ለእግዚአብሔር ሰግዶ ምግቡን በላ። ዳዊት ሕፃኑ ከሞተ በኋላ ይህን ሁሉ ነገር በማድረጉ አገልጋዮቹ ሁሉ ተገረሙ። በምን ምክንያት ነው ሕፃኑ ከሞተ በኋላ ኀዘኑን ያልቀጠለው? ዳዊት በጊዜው የሰጠው መልስ፥ እግዚአብሔር ልጁን ከሞት እንዲያድንለት ተስፋ በማድረግ ጾሞና ጸልዮ እንደ ነበረ ነው። አሁን ግን ልጁ ሞቶአል። ስለዚህ ሊያደርገው የሚችለው ነገር አይኖርም። ጾምና ጸሎቱን ቀጥሎ ቢሆንም፥ ሕፃኑን ከሞት ወደ ሕይወት መልሶ ሊያመጣው አይችልም ነበር። ነገር ግን ዳዊት በመጨረሻ፥ በሚሞትበት ጊዜ ከሕፃኑ ጋር ሊሆን ወደ እርሱ ዘንድ ይሄዳል። ዳዊት ለዘላለም በእግዚአብሔር ቤት እንደሚኖር እርግጠኛ ነበር። በ2ኛ ሳሙኤል 12 ውስጥ ዳዊት ሲናገር፥ አንድ ቀን ሄዶ በሚኖርበት ስፍራ ሕፃኑ የዘላለም ሕይወትን አግኝቶ በእግዚአብሔር ቤት መኖር መጀመሩን ዳዊት ያመነ መሆኑ ይገመታል። ዳዊት በንግግሩ ሕፃኑ እንደ ሞተ ሁሉ እርሱም የሚሞት መሆኑን ብቻ ሊናገር አይችልም ነበር? የተናገረው ይህን አይመስልም። ለእግዚአብሔር ሰግዶአል፥ እንደዚሁም ራሱን በማጽናናት ላይ ነበር (ቁጥር 22–23)። ዳዊት 'ከሕፃኑ ሞት በኋላ ለእግዚአብሔር መሰገድና ከዚያም መጽናናቱ እርሱም አንድ ቀን ሟች መሆኑን ብቻ አሳስበው ብሎ መገመት ያዳግታል። በቁጥር 23 እንደምናነበው፥ ዳዊት አንድ ቀን ከሕፃኑ ጋር እንደሚሆን ተስፋ ያደረገ ይመስላል። ስለዚህ በ2ኛ ሳሙ. 12፡22–23 የተጻፈው ቃል የሚሞቱ ሕፃናት በእግዚአብሔር ዘንድ ሆነው የዘላለምን ሕይወት እንደሚኖሩ ያመለክታል።

ኢየሱስ በወንጌል ውስጥ ብዙ ጊዜ ስለ ትንንሽ ልጆች ይናገራል። በማርቆስ 10፡13–16 ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው ሰዎች ልጆችን ወደ ኢየሱስ ዘንድ እንዳመጡ ተጽፎአል። ደቀ መዛሙርቱ ግን እነዚህ ትንንሽ ልጆች

ኢየሱስን ያስቸግሩታል ብለው ሠጉ። ግን ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በዚህ ጉዳይ ገሠጻቸው። ለኢየሱስ ልጆቹ ናቸው። ኢየሱስ ሕፃናትን ተቀብሎ ጠቃሚ የሆነ መንፈሳዊ ትምህርት ያስተምራቸው ነበር። አብረውት ለነበሩት ሰዎች የእግዚአብሔር መንግሥት እነዚህን ሕፃናት ለመሰሉት ነው ሲል ነገራቸው። ኢየሱስ ዘንድ ይመጡ የነበሩ ልጆች ትንንሾች እንደ ነበሩ ግልጽ ነው። ምክንያቱም ቁጥር 16 እንደሚለው አንሥቶም በክንዱ አቀፋቸው ይላል። ምንም እንኳን ልጆቹ ገና የተወለዱ ሕፃናት ባይሆኑም፣ ኢየሱስ በቀላሉ አንሥቶ ሊያቅፋቸው የሚችላቸው ዓይነት ነበሩ። እነዚህ ልጆች ኢየሱስ አዳኛቸው ለመሆኑ እምነታቸውን በሚገልጹበት ዕድሜ ላይ አልነበሩም። ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ላሉት ነው ሲል ተናገረ። እዚህ ላይ ይህን ቃል የመናገሩ ሁኔታ፥ መልካም ሥራቸውን ይዘው ሳይሆን፥ ደካሞች፥ አነስተኞችና በማንም ዘንድ ጎልተው የማይታዩ መሆናቸውን ተገንዝበው ወደ እርሱ ዘንድ የሚመጡ እነርሱ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደሚገቡ ሊያሳስብ ነው። ኢየሱስ በዚህ ንግግሩ ምናልባት እነዚህ ሁለት ወይም አራት ዓመት የሚሆናቸው ልጆች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባሉ ብሎ በግልጽ አልተናገረም። ግን የንግግሩ አንድምታ ወይም አቅጣጫው ይህንኑ የሚጠቁም ነው። በተለይ በማርቆስ 10፡13–16 ያለው ቃል፥ የሚሞቱ ትንንሽ ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር ሆነው የዘላለምን ሕይወት እንደሚኖሩ በጥብቅ የሚያመለክት ከፍል ነው።

በማቴዎስ 18፡1–14 ያለውም ተመሳሳይ ቃል ነው። በዚህ ከፍል የጌታ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን በእግዚአብሔር መንግሥት ታላቁ ማን ነው? ሲሉ ጠየቁት። ኢየሱስም ትንሽ ልጅ በመጥራትና በመካከላቸው በማቆም መልሱን ሰጣቸው። ተጠርቶ የቆመው ልጅ መቆም የሚችል ነበር፥ ግን ጥቅሱ ትንሽ ልጅ ያደርገዋል። እንደዚሁም ኢየሱስ ሲናገር፥ በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉም ታላቅ የሚሆኑት ወደ እርሱ ዘንድ የዚህን ልጅ ትሕትና ተላብሰው የሚመጡ መሆናቸውን አስገንዝቧል። በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚታየው በኢየሱስም ጊዜ የልጆች ድርሻ በጸጥታ በዕድሜ የገፉትን ማገልገል ነበር። ስለዚህ ልጆች ትሑት፥ ራሳቸውን ያስገዙና ታዛዦች መሆን ይጠበቅባቸው ነበር። ስለ ራሳቸው ትልቅነት ስለማያስቡ፥ ሁልጊዜ ጥገኝነትና ጎልቶ ያለመታየት ሁኔታ ይታይባቸዋል። ስለዚህ ኢየሱስ ወደ እርሱ ለሚመጡት ሰዎች ሁሉ እንደዚህ ያሉ ልጆችን በምሳሌነት በማቅረብ እነርሱ ወደ እርሱ ሊመጡ የሚችሉበትን ሁኔታ ይገልጥላቸው ነበር። ይህም በትሕትናና በእርሱ ላይ በመመርኮዝ፥ ኢየሱስ የሚሰጣቸውን ለመቀበል ብቁ አለመሆናቸውን በመገንዘብ ወደ እርሱ እንዴት እንደሚቀርቡ ምሳሌ ሆኖ የሚገልጽላቸው ነበር።

ነገር ግን ኢየሱስ ነገሩን ከፍ አድርጎ በማጉላት፥ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ሕፃን ናት አለ። በቁጥር 10 ውስጥ ኢክሎ ሲናገር፥ ለእነዚህ ታናናሾቹ ‹‹በሰማይ መላእክት አሉዋቸው አለ››። ኢየሱስ ይህን ሲናገር አባባሉ ትንንሽ ልጆች በሰማይ አብረዋቸው ሆነው የሚጠብቋቸው መላእክት አሉ ማለቱ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ሰዎች የሚጠብቁዋቸው መላእክት እንዳሉዋቸው የሚጠቁሙ ከፍሎች አሉ (መዝ. 34፡7፤ 91፡11)። እንግዲህ እንዲህ ከሆነ፣ የኢየሱስ አነጋገር ትንንሽ ልጆች

ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር የሚቆጠሩ መሆናቸውን ያመለክታል። እንዲያውም በቁጥር 14 ውስጥ አባቴ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዳቸውም እንዲጠፉ አይፈልግም በማለት ግልጽ ያደርገዋል። ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ለልጆቹ በጣም ትልቅ ግምት እንደሚሰጥ ይገልጻል። ነገር ግን ከዚህ የበለጠ የሚናገር ይመስላል፥ ይህም ለማቴዎስ 18፡14 ትንንሽ ልጆች አይጠፉም የሚለው ነው።

በዚህ ክፍል እንደተገለጸው፥ እግዚአብሔር የሚሞቱትን ትንንሽ ልጆች ወደ እርሱ ዘንድ አምጥቶ የዘላለም ሕይወትን የሚሰጣቸው ስለመሆኑ ግንዛቤ ይፈነጥቃል። ሆኖም እነዚህ ሕፃናት ከሞቱ በኋላ ወደ ሰማይ የሚገቡት በልዩ ተሰጥኦዋቸው ወይም ከኃጢአት ነፃ ስለሆኑ አይደለም። በ11ኛውና በ12ኛው ትምህርት ውስጥ እንደ ተከታተልነው፥ ሰዎች ሁሉ በኃጢአት መወለዳቸው የታወቀ ነው። ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ሕፃናት ደኅንነትን ስለሚያገኙበት መንገድ ባይገልጽም፥ ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው የሰጠውን ደኅንነት፥ እምነትን በተግባር ለመግለጽ ላልደረሱ ሕፃናት እግዚአብሔር ሰጥቶአቸዋል።

እንዲሁም እግዚአብሔር ሕፃናት ስለተጠመቁ እንደማያድናቸው፥ ደግሞም ስላልተጠመቁ እንደማይኮንናቸው እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። እንደተመለከትነው ሁሉ፥ ጥምቀት ደኅንነትን አያመጣም። ነገር ግን ጥምቀት ለሰዎች የማዳን እምነታቸው ምልክትና ማኅተም ነው። ሕፃናትን የማጥመቅ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተነሣበት አንዱ ምክንያት፥ ክርስቲያኖች በሚሞቱበት ጊዜ ወደ ሰማይ የሚሄዱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነበር። ነገር ግን ሕፃናትና ትንንሽ ልጆች በጥምቀት ምክንያት እግዚአብሔር ያድናቸዋል የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ የለም። የእግዚአብሔር ሕፃናትን የማዳን ነገር፥ እርሱ በክርስቶስ ሞት ትሩፋት ተጠቅሞ እምነታቸውን ለመግለጽ ለማይችሉ ሕፃናትና ትንንሽ ልጆች የሚሰጠው ሉዓላዊ የሆነ ምሥጢራዊ ሥራው ነው።

17ኛ ጥያቄ፡- ልጆቻቸውን በሞት ላጡ ወላጆች ማጽናኛነት በእነዚህ ጥቅሶች እንዴት ትጠቀማላችሁ?

ወላጆች ልጆቻቸውን በሞት በሚያጡበት ጊዜ፥ ከባድ የሆነ የትምህርተ መለኮት የማጽናኛ ቃል አያስፈልጋቸውም። ይህን በመሰለ ከባድ ወቅት ከእነርሱ ጎን ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስን አብሮ ማንበብና አብሮ መጸለይ ያሻል። መጽሐፍ ቅዱስን በምታነቡበት ጊዜ፥ አሁን ያጠናናቸውን ክፍሎች ብታነቡ የተሻለ ነው። እነዚህ ክፍለ ምንባቦች እግዚአብሔር ለልጆቻቸው ስላለው ፍቅር በመግለጽ ያጽናናቸዋል።

3. ለመሆኑ በመጨረሻው ሰዎች ሁሉ ይድናሉ ወይ?

ሰዎች በክርስቶስ ሥራ ብቻ እንደሚድኑ ተመልክተናል (ትምህርት 13 እና 14)። እንደዚሁም እግዚአብሔር ወደ ራሱ የጠራቸው የሚያምኑና ንስሐ የሚገቡ፥ ኋላም ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱ፥ በመጨረሻ የደኅንነትን

በረከቶች እንደሚያገኙ ተገንዝበናል (ትምህርት 15 እና 16)። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተረጋገጠው፥ በክርስቶስ ውስጥ እምነታቸው የተረጋገጠላቸው ብቻ ይድናሉ። በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር ክርስቶስን ንቀው ሳይቀበሉት የሚቀሩትን ለዘላለም እንደሚቀጣቸው የሚያስተምሩን ብዙ ጥቅሶች አሉ።

18ኛ ጥያቄ፡– ማቴ. 25፡41፥ 46 አንብብ። ሀ) ክርስቶስ ጻድቃን ባለመሆናቸው የሚፈርድባቸው ወዴት ይሄዳሉ? ለ) 2ኛ ተሰ. 1፡8–9 አንብብ። እግዚአብሔር የማያውቁትን እንዴት አድርጎ ይቀጣቸዋል? ሐ) ራእይ 20፡10፥ 14–15፤ 21፡8 አንብብ። በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ያልተገኙ ምን ይሆናሉ? መ) ለምን ያህል ጊዜ በዚያ ይሆናሉ?

መጽሐፍ ቅዱስ ደኅንነት በክርስቶስ አማካይነት ይመጣል፥ ደግሞም በክርስቶስ የሚያምኑ ይድናሉ ብቻ ብሎ አያስተምረንም። እንደዚሁም ክርስቶስን የሚንቁ ለዘላለም ይጠፋሉ ሲልም ያስተምራል። በማቴዎስ 25፡31–46 ውስጥ ኢየሱስ ስለ በጎችና ፍየሎች ፍርድ ይነግረናል። በዚህም እርሱን የሚቀበሉትንና እርሱን የሚንቁና የሚተዉትን ለማመልከት ነው። ሳይቀበሉት ንቀው የተዉት በዘላለማዊ ኩነኔና በእሳት ይቀጣሉ (ቁጥር 41፥46)። በ2ኛ ተሰ. 1፡8–9 ውስጥ ጳውሎስ ሲናገር፥ እግዚአብሔርን የሚያውቁት ከኃይል ክብሩ ተለይተው በዘላለማዊ ጥፋት ይቀጣሉ ይላል። እንደዚሁም ራእይ ምዕራፍ 20፥ ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ሁሉ ቀንና ሌት ስለሚሠቃዩበት የእሳት ባሕር ይገልጻል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው ጊዜ ሰዎች ሁሉ እንደሚድኑ የማይናገር መሆኑ ግልጽ ነው። በመሆኑም አንዳንዶች ክርስቶስን ባለመቀበላቸው ይጠፋሉ።

ሆኖም ግን፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በመጨረሻው ጊዜ ሰዎች ሁሉ እንደሚድኑ የሚያስተምሩ የሚመስሉ ጥቂት ክፍለ–ምንባቦች አሉ። እንግዲህ ክርስቶስን ያልተቀበሉ እንደሚጠፉ በግልጽ የተመለከትን ከሆነ፥ የተባሉት ክፍለ ምንባቦች ታዲያ ምን ያስተምራሉ?

19ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ዮሐ. 1፡29ን አንብብ። የእግዚአብሔር በግ የማንን ኃጢአት ነው የሚያስወግደው? ለ) 1ኛ ጢሞ. 2፡6ን አንብብ። ክርስቶስ ራሱን እንደ ቤዛ አድርጎ የሰጠው ለማን ነው? ሐ) 1ኛ ጢሞ. 4፡10ን አንብብ። ክርስቶስ የሚያድነው ማንን ነው? መ) ዕብ. 2፡9 አንብብ። ክርስቶስ ሞትን የቀመሰው ለማን ሲል ነው? ሠ) 1ኛ ዮሐ. 2፡2ን አንብብ። ክርስቶስ የኃጢአት ማስተሰሪያ የሆነው ለማን ነው? ረ) 1ኛ ዮሐ. 4፡14ን አንብቡ። የልጁ መድኃኒትነት ለማን ነው?

20ኛ ጥያቄ፡– 2ኛ ጴጥ. 3፡9 አንብብ። እግዚአብሔር ወደ ንስሐ እንዲመጣ ማንን ይፈልጋል?

የተወሰኑ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች በአንድ በኩል ክርስቶስ ለመላው ዓለም ኃጢአት መሞቱን ያስተምራሉ። ዮሐ. 1፡29 ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት መውሰዱን ይናገራል። 1ኛ ጢሞ. 2፡6 ደግሞ ክርስቶስ ራሱን አሳልፎ ቤዛ አድርጎ ሰጠ ይላል። 1ኛ ጢሞ. 4፡10 ክርስቶስ

የሰዎች ሁሉ አዳኝ ነው ይላል። እንዲሁም ዕብ. 2፡9 ክርስቶስ ለሁሉም ሲል ሞትን ቀመሰ ይላል። 1ኛ ዮሐ. 2፡2 ክርስቶስ የዓለም ሁሉ ኃጢአት ማስተሰሪያ ነው ይላል። ቀጥሎም በ1ኛ ዮሐ. 4፡14 ውስጥ ወልድ የዓለም አዳኝ ነው ይላል። ለማንኛውም ዘርና ጎሣ በዓለም ክፍሎች ሁሉ ላሉ የሰው ልጆች ክርስቶስ ሞቶአል ብለው እነዚህ ጥቅሶች እንደሚያስተምሩ አድርገው ይገምታሉ። ነገር ግን እነዚህ ጥቅሶች ከዚህ የበለጠ የሚናገሩ ይመስላሉ። በዚሁ መሠረት የክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሞት በዓለም ላይ ላሉ ለኃጢአታቸው ቤዛ ሊሆን ይችላል የሚል ግንዛቤ ያላቸው ይመስላሉ። 2ኛ ጴጥ. 3፡9 ሰው ሁሉ ንስሐ እንዲገባና የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኝ ይላል። ሐዋርያው በ2ኛ ጴጥ. 2፡1–3 ባለው ክፍል ሲያስጠነቅቅ፥ «የዋጃቸውን ጌታ የሚክዱ» ሐሰተኞች መምህራንና ነቢያት ይነሣሉ ብሏል። የክርስቶስ ሞት የኃጢአታቸውን ዋጋ ሊከፍልላቸው ሲችል ነገር ግን ክርስቶስን ንቀውና ችላ ብለው እነርሱ በፈቀዱት መንገድ ሄዱ። እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እንዲድን ፈቃዱ ነው፥ የክርስቶስ ሞት ቤዛ ሆኖ የሁሉንም የኃጢአት ዋጋ እንዲከፍል አደረገ (ዮሐ. 1፡29)። እነሆ፥ ክርስቶስ ለሁሉም አስፈላጊውን ቤዛ ከፍሏል (1ኛ ጢሞ. 2፡6)። ክርስቶስ በመሥዋዕትነቱ የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ሆኖአል (1ኛ ዮሐ. 2፡2)። ክርስቶስ ለሰው ሁሉ ሞትን ቀምሶአል (ዕብ. 2፡9)። ክርስቶስ ሁሉን የሚቤዥ መድኅን ነው (1ኛ ጢሞ. 4፡10፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡14)። የደኅንነት ተግባር ሁሉ ለሰዎች ሁሉ ተፈጽሞአል። ነገር ግን እያንዳንዱ ግለሰብ ክርስቶስ ያደረገለትን ይህን ተግባር ሊቀበል ወይም ላይቀበል ይችላል። ነገር ግን ይህን ክርስቶስ ያከናወነላቸውን ተግባር ሁሉ በእምነት የሚቀበሉ የደኅንነት በረከቶችን ተቋዳሽ ይሆናሉ። በአንጻሩም ክርስቶስ ያደረገላቸውን ሥራ ንቀው የተዉትን ደግሞ ለዘላለም ይቀጣቸዋል። ልብ አድርጉ እነዚህ ጥቅሶች የሚሉት ሰዎች ሁሉ ይድናሉ ሳይሆን፥ የሚድኑት ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁሉ የፈጸመውን ተግባር በእምነት የሚቀበሉት እንደሚሆኑ ነው። በ16ኛው ትምህርት ውስጥ ሌሎች ጥቅሶች እንደሚናገሩት፥ ጌታ ኢየሱስ የፈጸማቸውን ተግባራት የሚቀበሉና መቀበላቸውንም የሚገልጹ የዘላለምን ደኅንነት ያገኛሉ።

21ኛ ጥያቄ፡– ፊልጵ. 2፡10–11 አንብብ። በክርስቶስ ፊት ተንበርክከው ንስሐ የሚገቡት እነማን ናቸው?

22ኛ ጥያቄ፡– ሮሜ 5፱18 አንብብ። ሀ) የአንዱ ጽድቅ ሕይወትን የሰጠው ለማን ነው? ለ) ሮሜ 5፡17 አንብብ። በሕይወት ሳሉ በክርስቶስ አማካይነት የሚገዙ እነማን ናቸው? ሐ) 1ኛ ቆሮ. 15፡22 አንብብ። ሕያዋን የሚሆኑት እነማን ናቸው?

23ኛ ጥያቄ፡– ሮሜ 11፡ 32 አንብብ። እግዚአብሔር ምሕረቱን ለእነማን አሳየ?

በመጨረሻው ጊዜ ሰዎች ሁሉ እንደሚድኑ በማስመሳል፥ አንዳንዶች የሚጠቀሙባቸው ጥቂት ጥቅሶች አሉ። ነገር ግን እነዚህ የሚጠቅሱዋቸው ክፍሎች የሚያስተምሩት በጣም የተለየ አሳብ ነው። ፊልጵ. 2፡10–11 ላይ ስንመለከት፥ ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፤ ምላስም ሁሉ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክራል፤ ሰዎች ሁሉ የኢየሱስን ደኅንነት ይቀበላሉ ማለቱ ነው ይላሉ። ነገር ግን ይህ ጥቅስ በመጨረሻ ሰዎች ሁሉ ይድናሉ አይልም።

ይልቅስ ፊልጵ. 2፡10–11 የሚለው፥ የተፈጠሩት ሁሉ ግለትም፥ የሰው ልጆች፥ መላእክት ሆኑ ሰይጣናትም ሳይቀሩ፥ በመጪረሻው ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ይመሰክራሉ ነው የሚለው። ስለዚህ ክርስቶስን በፈቃዳቸው የተቀበሉት ሁሉ ጌታ መሆኑን ይመሰክራሉ። በአንጻሩ ደግሞ ፈቅደው ያልተቀበሉት በግድ ጌታ መሆኑን ይመሰክራሉ። ስለሆነም፥ ሁሉም ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ይመሰክራሉ፤ ይሁን እንጂ፤ ሁሉም ደግሞ አይድኑም።

ሮሜ 5፡18 የአንዱ የአዳም ኃጢአት የቅጣትን ፍርድ በሰው ሁሉ ላይ እንዳመጣ፥ እንዲሁም የአንድ የክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ብዙዎችን ከቅጣት ነፃ አድርጎ ሕይወትን ይሰጣል ይላል። ይህ ጥቅስ ይህን ማለቱ፥ ሁሉም ሰው ይጸድቃል ማለቱ አይደለም። ጳውሎስ ለመናገር የፈለገው፥ የአዳም ዘር የሆነ ሁሉ እንደ ተኮነነ፥ እንደዚያው ደግሞ በክርስቶስ የጸደቀ ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንደሚያገኝ ነው። በቁጥር 17 ግልጽ እንደሆነው፥ ጳውሎስ በምድር ላይ ያለ እያንዳንዱ ሰው ይድናል አላለም፥ እርሱ ያለው የእግዚአብሔርን ጸጋና ጽድቅ የተቀበሉ ብቻ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የዘላለምን ሕይወት ይወርሳሉ ነው። ሮሜ ምዕራፍ 5ም እንደሚያስተምረው፥ አንድ ሰው ለመዳን የእግዚአብሔርን ጸጋ መቀበል አለበት ይላል። ይህን ሲል ሰው ሁሉ ይድናል ማለት አይደለም። በተመሳሳይ መንገድ 1ኛ ቆሮ. 15፡22 ውስጥ ያለው ቃል፥ ሰው ሁሉ ሕያው ይሆናል አይልም። ሕያዋን የሚሆኑት፥ በክርስቶስ የሆኑ ብቻ ናቸው። እንደ መጪረሻው ጥቅስ ሆኖ ሰዎች ሁሉ በጊዜው ፍጻሜ ላይ እንደሚድኑ ይናገራል ተብሎ የሚጠቀሰው ሮሜ 11፡32 ነው። ቃሉም፥ እግዚአብሔር ምሕረቱን ለሰው ሁሉ ያሳያል የሚለው ነው። ነገር ግን ይህ ጥቅስ ሐዋርያው እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ሳይቀበሉ ስለ ቀሩ፥ እግዚአብሔር በመጪረሻ ደኅንነትን ለአሕዛብ አሳልፎ እንደ ሰጠ፥ በሦስት ምዕራፎች ላይ የተናገረው ትምህርት ማጠቃለያ ነው። እዚህ ላይ የሐዋርያው ጳውሎስ ማጠቃለያ፥ እግዚአብሔር ደኅንነትን ለመስጠት የሰዎችን ታዛዥነትና ወደ እርሱ መመለስን እንደሚፈልግ ለማስረዳት ነው። ስለዚህ ደኅንነት ለአይሁዶች ብቻ የተሰጠ ነገር አይደለም። ደኅንነት በዓለም ላሉ ሰዎች ሁሉ ሊሰጥ የሚችል ነው። ሮሜ 11፡32 እግዚአብሔር ሁልጊዜ ምሕረቱን ለሌሎች ለመስጠት በአንዳንድ ሰዎች እምቢተኝነት እንደሚጠቀም ለማስተማር ነው።

24ኛ ጥያቄ፡– ክርስቶስ ለሰዎች ሁሉ ደኅንነትን ስለ መስጠቱ ያላችሁ አስተያየት ምንድን ነው?

ክርስቶስ ሰዎች ሁሉ ደኅንነትን እንዲያገኙ የፈቀደ በመሆኑ ተስፋ ቆርጠን ግንኙነታችንን ማቆም የለብንም። እነዚህ ሰዎች ከሃይማኖታቸውና ከሳድሜያቸው ሁኔታ ወይም አስቀድመው ክርስቶስን ባለመቀበላቸው ወደ እርሱ ሊመጡ አልቻሉ ይሆናል። ሆኖም ክርስቶስ ለእነርሱ ሲል ሞቶአል። ደግሞም እግዚአብሔር ደኅንነት ሊሰጣቸው ተዘጋጅቷል። ስለዚህ የወንጌልን ቃል በታማኝነት ልንነግራቸውና በድፍረት ልንቀርባቸው ይገባል።

ሦስተኛ ቀን– ሰዎች የክርስቶስን መልእክት ሳይሰሙ ሊድኑ ይችላሉ?

እንግዲህ ዛሬ ስለ ደኅንነት ከሚነሡ ከባድ ከሆኑ ጥያቄዎች አንዱን ለመመለስ እንሞክራለን። ስለ ክርስቶስ በፍጹም ሰምተው የማያውቁ አንዳንድ ሰዎች በእግዚአብሔር በማመናቸው ይድናሉ?

ከአንድ መቶ ዓመት በፊት አካባቢ፥ በደቡብ ኢትዮጵያ ኢሳ የተባለ ነቢይ ተነሥቶ ነበር። ይህ ነቢይ በሕይወቱ ዘመን በአብዛኛው በኢትዮጵያ ደቡባዊው ክፍል እየተዘዋወረ፥ ሰዎች ለርኩስ መናፍስት መስገዳቸውን ትተው አንዱን በሰማይ የሚኖር እውነተኛ አምላክ እንዲያመልኩ ያስተምራቸውና ያሳስባቸው ነበር። እስከምናውቀው ድረስ፣ ኢሳ የክርስቲያኖችን ወንጌል ጨርሶ አልሰማም ነበር። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውም አምላክም ሆኖ ወደዚህ ዓለም በመምጣት የንጽሕና ሕይወትን በመኖር የመሥዋዕትነትን ሞት እንደ ሞተ በፍጹም አልሰማም። እንዲሁም ከኃጢአቱ ለመዳን ሲል በክርስቶስ የማመን ዕድልም አላገኘም። ሆኖም ግን ኢሳ የሰማይ አምላክ የሆነውን አንዱን እግዚአብሔርን የማምለክ ዝንባሌ ይታይበት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ኢሳን ስለ መሰሉ ሰዎች የሚናገረው ነገር አለው? እግዚአብሔር እንደ ኢሳ ያለ፥ በእርሱ የሚያምን፥ ግን የክርስቶስን መልእክት ለመስማት ዕድል ያላገኘን ሰው ያድን ይሆን? እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት የተገኘው ትሩፋት፥ እንደ ኢሳ ያሉ ስለ ክርስቶስ ጨርሰው ያልሰሙ ወይም በእርሱ ያላመኑ ሰዎች እንዲድኑበት ያደርግ ይሆን?

1. የአዲስ ኪዳን አጠቃላይ ዓላማ ሰዎች የክርስቶስን መልእክት ሰምተው፥ ደኅንነቱን ስለ መቀበላቸው በእምነታቸው አማካይነት እንዲያስታውቁ ነው።

25ኛ ጥያቄ፡– ዮሐ. 14፡6 አንብብ። ወደ አብ የሚያደርሰው ብቸኛው መንገድ ማን ነው?

26ኛ ጥያቄ፡– የሐዋ. ሥራ 4፡12 አንብብ። ሰዎች በማን ስም ብቻ ይድናሉ?

27ኛ ጥያቄ፡– ሮሜ 1፡18–23 አንብብ። ሀ) ሰዎች ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ምን ያውቃሉ? (ቁጥር 20) ለ) ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ባላቸው በዚህ እውቀት ምን ያደርጋሉ? (ቁጥር 18፥ 21–23)

28ኛ ጥያቄ፡– ሮሜ 10፡13–14 አንብብ። ሀ) የሚድነው ማን ነው? (ቁጥር 13) ለ) ሰዎች የጌታን ስም መጥራት እንዲችሉ ምን ያስፈልጋቸዋል? (ቁጥር 14)

አዲስ ኪዳን በግልጽ እንደሚናገረው፥ የደኅንነት አጠቃላይ ዓላማ፥ የክርስቶስን መልእክት ማድመጥና የሰሙትንም በእምነት መግለጥ ነው። በዮሐንስ 14፡6 ውስጥ ኢየሱስ ራሱ፥ ማንም ቢሆን በእርሱ በኩል ካልሆነ ወደ አብ ሊመጣ እንደማይችል ተናግሮአል። ብዙ ምንባቦችን ከጻፈ በኋላ ሰዎች መዳን ከፈለጉ እምነታቸውን በኢየሱስ ላይ ማድረግ እንዳለባቸው ዮሐንስ ጽፎአል (ምሳሌዎቹ፡– ዮሐንስ 1፡12፤ 3፡15፤ 16፥ 36)። በግልጽ

እንደሚታየው፥ ኢየሱስ የተናገረው፥ ወደ አብ ለመድረስ የሚቻለው በእርሱ በማመን ብቻ መሆኑን ነው። ቀደም ባሉት የሐዋርያት ሥራ ምዕራፎች እንደተጻፈው፥ ሐዋርያት በኢየሱስ አማካይነት ስለሚገኘው ደኅንነት ስለ ሰበኩ፥ የአይሁድ መሪዎች ተቆጥተው ነበር። ልክ እንደ ሐዋርያት፥ እነዚህ የአይሁድ መሪዎችም በእስራኤል አንድ አምላክ ያምኑ ነበር። እንዲሁም መዳን የሚገኘው በእርሱ መሆኑን ያወቁ ነበር። ነገር ግን በሐዋርያት ሥራ 4፡10–12 ውስጥ፥ ጴጥሮስ አንዱንና የደኅንነት መንገድ እርሱ ብቻ የሆነውን ክርስቶስን አለመቀበላቸውን ነገራቸው። ስለሆነም እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ደኅንነትን ለማግኘት በሰማይ የሚኖር አንዱን እውነተኛ አምላክ ማመናቸው ብቻ አይበቃም ነበር። ደኅንነትን ለማግኘት እንዲችሉ በኢየሱስ ማመን ነበረባቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱም እንደሚያስተምረው፥ በሰማይ ስለሚኖረው አምላክ ማወቅ ብቻ አይበቃም ይላል። ቀጥተኛው የደኅንነት መንገድ ስለ ክርስቶስ የሚታወጀውን ቃል መስማትና የሰሙትን በእምነት መግለጥ ነው። በሮሜ ምዕራፍ 1 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚለው፥ ሰዎች ሁሉ ስለ ሰማዩ አምላክ የተወሰነ እውቀት አላቸው። ነገር ግን ይህ እውቀት ሊያድናቸው የሚበቃ አይደለም። በሰማይ ስለሚኖረው አምላክ የሚያውቁት «ዘላለማዊ ኃይሉንና አምላክነቱን» ነው (ሮሜ 1፡20) ይላል። ታዲያ ሰዎች በዚህ እውቀት እንዴት ይጠቀሙበታል? «እውነቱን ሸፈኑበት» እግዚአብሔርን በማክበር ፈንታ፥ ፍጥረታትን አመለኩ (ሮሜ 1፡18፥21–23)። በፍጥረታት አማካይነት ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ደኅንነትን ለማስገኘት በቂ አይደለም። ብዙ ጊዜ ሰዎች ይህን እግዚአብሔርን የማወቅ ሁኔታ ትተው ፊታቸውን ያዞሩና እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች ያመልካሉ (ሮሜ 1፡25)። ጳውሎስ በሮሜ 10፡13–14 እንደሚናገረው፥ ሰዎች መዳን ከፈለጉ የጌታን ስም መጥራት አለባቸው። ጳውሎስ፥ «የጌታ ስም» በሚልበት ጊዜ፥ በትክክል ስለ ጌታ ኢየሱስ ማሰቡ ነው። (በሮሜ 10፡9 ውስጥ የተጻፈውን ዐውደ ንባብ ተመልከት።) ሰዎች፥ የጌታን ስም ለመጥራት ስለ ክርስቶስ የተነገረውን መልእክት ሰምተው በእምነት ሊገልጡት ይገባል (ሮሜ 10፡14)። የደኅንነት ዓላማ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና ሞት የተነገረውን ሰምተው ለደኅንነታቸው በእርሱ ማመን ነው።

2. ሰዎች ሁሉ ስለ ክርስቶስ ሳይሰሙ እንዲድኑ እግዚአብሔር በቂ ፍንጭ ሰጥቶአል?

ቢያንስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ጥቅሶች ስለ ክርስቶስ ጨርሶ ያልሰሙና በእርሱ አምነው ደኅንነትን ስላላገኙ ሰዎች እግዚአብሔር የሚሰው ፍንጭ እንዳለ ይጠቁማሉ። እነዚህ ጥቅሶች ለእኛ ምን ይሉናል?

29ኛ ጥያቄ፦ ዮሐ. 1፡9 አንብብ። ሀ) ጌታ ኢየሱስ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ ለእነማን ብርሃንን ሰጠ? ለ) ዮሐንስ 1፡5፥10 አንብብ። ኢየሱስ ግን እንደ ነበረ ሁሉም አውቀው ነበር? ሐ) ዮሐ. 1፡12 አንብብ። እነማን በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች ሆኑ?

30ኛ ጥያቄ፡– የሐዋ. ሥራ 14፡16–17 አንብብ። ባለፉት ዘመናት እግዚአብሔር ለሕዝቦች ሁሉ ምን አደረገላቸው?

ዮሐንስ 1፡9 እንደሚናገረው ኢየሱስ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያበራ ብርሃን ነበር ይላል። ነገር ግን ይህን ክፍል ሲመለከቱት መሠረተ አሳቡ ግልጽ እንደሚያደርገው የኢየሱስ መምጣት ሰዎች ሁሉ ለመዳን እግዚአብሔርን በበቂ ሁኔታ እንዲያውቁ አላደረጋቸውም የሚል ነው። ኢየሱስ የሚያበራው ብርሃን፥ በሰዎች ልቦና ላይ የሚበራ ብርሃን ነው። በልባቸው ውስጥ ያለውን ጨለማ ወደ ብርሃን አውጥቶ ያሳያል (ዮሐንስ 1፡5)። እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ለሰዎች የገለጠው ዋናው መገለጫ ነው። ይህን ብርሃን ያዩ ብዙዎች ግን እንደ ፈጣሪያቸው አድርገው አላወቁትም፥ ደግሞም እግዚአብሔርን የሚገልጥ ብርሃን አድርገው አልተቀበሉትም (ዮሐንስ 1፡5፥10)። ነገር ግን ስለ እርሱ የሰሙት፥ ሰምተውም በእምነት የተቀበሉት የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ደኅንነትን አገኙ (ዮሐንስ 1፡12)። ዮሐንስ 1፡9 እግዚአብሔር፥ ሰዎች ሁሉ ስለ ክርስቶስ ጨርሶ ባይሰሙም፥ ይድኑ ዘንድ በቂ ብርሃን ይሰጣል ብሎ አያስተምርም። ምክንያቱም የጥቅሱ መሠረተ አሳብ፥ ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ቢፈልጉ፥ አስቀድመው ሊቀበሉት እንደሚገባ በግልጽ ያስተምራል (ዮሐ. 1፡12)።

በሐዋርያት ሥራ 14፡16–17 ውስጥ እንደተጻፈው፥ እግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ በገዛ ራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ ትቶአቸው ነበር። ይሁን እንጂ እርሱ እንዴት ያለ ቸር አምላክ መሆኑን የሚመሰክር መልካም ሥራ ማድረጉን አልተወም ነበር። ልብ በሉ እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ደኅንነትን ሰጠ አይሉም። በዚህ ፈንታ እነዚህ ጥቅሶች በሮሜ ምዕራፍ 1 ውስጥ ካለው ጋር አንድ ዓይነት አሳብ ይናገራሉ። እርሱም እግዚአብሔር ሰዎች ስለ እርሱ የሚያውቁትን እንዳላወቁ ሆነው የራሳቸውን መንገድ ተከትለው ወደ ኃጢአት እንዲሄዱ አድርጎ ነበር። አሁን ግን በክርስቶስ ወደ ደኅንነት ይጠራቸዋል። ምንም እንኳን በመረጡት መንገድ እንዲሄዱ እርሱ ቢተዋቸውም፥ በተፈጥሮ አማካይነት ስለ ቸርነቱ በአጠቃላይ ሁኔታ መግለጡን ቀጠለ። የሐዋርያት ሥራ 14፡16–17 ያለው ክፍል፥ እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ጨርሰው ያልሰሙ ሰዎችን ያድናል ብሎ አያስተምርም።

አንዳንድ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ስለ ክርስቶስ ከመስማቱ በፊት በእግዚአብሔር አምኖ የዳነ ሰው ምሳሌ ሆኖ የሚቀርብበት ጊዜ አለ። እግዚአብሔር ቆርኔሌዎስን ስለ ክርስቶስ ከመስማቱ በፊት ነበር ያዳነው? የሐዋርያት ሥራ 10፡2 ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ ሃይማኖተኞችና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ነበሩ ይላል። ከኢየሱስ የተነገራቸውን መልእክት ከመስማታቸውም በፊት ቢሆን፥ አንዱን እውነተኛ የእስራኤል አምላክን ያመልኩና እርሱንም ለመታዘዝ ይጥሩ ነበር። ቢሆንም፤ ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ የእስራኤል አምላክ አንዱና እውነተኛው አምላክ መሆኑን ተረድተው ሊያመልኩት ይጥሩ የነበሩ አሕዛብ ነበሩ። ነገር ግን የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ቆርኔሌዎስ ስለ ኢየሱስ ከመስማቱ በፊት ዳነ አይልም። ታዲያ እግዚአብሔር እንዲህ

ለሚያከብረውና እንዲያድነውም ለሚፈልገው ለቆርኔሌዎስ ምን አደረገለት? ሐዋርያው ጴጥሮስ ሄዶ ስለ ክርስቶስ እንዲሰብክለት ላከው። ቆርኔሌዎስ፥ «በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአት ይቅርታ ያገኛል» (የሐዋ. ሥራ 10፡43) የሚለውን የጴጥሮስ መልእክት እንደ ሰማ፥ እርሱና ቤተሰቡ በኢየሱስ አመኑ፥ መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ። ስለ ኢየሱስ የተናገራቸውን መልእክት ከሰሙ በኋላ ነበር ሙሉ የአዲስ ኪዳን አማኞች በመሆን ሙሉውን የአዲስ ኪዳን ደኅንነትን ያገኙት። ስለዚህ የቆርኔሌዎስ ታሪክ እንደሚያመለክተው፥ በአንድ እውነተኛ አምላክ ለማምለክ የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ፥ እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ የሚናገር መልእክት የሚያቀርብላቸው ሰው እንደሚልክላቸው ነው። እግዚአብሔር የእርሱን ደኅንነት ለማግኘት በእርሱ ለማመን የሚፈልጉትን አይኮንናቸውም።

3. ክርስቶስ ለኃጢአት ሲል ለመሞት ከመምጣቱ በፊት ሰዎች ቀድሞ በብሉይ ኪዳን ጊዜ ይድኑ እንደ ነበሩት፥ ዛሬም ሊድኑ ይችላሉ?

አንዳንድ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ይድኑ በነበረበት መንገድ ዛሬም ሊድኑ ይችላሉ ይባላል። በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ሰዎች ክርስቶስ መጥቶ ለኃጢአት ሲል ከመሞቱ በፊት ነበር የዳኑት። ደኅንነታቸው የክርስቶስን መልእክት በመስማትና በእርሱ በማመን አልነበረም። ዛሬ ሰዎች ይህንኑ በመሰለ መንገድ ሊድኑ ይችላሉ?

ልንመልሰው የሚገባን የመጀመሪያው ጥያቄ፦ በብሉይ ኪዳን ጊዜ የነበሩ ሰዎች እንዴት ሊድኑ ቻሉ? የሚል ነው።

31ኛ ጥያቄ፦ ዕብ. 9፡13-15 አንብብ። ሀ) የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት በሚያቀርቡት ሰዎች ላይ ምን ውጤት ነበረው? (ዕብ. 9፡13)። ለ) የክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሞት በብሉይ ኪዳን አማኞች ላይ ምን ውጤት ነበረው? (ዕብ. 9፡15)።

32ኛ ጥያቄ፦ ዕብ. 10፡1፥4፥11 አንብብ። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ይቀርቡ የነበሩ መሥዋዕቶች ያቀርቡ የነበሩ ሰዎችን ኃጢአት ያስወግዱላቸው ነበር?

33ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 3፡25-26 አንብብ። የብሉይ ኪዳን አማኞች ኃጢአት ምን ጊዜ ቅጣቱን ይቀበል ነበር?

34ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 3፡9-12፥20 አንብብ። ሀ) የብሉይ ኪዳንን ሕግ አሟልቶ ይፈጽም የነበረ ሰው ነበር? (ሮሜ 3፡9-12) ለ) ለብሉይ ኪዳን ሕግ በመታዘዙ አንድ ሰው ይጸድቅ ነበር? (ሮሜ 3፡20)

35ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 4፡3 አንብብ። የአብርሃም ጻድቅነት እንዴት ተረጋገጠለት?

36ኛ ጥያቄ፦ ኦሪት ዘዳግም 10፡16ና ኤርምያስ 4፡4 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ሕዝቦቹ እንዴት እንዲገረዙ ይነግራቸው ነበር? ለ) እንዲህ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

37ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 2፡28-29 አንብብ። በእግዚአብሔር ዓይን እውነተኞቹ አይሁዶች እነማን ናቸው?

በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሰዎች እንዴት ይድኑ ነበር? አንዱና አደናጋሪ የሆነው ነገር፥ እነዚያ ሰዎች መሥዋዕትን በማቅረብ ወይም በመልካም ሥራቸው ዳኑ የሚለው ሁኔታ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ እንደሚያደርገው፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ሰዎች በሕጉ ወይም በመሥዋዕቱ አልዳኑም። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ማንም ሰው ሕጉን አሟልቶ አልጠበቀም። ሕጉንም በመጠበቅ በእግዚአብሔር ዘንድ የጸደቀ አልነበረም (3፡9–12፥20)፥ የብሉይ ኪዳን ጊዜ መሥዋዕት ውጪአዊና ሥነ ሥርዓታዊ ማንጻት መሥዋዕቱን ለሚያቀርቡት ሰዎች ይሰጣቸው ነበር (ዕብ. 9፡12)፥ እንጂ እውነተኛ የኃጢአት ስርየት አይሰጣቸውም ነበር። ምንም ዓይነት የእንስሳ መሥዋዕት እውነተኛውን የኃጢአት ስርየት ሰጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ለጽድቅ አያበቃም (ዕብራውያን 10፡1፥4፥11)። ከዚህ ይልቅ ለብሉይ ኪዳን አማኞች የኃጢአትን ይቅርታ የሰጣቸው የክርስቶስ ሞት ነበር። የብሉይ ኪዳን ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ፊት በእምነት ቀርበው መሥዋዕትን ሲያደርጉ፥ እግዚአብሔር ተስፋውን በመጠበቅ የኃጢአት ይቅርታን እንደሚሰጣቸው በማመን ሲሆን፥ እግዚአብሔርም ውጫዊ ሥነ ሥርዓታዊ ማንጻትን ያደርግላቸው ነበር (ዕብ. 9፡13)። ቢሆንም ኃጢአታቸው የቅጣቱን ዋጋ ስላላገኘ በሙሉና ዘላለማዊ ይቅርታን አላገኙም ነበር። በዚህ ፈንታ እግዚአብሔር ያደረገው ነገር ቢኖር ኢየሱስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ የኃጢአታቸውን ሙሉና የመጨረሻ ቅጣት አቆየው። ግን ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ፥ እግዚአብሔር የክርስቶስን የሞት መሥዋዕትነት፥ በብሉይ ኪዳን ጊዜ በእውነተኛ እምነት ወደ እርሱ ዘንድ ለመጡት ኃጢአት ቤዛ አደረገው (ሮሜ 3፡25–26፥ ዕብራውያን 9፡15)።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳን ሕዝቡን «የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ» ሲል ያዛቸው ነበር (ዘዳግም 10፡16፤ ኤርምያስ 4፡4)። እንግዲህ ሕዝቡ ውጪአዊውን የግርዘት ሥነ ሥርዓት በመፈጸም ብቻ የኃጢአት ይቅርታን ሊያገኙና ደኅንነትን ሊቀበሉ እንደማይችሉ በዚህ ሁኔታ ይገልጽላቸው ነበር። ለማንም ሰው ቢሆን ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት በምንም አኳኋን የኃጢአት ይቅርታን ወይም ደኅንነትን ሊሰጥ አይችልም። ስለዚህ ሰዎች እነዚህን ለማግኘት ከፈለጉ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ከልባቸው ለእግዚአብሔር መታዘዝ አለባቸው። በብሉይ ኪዳን ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ወደ እርሱ የቀረቡና በልባቸው በእርሱ ላይ የተሞረኮዙ፥ የእግዚአብሔር እውነተኞች ሰዎች ብቻ ደኅንነቱን ሊቀበሉ ቻሉ (ሮሜ 2፡28–29)።

የሚከተለው ሠንጠረዥ በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሰዎች እንዴት እንደሚድኑ ያመለክታል። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ይህን በሞቱ የተገኘውን ትሩፋት ለብሉይ ኪዳን አማኞች ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲጠቅማቸው አድርጎአል።

እግዚአብሔር ተስፋ የገባበትን ደኅንነት	በብሉይ ኪዳን ጊዜ ለነበሩ
ይሰጥ ዘንድ፥ ሰዎች በእምነት	አማኞች የወደፊቱ
መሥዋዕታቸውን ለእግዚአብሔር	የክርስቶስ መስቀል

ያቀርቡ ነበር። በእግዚአብሔር ያመኑ ተሸፍኖባቸው ነበር። ቢሆኑም፥ የተስፋውን መፈጸም ሊያዩ አልቻሉም።

የብሉይ ኪዳን አማኞች በአንድ በሰማይ በሚኖር በእግዚአብሔር በማመናቸው ብቻ አልዳኑም። እርሱ በሰጠው ተስፋ መሠረት ደኅንነትን እንደሚቸራቸው ስላመኑ ሊድኑ ችለዋል። እንዲሁም በእግዚአብሔር ቃል ስለ አመኑ ዳኑ። ይህም እኛ በእግዚአብሔር ቃል በእምነት እንደዳንነው ዓይነት ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ፈውስን ያገኙ እንደ ንዕማን ያሉ አሕዛብ ስለ እስራኤል እውነተኛ የሆነ አንድ አምላክ ሊያውቁና በእርሱና በተስፋዎቹ ሊያምኑ ችለዋል። ዛሬ እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምን ግን ስለ ኢየሱስ በፍጹም ያልሰማውን ሰው ያድነዋል? በክርስቶስ ሥራ የተገኙትን ትሩፋቶች ማለትም የሞቱንና ትንሣኤውን ትሩፋቶች ስለ ኢየሱስ ሰምቶ ለማያውቅ ሰው ግን በአንዱ በእውነተኛው አምላክ ለሚያምን ሰው ይሰጠዋልን? አዲስ ኪዳን እንደሚያስተምረው ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶአል፥ የእግዚአብሔር ፍላጎት ስለ ኢየሱስ ሕይወትና ሞት ሰምተው በእምነት የሚያረጋግጡትን ማዳን ነው። ስለ ኢየሱስ በፍጹም ያልሰሙ ሰዎች ካሉ፥ ነገር ግን ቆርኔሌዎስ እንዳደረገው በአንዱ በሰማይ የሚኖር አምላክ ፊት ራሳቸውን ዝቅ ለሚያደርጉት፥ ስለ ኢየሱስ የሚናገረው መልእክት እንዲሰብኩላቸው እግዚአብሔር መልእክተኛውን ይልክላቸዋል። የኢሳን ታሪክ የመሰለ በምንሰማበት ጊዜ፥ በአስተሳሰባችንም ሆነ በአስተያየታችን ረገድ መጠንቀቅ አለብን። ምክንያቱም ስለ ኢሳ ፍጻሜ የማናውቃቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ምናልባት ከመሞቱ በፊት ስለ ኢየሱስ ሰምቶ፥ እንደ አዳኙ አምኖበት ይሆናል። ምንም ያክል ኢሳ ስለ ኢየሱስ የምሥራቹን ለመስማት ባይታደልም፥ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ስለሆነ፥ እርሱ በመረጠው መንገድ ማንንም ሊያድን ይችላል። ስለሆነም እግዚአብሔር በጥበቡና በምሕረቱ እንደ ኢሳ ያሉትን ሰዎች ማዳን አያዳግተውም። ሆኖም አዲስ ኪዳን ይህን የመሰለ ትምህርት አያስተምርም። የተደጋገመው የአዲስ ኪዳን ትምህርት፥ እግዚአብሔር ስለ ጌታ ኢየሱስ የሚናገረውን ሰምተው በእምነት የሚቀበሉትን እንደሚያድን ነው።

38ኛ ጥያቄ፡— ሰዎች ሊድኑ የሚችሉት ስለ ኢየሱስ በሚነገራቸው መልእክት ባላቸው እምነት ነው ስለሚለው አሳብ ምን አስተያየት አለን?

ሰዎች ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን መልእክት ሰምተው ስለማመናቸው ጠቃሚነት በምናስብበት ጊዜ፥ አንድ ግልጽ የሆነ አስተሳሰብ ሊኖረን ይገባል፥ ይህም በሕይወታችን ውስጥ ሊኖር የሚገባው ነገር ይህን መልእክት ከሌሎች ሰዎች ጋር መካፈል ነው። በአኗኗራችን ስለ ኢየሱስ ልንመሰክር ይገባናል። ስለዚህ በአኗኗራችን በስሙ ላይ ሐፍረትንም ወይም ነቀፌታን እንዳናደርስ መጠንቀቅ አለብን። ከመልካም ሕይወታችን ወይም አኗኗራችን በመነሣት፥ ስለ ኢየሱስ የምናቀርበውን የምሥራች ቃል የሚሰብና ሌሎች ሊቀበሉት የሚችሉት እንዲሆን መጣር ይገባናል (ቲቶ 2፡10)። ከዚህም በስተቀር ሁልጊዜ፥ ስለ ክርስቶስ የሚያወሳ መልእክት የምናቀርብበትን

አጋጣሚ ሁሉ መፈለግ ይገባናል። ከሰዎች ሁሉ ጋር ስለ ክርስቶስ የደኅንነት ደስታና በረከቶች ማካፈል እጅግ ከፍ ያለ ዋጋ ያለው ድርጊት ነው። ሰዎች ሊድኑና ከእግዚአብሔር ጋር ሊታረቁ የሚችሉበት መንገድ ክርስቶስ ብቻ ነው። ሁል ጊዜ ልታካፍሉት የሚገባችሁ ዜናም ይህ ነው።

አራተኛና አምስተኛ ቀን

ለመጨረሻ ፈተናችሁ ይረዳችሁ ዘንድ መጽሐፉን በሙሉ ከልሱ።

ሳምንታዊ የስብሰባ ጊዜ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ፦ በዚህ ሳምንት በተማራችሁት ትምህርት ወይም ጥቅስ ላይ የተመሠረተ ለጸሎት የሚሆን፥ መሪው ከአምስት እስከ አሥር ደቂቃ የሚደርስ የመልእክት ዝግጅት ያድርግ።

2. ሳምንታዊ የጸሎት ጊዜ፦ የአሥር ደቂቃ ጊዜ ለጸሎት ተጠቀሙ፥ ዳግም ለመወለድ ሉዓላዊ የሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ስለሚያስፈልጋቸው ስለምታውቋቸው ሰዎች ጸልዩ።

3. ክለሳ፦ በዚህ ሳምንት በተማራችሁት ትምህርት ላይ ከባድ የሆኑ መልስ ያልተሰጣቸው ጥያቄዎች እንዳሉ፥ እንዲሁም እያንዳንዱ ተማሪ ስለተማረው ትምህርት ለመመልከት እንዲችል አሥራ አምስት ደቂቃ ለክለሳ ተጠቀሙ።

4. ውይይት

4ሀ. በአካባቢአችሁ የሚኖሩ ሰዎች ስለ ጥምቀት ምን አስተያየት አላቸው? በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተሰጠው ትምህርት መሠረት፥ በእምነትና በጥምቀት መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት አድርጋችሁ ታብራራላችሁ?

4ለ. አንድ ሰው ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበለው ለመዳን ነው ቢላችሁ፤ ለዚህ ሰው መልሱን ለመስጠት በዚህ ሳምንት በተማራችሁት ትምህርት እንዴት ትጠቀማላችሁ?

4ሐ. ሕፃን ልጃቸው የሞተባቸውን ወጣት እናትና አባትን ለማጽናናት በዚህ ሳምንት በቀሰማችሁት ትምህርት እንዴት ትጠቀማላችሁ?

4መ. ሰዎች ሁሉ በመጨረሻው ጊዜ ይድናሉ ለሚል ሰው በዚህ ሳምንት ትምህርታችሁ በመጠቀም እንዴት ያለ መልስ ትሰጡታላችሁ?

4ሠ. በኢየሱስ ሞት ምክንያት፥ እግዚአብሔር ስለ ኢየሱስ ጨርሶ ያልሰሙትን ሰዎች ያድናቸዋል ለሚል ሰው በዚህ ሳምንት በተማራችሁት ትምህርት በመጠቀም እንዴት ያለ መልስ ትሰጡታላችሁ?

የቤት ሥራ

1. አንድ ኦርቶዶክስ ለሆነ ወዳጃችሁ፥ በተሠገም ውስጥ ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰብአዊነት ያላችሁን ግንዛቤ እንዴት ትገልጹለታላችሁ?
2. «ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ታምናለህ?» ብሎ ለሚጠይቃችሁ ሙስሊም ወዳጃችሁ ምን መልስ ትሰጡታላችሁ?
3. ዛሬ የኢየሱስ ትንሣኤና እርገት ለእኛ ምን ጥቅም አለው?
4. ኦርቶዶክሳዊ ወይም ሙስሊም ለሆነ ሰው የደኅንነትን መንገድ አብራራለት።
5. በክርስቶስ ማመናቸውን ያላወቁ፥ አሁን ግን ከኃጢአታቸውና ከደከመው እምነታቸው የተነሣ ክርስትናቸውን ያቆሙና ፍርሃት ላለባቸው ሰዎች የምትሰጡት ምክርና ትምህርት ምንድን ነው?